# የታሪክ ማስታወሻ

ከደጃዝማች ከበደ ተሰማ

ተኀትመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፴ወ፬ቱ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡
ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።



ዳግማዊ ፡ አጤ ፡ ምኒልክ ።



ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡
(በ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ) ።



ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ።
(፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ን ፡ ነ ፡ ዘኢትዮጵያ) ፡

# መግቢያ ፡

የዚህ ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ረቂቅ ፡ የጻፍሁት ፡ በ፲፱፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡
ኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ በስደት ፡ ሳለሁ ፡ ነበር ፤ የኢትዮጵያ ፡ የነጻነት ፡ጮራ ፡
በፈነጠቀበት ፡ ጊዜ ፡ ቀዳሚ ፡ መላክተኛ ፡ ሆኜ ፡ በሱዳን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በገባሁ ፡ ጊዜ ፡ ረቂቁ ፡ ከንዝ ፡ ጋር ፡ ቋራ ፡ ላይ ፡ ቀርቶ ፡ነበ
ርና ፡ ጠፋብኝ ። ቢሆንም ፤ ታሪኩ ፡ በአእምሮዬ ፡ ውስጥ ፡ ተቀርጾ ፡ሁል
ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ይለኝ ፡ ስለነበር ፡ በ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የዚህን ፡ ማስታወሻ ፡
ረቂቅ ፡ በድጋሚ ፡ ጻፍኩት ።

ኢየሩሳሌም ፡ ሳለሁ ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ፡ ያልሁትም ፡ ስለ ፡ ንግሥተ ፡
ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተጻፈው ፡ የቀድሞው ፡
ታሪክ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከሚለው ፡ ከም
ዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ ጀምሮ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ ከስደቱና ፡ ከጦርነቱ ፡ ዘመን ፡ ፍጻሜ ፡
በኋላ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ።

ይህን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ የጻፍኩበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡
እኔ ፡ በሕይወቴ ፡ ያየሁት ፡ በልጆቼና ፡ በቤተሰቤ ፡ ዘንድ ፡ እንዲታወቅ ፡
ለማድረግና ፡ እንደዚሁም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ በየጊዜው ፡
አግኝቶት ፡ የነበረውን ፡ ችግርና ፡ ትግል ፤ ይልቁንም ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳ
ማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ገና ፡ ከአልጋ ፡ ወራሽነታቸው ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡
ይደርስባቸው ፡ የነበረውን ፡ የችግር ፡ ፈተና ፡ እንደምን ፡ ባለ ፡ ትዕግሥ
ትና ፡ ብርታት ፡ አሳልፈው ፡ እዚህ ፡ ጊዜ ፡ የደረሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ለማ
ስረዳትና ፡ ወደፊትም ፡ ለሚደክሙበት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ መሰናክል ፡ ለሚ
ሆኑ ፡ መምከሪያና ፡ መመለሻ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ።

ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠውንና ፡ የመረጠውን ፤ ሰው ፡ ሊነ
ሳና ፡ ሊገፋው ፡ የማይችል ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ሲሆን ፤ ኢትዮጵ
ያም ፡ ለመቼውም ፡ ቢሆን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አገር፡ሆና፡
እንድትኖር ፡ መሪ ፡ እየሆኑ ፡ አደራው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚሰጣቸው ፡
ንጉሠ ፡ ነገሥቶቻችን ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተሰየሙልን ፡ መሆ
ናቸውን ፡ እያስታወስን ፤ አገሩ ፡ አገራችን ፤ ንጉሡ ፡ ንጉሣችን ፤ ብለን ፡
ቅን ፡ አገልግሎታችንን ፡ ሳናጓድል ፡ እንድንሠራ ፡ ለማስታወስ ፡ ነው ።

እላይ ፡ እንደተገለጠው ፡ ይህ ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ከተጻፈ ፡
ረዘም ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ አልፎአል ። ለመታተም ፡ የበቃው ፡ ግን ፤ በተማሪ ፡
ቤትና ፡ በመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተሠማርቼ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ካጋጠሙኝ ፡
ነገሮች ፡ አንድ ፡ አንዶቹን ፡ ያጫወትኋቸው ፡ ወዳጆቼ ፡ «ብዙዎቹ ፡ የማ

ናውቃቸው ፡ ታሪኮች ፡ ናቸውና ፡ ለምን ፡ በታሪክ ፡ መልክ ፡ አትጽፋቸውም» ፡ በማለት ፡ ስለአሳሰቡኝና ፡ ስለአደፋፈሩኝ ፡ ሲሆን ፡ ፲፱፻፰ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሥራ ፡ ምክንያት፡ አጋጥመውኝ ፡ ከነበሩት ፡ ነገሮች ፡ ትዝ ፡ ያሉኝንና ፡ ታሪክ ፡ ነክ ፡ የመሰሉኝን ፡ ቀደም ፡ ብዬ ፡ በዚህ ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ አስፍሬአቸው ፡ ስለነበረ ፡ የጠያቂዎቼን ፡ ፈቃድ ፡ ለማሟላት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መሠረቱ ፡ እላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ለልጆቼና ፡ ለእኔ ፡ ቤተሰቦች ፡ ለማሳወቅ ፡ የተጻፈ ፡ መሆኑን ፡ አንባቢዎች ፡ ተገንዝበውልኝ ፡ ለምን ፡ ሙሉ ፡ ታሪክ ፡ አልሆነም? የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ቢቀርብ ፡ ከዚህ ፡ በበለጠ ፡ ለመጻፍ ፡ ባለመቻሌ ፡ መሆኑን ፡ በትህትና ፡ እገልጣለሁ ። ወደፊት ፡ ግን ፡ ዕድሜ ፡ ቢሰጠኝና ፡ ዕድል ፡ ቢአጋጥመኝ ፡ ሁለተኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ሃሳብና ፡ ምኞት ፡ አለኝ ።

ከደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡

# መግለጫ ፡

ረዘም ፡ ካለ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ጽፌው ፡ የነበረውን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ እንዳሳትም ፡ ያበረታቱኝና ፡ በምክር ፡ የረዱኝ ፡ ብዙዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ሁሉንም ፡ አመሰግናለሁ ።

በተለይም ፡—

፩ኛ/ ስለጽሑፉ ፡ አቀማመጥና ፡ እትሙንም ፡ በመከታተል ፡ ክቡር ፡ ብላታ ፡ መርስዔ ፡ ኃዘን ፡ ወልደ ፡ ቂርቆስ ፡ ላደረጉልኝ ፡ ምክርና ፡ እርዳታ ፡ ሁሉ ፡ ምስጋናዬ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

፪ኛ/ በእጅ ፡ የጻፍኩትን ፡ ረቂቅ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲገለበጥ ፡ የረዱኝን ፡ አቶ ፡ መኩብብ ፡ ግርማኢየሱስን ፤ አቶ ፡ ውቤ ፡ ይማሙንና ፡ አቶ ፡ ሞገስ ፡ መንግሥቱን ፤ በመጨረሻም ፡ በመኪና ፡ ለማስገልበጥ ፡ ኃላፊነቱን ፡ ወስደው ፡ የግልበጣውን ፡ ሥራ ፡ የተከታተሉልኝን ፡ አቶ ፡ አስፋው ፡ ይትባረክንና ፡ በጽሕፈት ፡መኪና፡ በቅንነት ፡ የገለበጡልኝን ፡ ወይዘሮ ፡ ንጋቷ ፡ ተፈራን ፡ ከልብ ፡ አመሰግናቸዋለሁ ።

፫ኛ/ ሥራው ፡ ተጠናቅቆ ፡ ወደ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ከተላለፈ ፡ በኋላም ፡ አቶ ፡ ሰሎሞን ፡ አበበ ፡ የእርማቱን ፡ ሥራ ፡ በቅንነት ፡ በመከታተል ፡ ላደረጉልኝ ፡ እርዳታና ፡ እንደዚሁም ፡ የአርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅና ፡ ሠራተኞች ፡ ጠቅላላውን ፡ የእትም ፡ ሥራ ፡ እንዲቃናልኝ ፡ ላደረጉት ፡ ቅንነትና ፡ ትጋት ፡ ምስጋናዬ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሆኑ ፡ በመጽሐፌ ፡ ላይ ፡ እንዲገለጥ ፡ እወዳለሁ ።

በዚህ ፡ በተጻፈው ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ እንደተዳዩ ፡ አጋጣሚነት ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፤ ሰውዬው ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰበትን ፡ ሥራ ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ለመጻፍ ፡ ምኞት ፡ ነበረኝ ። ሆኖም ፤ የአንዳንዶቹን ፡ ማግኘትና ፡ መጻፍ ፡ ሲቻል ፡ የሌሎቹ ፡ ሊገኝ ፡ ባለመቻሉ ፡ መሳሳትን ፡ እንዳያስከትል ፡ የአብዛኛው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የተጻፈው ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ በተላለፈበት ፡ ዘመን ፡ በነበረው ፡ የማዕርግ ፡ ስሙ ፡ ነው ። «ታሪኩን ፡ በሠራበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ ለምን ፡ አልተጻፈም» ፡ የሚል ፡ ትችት ፡ ቢፈጠር ፡ በመቸገሬ ፡ መሆኑን ፡ አንባቢዎች ፡ እንዲገነዘቡልኝ ፡ እገልጣለሁ ።

መግለጫ ፡

እንደዚሁም ፡ እንደ ፡ ጉዳዩ ፡ አጋጣሚነት ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ስለሚገኝ ፡ ከጉዳዩ ፡ ጋር ፡ ስሙ ፡ የተጠራው ፡ ሰው ፡ ሥዕል ፡ እንዲኖር ፡ በብዙ ፡ ድካም ፡ ያንዳንዶቹ ፡ ተገኝቶ ፡ እንደታሰበው ፡ ሥፍራውን ፡ ለመያዝ ፡ ሲችል ፡ የሌሎቹ ፡ ሥዕል ፡ ከስማቸው ፡ ጋር ፡ ያልታተመው ፡ ሥዕላቸው ፡ ባለመገኘቱ ፡ ስለሆነ ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ ሳይሰጠው ፡ ምክንያቱ ፡ ይህ ፡ መሆኑ ፡ ታውቆ ፡ ይቅርታ ፡ እንዲደረግልኝ ፡ በትህትና ፡ እለምናለሁ ።

ደራሲው ።

# ማውጫ ፡


| | ገጽ ፤ |
|---|---|
| ምዕራፍ ፡ ፩ ፤ ደራሲው ፡ በልጅነት ፡ ዘመን ፤ በትምህርት ፡ ቤት ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ። | ፲፯ |
| ምዕራፍ ፡ ፪ ፤ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ በዙፋን ፡ ስለመቀመጣቸው ፤ በዘመናቸውም ፡ ስለተፈጸሙት ፡ አዳዲስ ፡ ሥራዎች ፡ | ፴፩ |
| ምዕራፍ ፡ ፫ ፤ በቶራ ፡ መስክና ፤ በሰገሌ ፤ በደሴና ፤ በመቅደላ ፡ በሌላም ፡ ስፍራ ፡ ውጊያ ፡ ስለመደረጉ ። | ፵፬ |
| ምዕራፍ ፡ ፬ ፤ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የአድማ ፡ ክስ ። አድመኞቹ ፡ በፍርድ ፡ ስለመቀጣታቸው ። | ፶፬ |
| ምዕራፍ ፡ ፭ ፤ወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ ወርቅና ፡ መሐመድ ፡ አባሻንቆ ፡ ስለመያዛቸው ። | ፶፯ |
| ምዕራፍ ፡ ፮ ፤ ስለደጃዝማች ፡ በየነ ፡ (ሊጋባው) ። | ፶፱ |
| ምዕራፍ ፡ ፯ ፤ ስለደጃዝማች ፡ በልቻ ፡ አባነፍሶ ። | ፷፩ |
| ምዕራፍ ፡ ፰ ፤ ደጃዝማች ፡ አባውቃውና ፡ ጊዜው ። | ፷፬ |
| ምዕራፍ ፤ ፱ ፤ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ የቋና ፡ ውጊያ ። | ፸፫ |
| ምዕራፍ ፡ ፲ ፤ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ (ፕሮቶኮል) ። | ፻ |
| ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፤ ኢትዮጵያ ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የማይጨው ፡ ጦርነት ። | ፻፲፭ |
| ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፤ ወደውጭ ፡ አገር ፡ በስደት ፡ ስለመሄድ ። | ፻፳፮ |
| ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፤ በስደት ፡ ዘመን ፡ በኢየሩሳሌም ። | ፻፷፪ |
| ምዕራፍ ፡ ፲፬ ፤ በአገር ፡ ውስጥ ፡ ላሉ ፡ አርበኞች ፡ በየጊዜው ፡ መልእክት ፡ ያደረሱ ። | ፻፹፱ |
| ምዕራፍ ፡ ፲፭ ፤ በሱዳን ፡ በኩል ፡ ወደኢትዮጵያ ፡ መግባት ። | ፪፻፯ |
| ምዕራፍ ፡ ፲፮ ፤ ወደ ፡ ጎጃም ፡ ስለመጓዛችንና ፡ በጉዞው ፡ ላይ ፡ የነበርነው ፡ ሰዎች ። ስራቆ ፡ ላይ ፡ ሳለን ፡ ስለላክሁት ፡ ራፖር ። | ፪፻፲፯ |

## ማውጫ ፡


ገጽ ፡

ምዕራፍ ፡ ፲፯ ፤ ወደጎጃም ፡ ስለመግባት ። ፪፻፶

ምዕራፍ ፡ ፲፰ ፤ ደጋ ፡ ዳሞት ፡ ከአርበኞች ፡ መሪዎች ፡ ጋር ፡ ስለመገናኘቴ ። ፪፻፺

ምዕራፍ ፡ ፲፱ ፤ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላኩ ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤዎችና ፡ ማስታወሻዎች ። ፫፻፲፫

ምዕራፍ ፡ ፳ ፤ ጠላት ፡ የሐሰት ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ስለመበተኑ ። ፫፻፴፪

ምዕራፍ ፡ ፳፩ ፤ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወሰን ፡ አልፈው ፡ ኦሜድላ ፡ ላይ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ ስለ መትከላቸው ። ፫፻፵፭

ምዕራፍ ፡ ፳፪ ፤ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተላኩልኝ ፡ የሥራ ፡ መምሪያ ፡ ደብዳቤዎችና ፡ ትእዛዞች ። ፫፻፷

ምዕራፍ ፡ ፳፫ ፤ ወደ ፡ መተከል ፡ ሄጄ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ እንደተገናኘሁ ። ፫፻፺

ምዕራፍ ፡ ፳፬ ፤ ስለ ፡ አገሩ ፡ ፍቅር ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ከድቶ ፡ የመጣ ፡ ባንዳ ፡ እንዳይጉላላ ፡ የተነገረ ፡ አዋጅ ። ፫፻፺፬

ምዕራፍ ፡ ፳፭ ፤ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለመጓዛቸው ። ፍቼ ፡ ከተማ ፡ ስለመግባታቸው ። ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ግርማዊ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለ መግባታቸው ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ሆነው ፡ የተናገሩት ፡ ታሪካዊ ፡ ንግግር ፡ ፬፻፲

ምዕራፍ ፡ ፳፮ ፤ ስለ ፡ አገርና ፡ ስለነፃነት ፡ ተባብሮ ፡ ስለመሥራት ፡ ምስጢርን ፡ ለባዕድ ፡ ማባከን ፡ እንደማይገባ ። ስለውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ። ፬፻፳፪

ምዕራፍ ፡ ፳፯ ፤ ነጻነት ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ስለተሾሙት ፡ ሚኒስትሮች ። የወለጋ ፡ ለቀምት ፡ አስተዳዳሪነት ፡ እንደተሰጠኝ ። በወለጋና ፡ በጐሬ ፡ በኩል ፡ የነበረው ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ተወግቶ ፡ ድል ፡ ስለመሆኑ ። ፖለቲካል ፡ ኦፊሰርስ ፡ በተባሉት ፡ የእንግሊዝ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ምክንያት ፡ በአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ስለነበረው ፡ ችግር ። ፬፻፵


# ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## በልጅነት ፡ ዘመን ፤- በትምህርት ፡ ቤት ፤- በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ።

### በልጅነት ፡ ዘመን ፤

ይህችን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ የጻፍሁ ፡ እኔ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ በ፲፰፻፺፬ ፡ ዓ፡ም፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በመንዝና ፡ ይፋት ፡ አውራጃ ፤ በኤፍራታ ፡ ወረዳ ፤ በለጋ ፡ ገምባ ፡ ምክትል ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ሰቀልቴ ፡ በተባለው ፡ ቀበሌ ፡ ከቀኛዝማች ፡ መንገሻ ፡ ኢያነህና ፡ ከወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ ተሰማ ፡ ተወለድሁ ። ሁለት ፡ ዓመት ፡ ሲሆነኝ ፡ የእናቴ ፡ አባት ፡ አዛዥ ፡ ተሰማ ፡ እንበሴ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አዛዥ ፡ ስለነበሩና ፡ መኖሪያቸው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ስለሆነ ፡ ከኤፍራታ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አስመጥተውኝ ፡ በአያቴ ፡ ቤት ፡ ስለአደግሁ ፤ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ መጠሪያ ፡ ስሜ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ሆነ ፤ በተወለድሁ ፡ በአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜዬ ፡ ያማርኛ ፡ ትምህርት ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ይኖሩ ፡ ከነበሩት ፡ ከመምሬ ፡ ግዛው ፡ ዘንድ ፡ መማር ፡ ጀመርሁ ።

### በትምህርት ፡ ቤት ፤

የአማርኛ ፡ ትምህርት ፡ መማር ፡ በጀመርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ትምህርቴን ፡ በሚገባ ፡ ከማጥናት ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጠውን ፡ ጊዜዬን ፡ የማሳልፈው ፡ ጨዋታ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ በመሄድ ፡ ነበር ። አያቴ ፡ አዛዥ ፡ ተሰማ ፡ ግን ፡ ትምህርት ፡ በደንብ ፡ እንድማር ፡ ፍላጐታቸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በየጊዜው ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ መዋሌንና ፡ ማጥናቴን ፡ ሲጠይቁኝ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ የማልለይና ፡ በርትቼም ፡ የማጠና ፡ መሆኔን ፡ እየነገርኳቸው ፡ ደስ ፡ ሲላቸው ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ መሄዴን ፡ ትቼ ፡ ጨዋታ ፡ ወዳለበት ፡ ቦታ ፡ እየሄድኩ ፡ መዋልን ፡ እመርጥ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በላይ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ሳልሄድ ፡ እቆያለሁ ። አያቱም፡ አስተማሪዬን ፡ ባገኙዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ስለትምህርቴ ፡ ውጤት ፡ «እንደ ፡ ምንድንነው ፡ ደኅና ፡ ያጠናል ፡ ወይ»? ፡ ብለው ፡ ሲጠይቋቸው ፡ እንኳን ፡ ሊያጠና ፡ እተማሪ ፡ ቤትም ፡ ከመጣ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ሆኖታል ፡ አይቼውም ፡ አላውቅ ፡ ብለው ፡ ይነግሯቸዋል ። አያቴም ፡

ተናደው ፡ እቤት ፡ ሲያስፈልጉኝ ፡ ያጡኛል ። እኔ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ሄጄ ፡ ውዬ ፡ ማታ ፡ እቤቴ ፡ ስገባ ፡ የሚቆየኝ ፡ መታሠር ፡ መገረፍ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ አያቴ ፡ ምንም ፡ ቢገርፉኝና ፡ ቢያስሩኝ ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ እየሄድኩ ፡ ትምህርቴን ፡ የማልማር ፡ ሆኜ ፡ ስላስቸገርኩ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ከተማርኩ ፡ በኋላ ፡ ወላጅ ፡ አባቴን ፡ ጠርተው ፡ ውሰድልኝ ፡ አሏቸውና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ አገር ፡ ኤፍራታ ፡ ወደ፡ ተባለው ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ ተመለስኩ ። እዚያም ፡ ስደርስ ፡ አሁንም ፡ ያባቴ ፡ አባት ፡ አቶ ፡ አያንህ ፡ የሚኖሩት ፡ ኤፍራታ ፡ ስለሆን ፡ ለሳቸው ፡ ተሰጠሁ ፤ ያሁኑ ፡ አያቴ ፡ ያባቴ ፡ አባት ፡ ትምህርት ፡ ሙያ ፡ የማይመስ ላቸው ፡ ሙያ ፡ ተብሎ ፡ የሚቆጠረው ፡ ግብርና ፡ ጀግንነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ ናቸው ። እንዲያውም ፡ አስተማሪዬን ፡ «ይህ ፡ እከካም፡ ተማሪ፡ ልጄን ፡ በኩርኩም ፡ ሊመታው ፡ ነው ፡ ወይ ? አይደረግም ፤ የኔ ፡ ልጅ ፡ አምርቶ ፤ ጋልቦ ፤ ተኩሶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚበላው ፡ ጥንቆላ ፡ ተምሮ ፡ አይደለም» ፡ በማለት ፡ መማርን ፡ የሚከለክሉ ፡ ነበሩ ።

እኔም ፡ የማደላው ፡ የአሁኑ ፡ አያቴ ፡ ወደሚአስበት ፡ ዓላማ ፡ ስለነበረ ፡ ትምህርትን ፡ እርግፍ ፡ አድርጌ ፡ ትቼ ፤ አያቴ ፡ አቶ ፡ አያንህ ፡ በለጥ ፡ ኑሮአቸው ፡ በግብርና ፡ ስለነበር ፤ የእርሻ ፡ ቦታቸው ፡ ከመኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ሀያ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ያህል ፡ ርቆ ፡ ከሚገኝ ፡ በማጀቴ ፡ አሻ ጋራ ፡ ከሚታየው ፡ ሜዳ ፡ አይሮርና ፡ ውላ ፡ አብዬ ፡ በተባለ ፡ ቆላ ፡ መሬት ፡ ስለሆን ፤ በጠዋት ፡ ተነስተው ፡ በበቅሎ ፡ እየተጓዙ ፡ እዚያው ፡ እየዋሉ ፡ ማታ ፡ ይመለሳሉ ። ምሳም ፡ ባገልግል ፡ እየተዘጋጀ ፡ በበቅሎአቸው ፡ ዳራ ፡ እየያዙ ፡ ይሄዳሉ ። እኔም ፡ እሳቸውን ፡ እየተከተልኩ ፡ በዚያው ፡ በእርሻ ፡ ቦታ ፡ ውዬ ፡ ማታ ፡ እሳቸው ፡ ሲመለሱ ፤ አብሬ ፡ እመለሳለሁ ።

ገበሬዎቹ ፡ በሬዎቹን ፡ እንደተጠመዱ ፡ እያቆሙ ፡ ውሃ ፡ ለመጠጣት፡ ሆር ፡ ሲሉ ፡ እርፍ ፡ ጨብጬ ፡ ለማረስ ፡ እታገል ፡ ነበር ። በቀጥታ ፡ማረስ፡ ሲቀናኝ ፤ በሮቹ ፡ በሚዞሩበት ፡ ጊዜ ፡ በእርፉ ፡ ሞፈሩን ፡ አንስቶ ፡ ማዞ ርና ፡ ከማረሻውና ፡ ከወገሉ ፡ መሐል ፡ በማረሻው ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ጭቃ ፡ ለእርሻው ፡ እንዲያመች ፡ ማላቀቁ ፡ ጥቂት ፡ ያስቸግረኝ ፡ ነበር ። ገበሬዎቹ ፡ ከሄዱበት ፡ ወዲያው ፡ ሲመለሱ ፡ ተቀብለውኝ ፡ እነሱ ፡ ሲያ ርሱ ፡ እኔ ፡ ባካባቢው ፡ ከሚገኘው ፡ ዱር ፡ የቊርቊራ ፡ ፍሬና ፤ የእንኮይ ፡ ፍሬ ፤ አጋምና ፡ ደደሆ ፡ የሞላበት ፡ ጫካ፡ ስለሚገኝ፡ ወደዚያ ፡ ተሰማርቼ፡ ከብት ፡ ከሚጠብቁት ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ሆኜ ፡ ስለቅምና ፡ ስመገብ ፡ ነበር ፡ የምውለው ። አያቴም ፡ በበቅሎ ፡ ከአንደኛው ፡ ማሳ ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ ሲያሳርሱ ፡ ውለው ፡ ማታ ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሲመለሱ ፡ አረኞች ፡ እንጨት ፡ ለቅመው ፤ ተሸክመው ፡ ከብቶቻቸውን ፡ እየነዱ ፡ ገበሬዎቹም ፡ ሲያርሱባቸው ፡ የዋሉትን ፡ በሬዎች ፡ እየነዱ ፡ ቀንበሩ ፡ በበሬዎቹ ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሞፈሩን ፡ ከነእርፉ ፡ ተሸክመው ፡



እያቅራሩ ፡ አቀበቱን ፡ ሳይታወቃቸው ፡ ይወጡታል ። እኔም ፡ ከሚመስ ሉኝ ፡ ልጆች ፡ ጋር ፡ ሲዘፍኑ ፡ እየዘፈንኩ ፤ አቶ ፡ አያንህም ፡ ከኋላችን ፡ ሆነው ፡ ለሚሸልሉት ፡ አንዳንድ ፡ የሽለላ ፡ ግጥም ፡ እየነገሩ ፡ ይጓዛሉ ።

በሥራ ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሥራ ፡ ሲውሉ ፡ በበዓል ፡ ቀን ፡ ማጀቴ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለምና ፡ ሳንቃ ፡ በር ፡ ማርያም ፡ ሲሄዱ ፡ አብሬ ፡ እሄድ ፡ ነበር ።

የትምህርት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አይታሰብም ፡ ነበር ። ማታ ፡ ማታም ፡ እሳት ፡ ዳር ፡ በእግራም ፡ አንኮላ ፡ (እቦሬ) ፡ ጠላው ፡ እየተቀዳ ፡ እየተጠጣ ፡ ሽለላ ፡ የሚያውቁት ፡ እየሸለሉ ፡ በየጊዜው ፡ በጥሙጋ ፡ ሲዘምት ፡ የተ ገኘው ፡ ሙያ ፡ እየተተረከ ፡ ያመሻሉ ።

ከግጥሞቹም ፡ ትዝ ፡ የሚሉኝ ፡ የሚከተሉት ፡ ነበሩ ።

አንሸሽም ፡ አንሸሽም ፡ አንሸሽም ፡ ብንሸሽም ፡ ተጓደን ፤
ሽሽት ፡ ነውራችን ፡ ነው ፡ ሰቀልቴ ፡ ተወልደን ።
ሴትም ፡ አይደል ፡ ሴትም ፡ አይደል ፡ የወንድ ፡ ነው ፡ ምጡ ፤
አዳል ፡ ምድር ፡ ወርዶ ፡ ፋርሲን ፡ ሲረገጡ ።
እምቢ ፡ ብሎ ፡ እንደሁ ፡ ጠላት ፡ ደድሮ ፡
የሰቀልቴን ፡ ልጅ ፡ አዙረው ፡ ቶሎ ።
እንዲበትነው ፡ እንደዛር ፡ ቆሎ ።
ይሳባል ፡ እንጂ ፡ ሰንጋ ፡ አይነዳም ፡
ጉራች ፡ አያንህ ፡ ሻሚ ፡ መተኮ ፡ የሚዳው ፡ ገዳም ።
የሚዳ ፡ ጋላ ፡ ልጅዋን ፡ ስትቀጣ ፤
ብላ ፡ ትላለች ፡ መተኮ ፡ መጣ ፡
እያየህ ፡ ተጓዝ ፡ ተው ፡ ትሞታለህ ፡
ሻሚ ፡ መተኮ ፡ ጉራች ፡ አያንህ ፡
አይወረውሩት ፡ የእሳት ፡ አሎሎ ፡
አይቆረጥሙት ፡ የብረት ፡ ቆሎ ፡
የቢያደግልኝ ፡ ልጅ ፡ በድሌ ፡ ኖሮ ፡

እኛም ፡ ልጆቹ ፡ ዙሪያውን ፡ ከበን ፡ እሳት ፡ እየሞቅን ፡ የነሱን ፡ ጨዋታና ፡ ታሪክ ፡ ስንሰማ ፡ እናመሻለን ፡ በአያቴ ፡ በአቶ ፡ አያንህ ፡ በለጥ ፡ በንድ ፡ የአስተዳደጌ ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሆኖ ፡ ከትምህርት ፡ የማልገናኝ ፡ መሆኔንና ፡ የአባታቸውን ፡ ሀሳብ ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ወላጅ ፡ አባቴ ፡ ቀኛዝማች ፡ መንገሻ ፡ አያንህ ፡ ሡረት ፡ እህታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ሙሉነሽ ፡ አያንህ ፡ ዘንድ ፡ ሆኜ ፡ የጀመርኩትን ፡ የአማርኛ ፡ ትምህርት ፡ እንድጨርስ ፡ አደረጉኝ ። የአማርኛ ፡ አስተማሪዬም ፡ ሡረት ፡ ቊስቋም ፡ በተባለው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚኖሩ ፡ አለቃ ፡ ወልዴ ፡ ሐና፡ ይባላሉ ።

አዲስ ፡ አበባም ፡ ሆን ፡ ኤፍራታ ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ባካባቢዬ ፡ የሚገኙት ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ስለነበሩ ፡ ከላይ ፡ እንደተረክሁት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜዬን ፡ የማሳልፈው ፡ በጨዋታ ፡ ነበር ።

በየጊዜው ፡ በዓሉንና ፡ ጊዜውን ፡ እየተከተለ ፡ የሚመጣው ፡ የጨዋታ ፡ ዓይነት ፡ ብዙ ፡ ነው ። በትንሣኤ ፡ ዘመን ፡ ጊጤና ፤ ኳስ ፡ ምክቶሽ ፡ ቅምምጦሽ ፡ በቡድን ፡ እየሆኑ ፡ የሚጫወቱት ፡ አለ ። በልደት ፡ ገና ፡ ጨዋታ ፡ ነበር ። ከእንጨት ፡ ስር ፡ የተድበለበለ ፡ እሩር ፡ ከጠፍር ፡ የሚሠራ ፡ ጥንግ ፡ መጨዋቻ ፡ ይሆናል ። የገና ፡ መጫወቻው ፡ ቦታ ፡ እቅብቅብ ፡ ውስጥ ፡ ነው ። የገና ፡ ጨዋታ ፡ በጣም ፡ እወድ ፡ ነበር ። አዲስ ፡ አበባም ፡ በነበርኩበት ፡ ጊዜ ፡ ከልጆች ፡ ጋር ፡ ሆነን ፡ ደግሞ ፡ ጭቃውን ፡ እያቦካን ፡ እንደ ፡ ጠመንጃ ፡ እንሠራና ፡ መሐከሉ ፡ በጣም ፡ ስስ ፡ ሆኖ ፡ በጠፍጣፋው ፡ እንደጣባ ፡ ሆኖ ፡ ይዘጋጅና ፡ ጦርነት ፡ እንግጠም ፡ እንልና ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የሚመጡ ፡ ፈረንጆች ፡ በፈረስ ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ሲመጡ ፡ እየጠበቅን ፡ አጠገባችን ፡ ሲደርሱ ፡ መደዳውን ፡ እንተኩሳለን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ፈረሶቻቸው ፡ እየደነበሩ ፡ ተቀማጮቹ ፡ ሲቸገሩ ፡ እኛ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ በደስታ ፡ እንቦርቃለን ።

እንደዚህ ፡ በምናደርግበት ፡ ባንደኛው ፡ ቀን ፡ ከወደ ፡ ቀበና ፡ ሁለት ፡ ሰው ፡ በፈረስ ፡ ያስከተለ ፡ እሱም ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ አንድ ፡ ፈረንጅ ፡ ሲመጣ ፤ ጠበቅንና ፡ እንደልማዳችን ፡ ተኩስንበት ፡ እርሱም ፡ ተጠንቅቆ ፡ መጥቶ ፡ ኖሮ ፡ በጉማሬ ፡ አለንጋ ፡ እያንዳንዳችንን ፡ ይገርፈን ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ለመከላከል ፡ እጄን ፡ ሳወዛውዝ ፡ የጉማሬው ፡ አለንጋ ፡ እጄ ፡ ውስጥ ፡ ሲገባልኝ ፡ ነጠቅሁትና ፡ ሸሸሁ ። እነርሱም ፡ በፈረስ ፡ ተከተሉኝ ። የመንገዱ ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ ፈረፈር ፡ ስለነበር ፡ እፈረፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብቼ ፡ ስሮጥ ፡ ከፈረሱ ፡ ወረደና ፡ መጣ ። ከፈረፈሩ ፡ ወጣሁና ፡ እየሮጥኩ ፡ እንደገና ፡ ከፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣና ፡ ተከተለኝ ። የማላመልጥ ፡ መሆኔን ፡ ስላወቅኩ ፤ አለንጋውን ፡ ወደ ፡ ፈረፈሩ ፡ ወረወርኩትና ፡ እሩጫዬን ፡ ቀጠልኩ ። ፈረንጁም ፡ ከፈረሱ ፡ ወርዶ ፡ አለንጋው ፡ ወደተወረወረበት ፡ ወደፈረፈሩ ፡ ሲገባ ፡ ለማምለጥ ፡ ቻልኩ ። የአዲስ ፡ አበባውን ፡ ትምህርት ፡ የከለከሉኝ ፡ ጨዋታዎች ፡ የዚህ ፡ ዓይነቶች ፡ ሲሆኑ ፡ ወደ ፡ ኤፍራታ ፡ ከሄድኩ ፡ በኋላ ፡ የነበሩትን ፡ የጨዋታ ፡ ዓይነቶች ፡ እቀጥላለሁ ።

፩ ፤ በትንሣኤ ፡ ሰሞን ፡ ግተም ፡ የተባለ ፡ እንጨት ፡ እንደቁልቋል ፡ ያለ ፡ በመሐል ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ይቆማል ። ስገድ ፡ የሚባለው ፡ እንጨት ፡ በዘንግ ፡ መልክ ፡ እየሆነ ፡ ይሾልና ፡ ሃያም ፤ ሠላሳም ፡ ሰው ፡ አንዳንድ ፡ ይዞ ፡ ይመጣና ፡ የሁሉንም ፡ በየተራ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይይዝና ፡ ሃያ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ወደፊት ፡ ሳይንደረደር ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ቆሞ ፡ እየወረወረ ፡ ይወጋል ። እንደ ፡ አነጣጣሪነቱ ፡ ባንድ ፡ ዘንግ ፡ ወይም ፡ በገሚሱ ፡ የሚወጋ ፡ አለ ። በሁሉም ፡ የሚስት ፡ አለ ። የወጋው ፡ ነጻ ፡ እየሆነ ፡ ሲሄድ ፡ የሳተው ፡ መደዳውን ፡ ይተኛና ፡ የወጋው ፡ ሁሉ ፡ እየረገጠው ፡ ያልፋል ።



፪ ፤ ኳስ ፡ ጨዋታ ፡ እንደዚሁ ፡ ከሃያ ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ ላይ ፡ ይሆንና ፡ በቡድን ፡ ተለይቶ ፡ የወዲህኛው ፡ ቡድን ፡ ለወዲያኛው ፡ ቡድን ፡ በዱላ ፡ ኳሷን ፡ ይለጋታል ። የቀለቡ ፡ እንደሆን፡ የቀለበው ፡ ወገን ፡ ለጊው ፡ እለጋበት ፡ ቦታ ፡ መጥቶ ፡ እተቀለበበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ በየቡድኑ ፡ ይቀመጥበትና ፡ ይጋልበዋል ። የተለጋለት ፡ ሳይቀልብ ፡ የቀረ ፡ እንደሆን ፡ ያልቀለበው ፡ ወገን ፡ እተለጋበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ መጥቶ የለጊውን ፡ ወገን ፡ ኳሱ ፡ አረፈችበት ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡ ተሸክሞ ፡ ይወስዳል ። አሸካከሙ ፡ መሐል ፡ እንደኩብት ፡ እግሩን ፡ አድርጎ ፡ ነው ። እትከሻው ፡ ላይ ፡ ሲወጣም ፤ ተጋላቢው ፡ እጁን ፡ እንደ ፡ ርካብ ፡ አድርጎ ፡ ይቀርብና ፡ ያን ፡ ተረግጦ ፡ ነው ፡ እትከሻው ፡ ላይ ፡ የሚወጣው ። ጋላቢው ፡ መጀመሪያ ፡ የለጋው ፡ ኳስ ፡ አረፈችበት ፡ ሲደርሱ ፤ በሰውዬው ፡ ግንባር ፡ ትክክል ፡ አድርጎ ፡ ዱላውን ፡ ወደ ፡ ኳስ ፡ ይሰድና ፡ የወጋት ፡ እንደሆን ፡ እንደገና ፡ በሰውዬው ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ኳሱን ፡ ይሰጡትና ፡ ይለጋና ፡ አሁንም ፡ ኳስ ፡ እደረሰችበት ፡ ድረስ ፡ ተሸክመው ፡ ይሄዳሉ ። ካልተሳተ ፡ እንዲሁ ፡ ሲጋልብ ፡ መዋል ፡ ነው ።

፫ ፤ ቅምምጦሽ ፡ የሚባለው ፡ ጨዋታ ።

ተጫዋቾቹ ፡ ልጆች ፡ ኳስ ፡ ይዘው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ኳሷን ፡ እያነጠሩ ፡ ሲጫወቱ ፡ ኳሷን ፡ አንዱ ፡ ሲያነጥር ፡ አንዱ ፡ የቀለበ ፡ እንደሆን ፡ ያነጠረው ፡ ላይ ፡ ይወጣና ፡ ኳሷን ፡ ሲያነጥር ፡ ከምድር ፡ ዙሪያውን ፡ ያከበበው ፡ ለመቅለብ ፡ ይሻማል ። እሰውዬው ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ እሰውዬው ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጠ ፡ የአነጠረውን ፡ ኳስ ፡ መልሶ ፡ የቀለበ ፡ እንደሆን ፤ ሰውዬውን ፡ እንደተቀመጠ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እቀለበ ፡ ድረስ ፡ በሰውዬው ፡ እንደተቀመጠ ፡ ይቆያል ። እሰውዬው ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ ኳሷን ፡ ሲአነጥር ፡ ራሱ ፡ በቀለበ ፡ ቁጥር ፡ ባካባቢው ፡ ያለው ፡ ተጫዋች ፡ ነወር ፡ ነወር ፡ እያለ ፡ ጐንበስ ፡ ይላል ። ሳይጐንብስ ፡ ወይንም ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ እንደቆመ ፡ በኳስ ፡ ወርዋሮ ፡ የተመታው ፡ ሰው ፡ ባለዕዳ ፡ ሆኖ ፡ ይቆያል ። እሰውዬው ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ ልጅ ፡ ያነጠረው ፡ ኳስ ፡ የተቀለበበት ፡ እንደሆን ፡ ቀላቢው ፡ ይቀመጥበታል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ በኳስ ፡ የተመታው ፡ ባለዕዳ ፡ ያለ ፡ እንደሆን ፡ እሱን ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጥና ፡ እርሱ ፡ ነጻ ፡ ሆኖ ፡ እንደገና ፡ ይጫወታል ።

፬ ፤ ምክት ፡ እንደዚሁ ፡ በቡድን ፡ ሆኖ ፡ እየተመለከተ ፡ ኳሷን ፡ በፍጥነት ፡ በማንሳትና ፡ በመምታት ፡ ብልጫ ፡ ያሳየ ፡ አሸናፊ ፡ ይሆናል ።

፫ ፡ ለቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ችቦ ፡ ያበሩና ፡ የታች ፡ አምባና ፡ የላይ ፡ አምባ ፡ የሚገናኙበት ፡ ሜዳ ፡ አለ ። በአበራው ፡ ችቦ ፡ ይደባደባል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አሸናፊው ፡ ወገን ፡ ሆ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይሄዳል ፡ ጠዋት ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሴቱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲዘፍን ፡ ወንዱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሲጨፍር ፡ ይውላል ።

፬ ፡ በቡሄ ፡ ጅራ ፡ ከሚባለው ፡ ትልቁ ፡ ወንዝ ፡ (ጅረት) ፡ ድረስ ፡ ሄዶ ፡ ከወዲህ ፡ ማዶና ፡ ከወዲያ ፡ ማዶ ፡ ያለው ፡ ወንዝ ፡ መልካ ፡ ላይ ፡ ይጋረፋል ። በፊት ፡ ትንንሽ ፡ ልጆች ፡ ይጋጠሙና ፡ ያንደኛው ፡ ወገን ፡ ያሸነፈ ፡ እንደሆነ ፡ ጐረምሳው ፡ ይነሳል ። ይጋጠማል ። አሁንም ፡ ያንደኛው ፡ ወገን ፡ ያሸነፈ ፡ እንደሆነ ፡ ሽማግሌው ፡ ሳይቀር ፡ ይገባና ፡ የመጨረሻውን ፡ ድል ፡ አገኝ ፡ ድረስ ፡ ይጋረፋል ። ለመጨረሻው ፡ ድል ፡ ሸሽቶ ፡ የሚደርስበት ፡ ከሁለቱም ፡ በኩል ፡ የተወሰነ ፡ ቦታ ፡ አለ ። እዚያ ፡ አባር ፡ ካደረሰ ፡ አያልፍም ። ማሸነፉን ፡ አረጋገጠ ፡ ማለት ፡ ነው ። ያን ፡ ያለፈ ፡ እንደሆነ ፡ ጅራፍ ፡ መሆኑ ፡ ይቀርና ፡ ጦርና ፡ ጐራዴ ፡ ይተኳለ ፋል ። ጨዋታነቱ ፡ ቀረ ፡ ማለት ፡ ነው ። ላገር ፡ ይተርፋል ። ይህን ፡ ጨዋታ ፡ ለማየት ፡ ሄጄለሁ ፡ እንጂ ፡ ቡድን ፡ ውስጥ ፡ ገብቼ ፡ ለመጫወት ፡ አልሞ ክርኩም ።

፭ ፡ በልደት ፡ ላይ ፡ የገና ፡ ጨዋታ ፡ መሆኑን ፡ በመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ገልጫለሁ ። አሁን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ የደገምኩት ፡ ሥርአቱን ፡ ለመ ግለጽና ፡ በጣም ፡ የምወደውም ፡ ጨዋታ ፡ ስለነበር ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ይመረጡና ፡ የቡድን ፡ አባት ፡ ይባላሉ ። ከተሰበሰበው ፡ ልጅ ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ እየሆኑ ፡ ወደ ፡ ቡድን ፡ አባቶች ፡ ይሄዳሉ ። ለም ሳሌ ፡ የቡድን ፡ አባቶች ፡ ይልና ፡ ከአንበሳ ፡ ከነብር ፡ ከእንጀራ ፡ ከጠላ ፡ ከገደል ፡ ከሾተል ፡ ይላል ። የቡድኑ ፡ አባት ፡ አንበሳ ፡ ያለ ፡ እንደሁ ፡ ለርሱ ፡ አንበሳ ፡ ያለው ፡ ሲሰጥ ፡ ቀሪው ፡ ለሌላኛው ፡ ቡድን ፡ ይገባል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምርጫው ፡ ሲያልቅ ፡ የቡድን ፡ አባቶች ፡ እሩሯን ፡ መሐል ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ገብተው ፡ ምግ ፡ ተያይዘው ፡ ይለጋሉ ። እንደፍጥነቱ ፡ ጥን ጓን ፡ ወይም ፡ እሩሯን ፡ የያዛት ፡ ለመለጋት ፡ ሲለቅ ፡ አንደኛው ፡ ቀለብ ፡ ያደረጋት ፡ እንደሆን ፡ እንደፍጥነቱ ፡ ይለጋታል ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ብር ታትን ፡ የሚጠይቅ ፡ ጨዋታ ፡ ይሆንና ፡ እንደጥንጓ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየሮጡ ፡ ጥንጓን ፡ ወደ ፡ ተወሰነው ፡ ግብ ፡ ለማግባት ፡ የሚደረገው ፡ ትግል ፡ ራስን ፡ እስከመርሳት ፡ የሚያደርስ ፡ ነው ። የግብ ፡ ብልጫ ፡ ያገ ኘው ፡ ሆ ፡ እያለ ፡ አሸናፊነቱን ፡ በመግለጥ ፡ ከተጨዋቾቹ ፡ ስም ፡ እየ ጠራ ፡ እንደ ፡ ሰውዬው ፡ ሁናቴ ፡ በመልኩ ፡ ዓይነት ፡ እየገጠመ ፡ ይሰ ድበዋል ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ስድቡ ፡ ያማርርና ፡ እመደባደብ ፡ ላይ ፡ ይደ ረሳል ።



ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ እንዲታወቅ ፡ በጨዋታው ፡ ላይ ፡ የሚገጠሙትን ፡ ግጥሞች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ እጠቅሳለሁ ።

ለቀጭን ፡ ጌታው ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ ይችን ፡ እግር ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ አል
ሄድባትም ፡
እየቆራረጥሁ ፡ እጥላለሁ ፡ የትም ።
ሲሄድ ፡ ቅትር ፡ ቅትር ፡ ሲበላ ፡ እንደአንበጣ ፡
ወዘና ፡ የሌለህ ፡ መጣይ ፡ የጨጓራ ፡ ቋንጣ ፤
ዘወር ፡ በል ፡ ከፊቴ ፡ በሽታዬ ፡ መጣ ።

ለአጭር ፡ ጌታው ፡ አቶ ፡ እገሌ ፡ አሎሎ ፡ ቁመት ፡ ዶሮ ፡ ሙሃይት ፡
ሰው ፡ እንዴት ፡ ይወልዳል ፡ አስመስሎ ፡ ጃርት ።

ለረጅም ፡ ይህን ፡ ረጅሙን ፡ ጐሚዶ ፡ ጐሚዶ ፡
ገሚሱን ፡ በርጩማ ፡ ገሚሱን ፡ ማገዶ ፡

ለለንቦጫሙ ፡ እኔ ፡ እሰድብሃለሁ ፡ አንተ ፡ ስማኝ ፡ ብቻ ፡
ከንፈርህ ፡ ቅልብስ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ስልቻ ።

ወትሮ ፡ ትምህርቱን ፡ ጨረሰ ፡ ተብሎ ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ አባል ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ የሚመረቀው ፡ ፊደልና ፡ ፊደለ ፡ ሐዋርያት ፡ ቆጥሮ ፡ ገበታ ፡ ሐዋርያት ፡ አርጋኖን ፡ ወንጌል ፡ አንብቦ ፡ ዳዊት ፡ ደግሞ ፡ ሲጨ ርስ ፡ ስለሆነ ፡ እኔም ፡ በጊዜው ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ትምህርት ፡ ጨርሼ ፡ ዳዊት ፡ ከደገምኩ ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደገና ፡ አባቴ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ይዘውኝ ፡ መጥተው ፡ ላያቴ ፡ ለአዛዥ ፡ ተሰማ ፡ ሰጡኝ ፡ አያቴም ፡ ጥንቱን ፡ ተባልተውኝ ፡ የነበረው ፡ ትምህርት ፡ አል ማርም ፡ በማለቴ ፡ ስለነበር ፡ ዳዊት ፡ ደግሜ ፡ መምጣቴን ፡ በመስማታ ቸው ፡ በጣም ፡ ስለተደሰቱ ፡ ዳዊት ፡ አመጡና ፡ እንድፈተን ፡ ተደረገ ። ፈተና ፡ የሚደረገው ፡ ከዳዊቱ ፡ መጀመሪያ ፡ «ፍካሬ ፡ ዘጻድቃን ፡ ወዘኃ ጥአን» ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ መዝሙር ፤ ከመጨረሻው ፡ ንዑስ ፡ አነ ፡ እምእ ኃውየ ፡ የሚለውን ፡ አንድ ፡ መዝሙር ፡ ስለሆነ ፡ በንባብ ፡ ተፈተንኩና ፡ አያቴ ፡ አዛዥ ፡ ተሰማ ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፡ ሙሉ ፡ ልብስ ፡ ተሸለምኩ ።

## በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፤

በ፲፱፻፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ እንዳገኝ ፡ አስገብተውኝ ፡ ልምምዴን ፡ ስቀጥል ፡ ቆየሁ ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥቱን ፡ ለቀው ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ በሕዝብ ፡ ተመርጠው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ሲወጡ ፤ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ መሥ

ሪያ ፡ ቤት ፡ እሠራ ፡ የነበረውን ፡ የሥራ ፡ ልምምድ ፡ አቋርጨ ፡ በንግሥት ፡ ንግሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ እልፍኝ ፡ እንደ ፡ ሀገር ፡ ልማድ ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ ደንብ ፡ ገብቼ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንድማር ፡ አያቴ ፡ አዛዥ ፡ ተሰማ ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ አቅርበው ፡ እጅ ፡ አስነሱኝ ። ባልደረባም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዋና ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ የነበሩትን ፡ ፊታውራሪ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ከተሬን ፡ ተቀብዬ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሥራ ፡ አገልግሎቱን ፡ ቀጠልሁ ።

እንግዲህ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ዠምሮ ፡ በትምህርትም ፡ ሆነ ፡ በሥራ ፡ ያደግሁት ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በዚያም ፡ ዘመን ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተቋቁሞ ፡ ስለነበረ ፡ ለመማር ፡ ገብቼ ፡ ከተመዘገብሁና ፡ ኤ ፡ ቢ ፡ ሲ ፡ ዲ ፡ ብዬ ፡ ፊደል ፡ መቁጠር ፡ ከጀመርኩ ፡ በኋላ ፡ ትምህርቴን ፡ አቋረጥሁ ። ምክንያቱም ፡ በጊዜው ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሆኖ ፡ ማደግ ፡ ከትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እየተማረ ፡ እንደ ፡ ማደግ ፡ የሚቆጠር ፡ ስለነበር ፡ አያቴ ፡ አዛዥ ፡ ተሰማ ፡ ይህን ፡ ልማድ ፡ በመከተልና ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ እድገት ፡ ይልቅ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ማደጉ ፡ የበለጠ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ በመገመታቸው ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ አስወጥተው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስላስገቡኝ ፡ ነው ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እቤተ ፡ መንግሥት ፡ በገባሁበት ፡ ዘመን ፡ የትምህርት ፡ ጣዕሙ ፡ እንዳሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ታውቆ ፡ ያልከበረበት ፡ ስለነበረ ፤ ከዚያ ፡ ወጥቼ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ልግባ ፡ ብል ፡ አንደኛ ፡ አገልግሎት ፡ የመሸሽ ፡ ግምት ፡ ይሆንብኛል ፡ በማለት ፤ ሁለተኛም ፡ ከፊታዴ ፡ ወጣሁ ፡ በማለት ፡ ያያቴን ፡ ርግማን ፡ የሚያስከትልብኝ ፡ ስለሆነ ፤ በአስያዙኝ ፡ ሥራ ፡ መጠንከርን ፡ መረጥሁ ፤ አያቴም ፡ ለሁሉጊዜ ፡ ይመክሩኝና ፡ ያስጠኑኝ ፡ የነበረው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፤ ንጉሥን ፡ በቅንነት ፡ ማገልገል ፤ በማንም ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ በምቀኝነት ፡ የተንኰል ፡ ሥራ ፡ አለመሥራትን ፤ ብቻ ፡ ነበር ፤ ትምህርት ፡ ጊዜን ፡ ተከትሎ ፡ የሚመጣ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ጊዜው ፡ ራሱ ፡ ስላልፈቀደልኝ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ቋንቋ ፡ ከመማር ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ትምህርትና ፡ እውቀት ፡ ይቆጠር ፡ የነበረው ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የአስተዳደር ፡ ዘዴ ፡ ነበር ፤ ከዚህም ፡ አንዱ ፡ ለዚህ ፡ ትምህርት ፡ ጠቃሚ ፡ የነበረው ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ ደንብ ፡ ስለሆነ ፡ በዚሁ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሳለሁ ፤ የተመለከትሁትን ፡ ባስታወስሁት ፡ ቁጥር ፡ ራሴን ፡ እንዳውቀው ፡ ያደርገኛል ።

በቀድሞ ፡ ጊዜ ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ የሚያድጉት ፡ በዛሬው ፡ ጊዜ ፡ በትምህርት ፡ ገበታ ፡ እንደሚሳተፉትና፡ እጩ፡ መኰንኖች፡ እንደ፡ ሚባሉት ፡ ለከፍተኛ ፡ ኃላፊነት ፡ ሹመት ፡ የሚታጩት ፡ ነበሩ ፤ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ ተራ ፡ ገብተው ፡ ሲሠሩ ፡ አነጋገራቸውና ፡ አካሄዳቸው ፤ ትጋታቸውና ፡ ብልህነታቸው ፤ ትዕግሥተኛና ፡ ቻይነታቸው ፤ ጀግንነታቸው ፡ ወይም ፡ ፈሪነታቸውና ፡ ምሥጢር ፡ ቻይነታቸው ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ የሚያስከብርም ፡ ሆነ ፡ የሚያዋርድ ፡ ጠባያቸው ፡ ሁሉ ፡ ዕለት ፡ በዕለት ፡ ይመረመራል ፤ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ፈተናውን ፡ ያለፉና ፡ የበለቁት ፡ እየተመረጡ ፡ ለአገረ ፡ ገዥነት ፤ ለጦር ፡ አለቅነት ፤ ለሕዝብ ፡ አስተዳዳሪነት ፤ ለዳኝነትና ፡ ለሚኒስትርነት ፤ ሲመረጡ ፡ ችሎታቸው ፡ ሳይፈቅድላቸው ፡ የቀሩት ፡ በዚያው ፡ በተራ ፡ ሠራተኛነት ፡ ይቀጥላሉ ፡ ወይም ፡ ይወገዳሉ ፤ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እያገለገሉ ፡ ያደጉት ፡ በሹመት ፡ ወደ ፡ ታዘዙበት ፡ በተላኩ ፡ ጊዜ ፤ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ሕግጋትና ፡ ሥርዓት ፡ ስለሚያውቁት ፡ በሚፈጽሙት ፡ ሥራ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ አስመስግነው ፡ እነሱም ፡ ተመስግነውና ፡ ተወደው ፡ ለመኖር ፡ ይችሉ ፡ ነበር ፤ በቅርብ ፡ በማደጋቸውም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ምኞትና ፡ ፍላጎት ፡ የሚያውቁ ፡ ይሆናሉ ።

እንደዚሁም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የያንዳንዳቸውን ፡ ጥያና ፡ አገልግሎት ፡ እንደሚያውቁላቸው ፡ ስለሚያምኑ ፡ በገኘሩና ፡ በተግገር ፤ ባሊቃና ፡ በጭፍራ ፡ መሐከል ፡ የሐሳብ ፡ አንድነትና ፡ የሥራ ፡ ኅብረት ፡ ነበር ፤ «ተመልከት ፡ ዓላማህን ፡ ተከተል ፡ አለቃህን ፡» የሚባለው ፡ የማዘዝንና ፡ የመታዘዝን ፡ ምሥጢር ፡ የያዘው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ያሸናፊነት ፡ ምልክት ፡ ነበር ።

በቤተ ፡ መንግሥት ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ ከተሰማራሁ ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ በጠቅላላው ፡ ባለው ፡ አስተዳደር ፡ ያየሁትንና ፡ ያጠናሁትን ፡ እንደ ፡ ትምህርት ፡ የሆነኝን ፡ ለነበር ፡ ይጠቅማል ፡ በማለት ፡ ይህችን ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ልጽፍ ፡ ስጀምር ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ምሥጢር ፡ ለመግለጽ ፡ በማሰብ ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን በጊዜው ፡ ላይ ፡ የተጠበቀ ፡ ምስጢር ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጊዜው ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ታሪክ ፡ መሆን ፡ ስለሚኖርበት ፤ እኔም ፡ ይህንኑ ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ የመንግሥቱን ፡ ጥንካሬና ፡ በየዘመኑ ፡ አጋጥሞት፡ የነበረውን፡ ትግል ፡ ለማስረዳት ፡ ያህል ፡ ነው ።

አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ተወግደው ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ እንዲነግሡ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ እንዲሆኑ ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ከያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ተባራሪ ፡ ጽሑፎች ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲደርሰው፡ በማድረግ ፡ በየአደባባዩና ፡ በየገበያው ፡ ላይ ፡ ይሰራጭና ፡ ይበተን ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከተጻፉት ፡ ቃላቶች ፡ ወ ስዋ ፡ ትገ ፡ የሚሉኝ ፡ ሕዝቡ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ ጠልቶ ፡ ለውጥ ፡ ያደረገበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጠውን ፡ ጽሑፍ ፡ ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ጠቅሼዋለሁ ፤

የገባር ፡ ልጅ ፡ እንኳን ፡ አባቱ ፡ ሲሞት ፡
የደረሰው ፡ እንደሁ ፡ ከአስር ፡ አንድ ፡ መሬት ፡
ተሥካሩን ፡ ያወጣል ፡ እስከ ፡ አስር ፡ ዓመት ፡
ምኒልክ ፡ ለኢያሱ ፡ ቢያወርሰው ፡ መንግሥት ፡
ሳያበቃው ፡ ቀረ ፡ ለአንድ ፡ ቀን ፡ ፍታት ፡
ይግረማችሁ ፡ ብሎ ፡ በሞቱ ፡ ማግሥት ፡
እጃንሜዳ ፡ ወጣ ፡ ፈረስ ፡ ጉግሥ ፡ ሊጫወት ።
የምኒልክ ፡ መንግሥት ፡ አምሮ ፡ ተደላድላ ፡
ብታንገላታትም ፡ ብትላትም ፡ ችላ ፡
እስካሁን ፡ ጠበቀች ፡ ነፍስ ፡ ብታውቅ ፡ ብላ ፡
አሁን ፡ ሃይማኖት ፡ ብትለውጥ ፡ የሌላ ፡
ለዘውዲቱ ፡ ሄደች ፡ ዘውዲቱ ፡ ኰብላ ፡
ከሆን ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪ ፡ ለኋላ ፡
ጠቅል ፡ እንላለን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ አላ ።
መቻል ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ የምኒልክ ፡ ሎሌ ፡
አልሰማም ፡ የማይል ፡ አለ ፡ ባለሚሌ ፡
ቀለብ ፡ ደመወዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ያደረገኝ ፡ ሎሌ ።
ይህንን ፡ የጻፍሁት ፡ እኔ ፡ ዘውዴ ፡ ኃይሌ ።





ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ።



ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

## ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ በዙፋን ፡ ስለመቀመጣቸው ። በዘመናቸው ፡ ስለተፈጸሙት ፡ አዳዲስ ፡ ሥራዎች ።

በንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የተሠሩትን ፡ ሥራዎች ፡ በሙሉ ፡ አጠናቆ ፡ ለመጻፍ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባልችል ፡ ለኔ ፡ የተገለጸልኝንና ፡ የማውቀውን ፡ ከረዥሙ ፡ ባጭሩ ፡ ብጽፍና ፡ ባስረዳ ፡ የንግሥቲቱን ፡ ደንበኛ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ የሚጽፈውን ፡ ብዙውን ፡ ታሪክ፡ አያጐድለውም ፡ በማለት ፡ ሐሳቤን ፡ እጀምራለሁ ።

ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክና ፡ ከወረይሉ ፡ ባላባት ፡ ልጅ ፡ ከወይዘሮ ፡ አብቺው ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፴፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እነዋሪ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ተወለዱ ። ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ ወይዘሮ ፡ ሸዋረጋንና ፡ ልጅ ፡ አስፋ ፡ ወሰንን ፡ ወልደው ፡ ስለነበረ ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ፫ኛ ፡ ልጃቸው ፡ ናቸው ። እነዚያም ፡ ገና ፡ በፊት ፡ በሞት ፡ ስለተለዩ ፡ በሕይወት ፡ የቀሩ ፡ ልጃቸው ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ብቻ ፡ ነበሩ ።

ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፵፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ለአጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ልጅ ፡ ለራስ ፡ አርአያ ፡ ዮሐንስ ፡ ተድረው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ሄዱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የ፯ ፡ ዓመት ፡ ተመንፈቅ ፡ ልጅ ፡ ስለነበሩ ፡ የጋብቻው ፡ ጉዳይ ፡ ለሁለቱ ፡ ነገሥታት ፡ የፍቅር ፡ መገናኛ ፡ ምልክት ፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ የተደረገ ፡ ነበር ።

በ፲፰፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ራስ ፡ አርአያ ፡ ዮሐንስ ፡ ታመው ስለሞቱ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ክረምቱን ፡ እዚያው ፡ ትግሬ ፡ ላይ ፡ ከረሙና ፡ በ፲፰፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኅዳር ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ተመለሱ ።

በ፲፰፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ደጃዝማች ፡ ውቤ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድን ፡ አግብተው ፡ ነበር ። ከጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላም ፡ ከእርሳቸው ፡ ተፋተው ፡ በ፲፰፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ደጃዝማች ፡ ጉግሣ ፡ ወሌን ፡ ፩ (በኋላ ፡ ራስ ፡ የተባሉትን) ፡ አገቡ ።

---

፩ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ ቀድሞ ፡ የቤጌምድርና ፡ የስሜን ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ የነበሩ ፡ የእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ብጡል ፡ ወንድም ፡ የራስ ፡ ወሌ ፡ ብጡል ፡ ልጅ ፡ ናቸው ።

ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በ፲፱፻፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ታመው ፡ አቤት ፡ ከዋሉ ፡ በኋላ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ (በኋላ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት) አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ አባታቸውን ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ እያስታመሙ ፡ ተቀመጡ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የመንግሥት ፡ ወራሽ ፡ የሆኑት ፡ የእኅታቸው ፡ የወይዘሮ ፡ ሸዋረጋ ፡ ምኒልክ ፡ ልጅ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱ ፡ ተጣልተዋቸው ፡ እቴጌይቱንም ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱንም ፡ ካዲስ ፡ አበባ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አስወጧቸው ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ በእንጦጦ ፡ ማርያም ፡ ከተማ ፡ ሲቀመጡ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱም ፡ ሙሎ ፡ ወረዳ ፡ በሚገኝ ፡ ፋሌ ፡ በሚባል ፡ ርስታቸው ፡ ላይ ፡ በግዞት ፡ ተቀመጡ ።

## በሕዝብ ፡ ምርጫ ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቷን ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ስለመውረሳቸው ።

በ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦ ፡ አቤቶ ፡ ኢያሱን ፡ ሽሮ ፡ ከመንግሥት ፡ ባስወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ተብለው ፡ የአባታቸውን ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ዙፋን ፡ እንዲወርሱ ፡ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የሐረሩ ፡ ገዢ ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ልጅ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ እንዲሆኑና ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ እንዲፈጽሙ ፡ የሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ ወሰነ ።

ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ለዚህ ፡ ከፍ ፡ ላለው ፡ ከአባት ፡ ሲያያዝ ፡ ለመጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ገዢነት ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በመላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምርጫ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ተብለው ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ ዙፋን ፡ ወረሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ ልጅ ፡ መኰንን ፡ ዋልቴን ፡ (በኋላ ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ የተባሉትንና ፡ አዛዥ ፡ ሽብሩ ፡ ደብሶን ፡ ቀኛዝማች ፡ ወርዶፋ ፡ ጨንገሬን ፡ ልኮ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱን፡ ከነበሩበት ፡ የግዞት ፡ ስፍራ ፡ ከፋሌ ፡ አስጠርቶ ፡ ባባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ አስቀመጣቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በየካቲት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በአራዳ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ (አሁን ፡ መናገሻ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በሚባለው ፡ ላይ) ፡ ሥርዐተ ፡ ንግሥ ፡ ደርሶላቸው ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ በአቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጅ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብለው ፡ ዘውድ ፡ ጫኑ ። ልዑል ፡ ራስ ፡ ተፈሪም ፡ ታላቁን ፡ የሰሎሞን ፡ ኒሻን ፡ ተሸልመው ፡ ለአልጋ ፡ ወራሽነት ፡ የሚገባው ፡ ክብርና ፡ ሥርዓት ፡ ጸሎትም ፡ ተደረገላቸው ።



በሳምንቱ ፡ የካቲት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ እሑድ ፡ ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንጉሥነት ፡ ዘውድ ፡ ሰጥተው ፡ በውስጣቸው ፡ የቤጌምድርና ፡ የስሜን ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ሾሙዋቸው ። የንግሡም ፡ ሥርዓት ፡ የተፈጸመው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ግቢ ፡ ከትልቁ ፡ አዳራሽ ፡ በስተ ፡ ደቡብ ፡ በተዘጋጀው ፡ ዳስ ፡ ውስጥ ፡ ነበር ።



ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ።

ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈሪ ፡ ሕጉን ፡ አክባሪ ፡ በጾም ፡ በጸሎት ፡ በዓለሙ ፡ ተቀምጠው ፡ በተባህትዎ ፡ እንደሚኖሩት ፡ መናንያኖች ፡ ዓይነት ፡ የሚኖሩ ፡ ቸርና ፡ እርኅርኅት ፡ ነበሩ ፤ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ስለመውረሳቸውም ፡ ከዚያ ፡ በፊት ፡ በጉዳዩ ፡ ከአንድም ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ እንኳ ፡ ያልተነጋገሩበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ያላንዳች ፡ ፖለቲካና ፡ ያለወገን ፡ ትግል ፡ የተሰየሙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምርጥ ፡ ሹም ፡ ናቸው ። በዘመናቸውም ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክን ፡ መታሰቢያ ፡ ቤትና ፡ ሌሎችንም ፡ ብዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ አሠርተዋል ፤ ዝርዝሩ ፡ ወደፊት ፡ በሚገኘው ፡ መስመር ፡ ተገልጿል ።

ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ከ፯ ፡ ወር ፡ በኢትዮጵያ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ተቀምጠው ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በመጋቢት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በድንገት ፡ ታመው ፡ ዐረፉ ።

ሥርዓተ ፡ ቀብራቸውም ፡ በነገሥታት ፡ ማዕረግ ፡ በታላቅ ፡ ክብርና ፡ በሰልፍ ፡ ሆኖ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የአባታቸው ፡ አጽም ፡ ባለበት ፡ በታዕካ ፡ ነገሥት ፡ በአታ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተፈጸመ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ዙፋኑ ፡ አሁን ፡ ላሉት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተላለፈ።

## በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የተፈጸሙ ፡ ሥራዎች ።

የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ብዙ ፡ አዳዲስና ፡ ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፡ የተፈጸሙበት ፡ ነው ። ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የበላይ ፡ ገዢነት ፡ ሲመረጡ ፤ ስለ ፡ ሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ የዛሬውን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ አድርጎ ፡ ባንድነት ፡ ሕዝቡ ፡ መርጧቸው ፡ ስለነበረ ፡ ንግሥቲቱ ፡ በሐዘንና ፡ በጸሎት ፡ አልጋ ፡ ወራሹና ፡ እንደራሴው ፡ በዕውቀት ፡ ተባብረው ፡ የፈጸሟቸው ፡ ሥራዎች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ገልጦ ፡ ለማስረዳት ፡ እሞክራለሁ ።

### (ሀ) አዳዲስ ፡ ሥራዎች ፤

፩ኛ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ የነበሩትን ፡ የዛሬውን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ በ፲፱፻፲፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡



ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ከመሳፍንትና ፡ ከመኳንንት ፡ ጋር ፡ አውሮፓን ፡ ሲጐበኙ ።



በመላክ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ ያገናኘና ፡ ያስተዋወቀ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ።

፪ኛ፤ ኢትዮጵያ፡ከዓለም፡ማኅበር፡አንድነት፡እንድትገባ፡ያደረገው፡ እንደዚሁ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ።

፫ኛ፤ የሀገሪቱ ፡ ተወላጅ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጳጳስ ፡ እንዲሆን ፡ የተደረገው ፡ በዚሁ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሲሆን ፤ ደግሞም ፡ በበለጠ ፡ የግብፁ ፡ ፓትሪያርክ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ተወላጅ ፡ ጳጳስ ፡ አድርገው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሾመውና ፡ ባርከው ፡ ተመልሰዋል ። ይህንም ፡ ያደረገው ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ።



ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ከእስክንድርያው ፡ ፓትርያርክ ፡ ከብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ዮሐንስ ፡ ጋር ።


### (ለ) ታላላቅ ፡ ሥራዎች ፤

፩ኛ፤ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ እንደነገሡ ፡ የነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ደንብ ፡ ነውና ፡ በጊዜው ፡ የነበረው ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ፡ መልክና ፡ ስም ፡ የታተመው ፡ ገንዘብ ፡ ቀርቶ ፡ ወደፊት ፡ በግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ መልክና ፡ ስም ፡ ገንዘብ ፡ እየታተመ ፡ እንዲሠራበት ፡ አስፈ

ላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ የሚታተምበት ፡ ቅርጽ ፡ በብር ፤ በአላድ ፤ በሩብ ፤ በመሐለቅ ፤ ተዘጋጅቷልና ፡ እንዲፈቀድ ፡ ብሎ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትራቸው ፡ ቢጠይቋቸው ፡ እኔን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መርጦ ፡ ያነገሠኝ ፡ እኔ ፡ ምንም ፡ የዋልኩለት ፡ ውለታ ፡ ሳይኖር ፡ የአባቴን ፡ ውለታ ፡ አስቦ ፡ ስለሆነ ፡ እኔም ፡ በበኩሌ ፡ የአባቴ ፡ ስም ፡ የሚጠራበትን ፡ ማሰብ ፡ ስላለብኝ ፡ በአባቴ ፡ ስም ፡ የታተመው ፡ ገንዘብ ፡ ተሠርዞ ፡ በእኔ ፡ ስም ፡ የታተመ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲተካ ፡ አልፈቅድምና ፡ በዚያ ፡ ይቀጥል ፤ በኔ ፡ ስም ፡ ገንዘብ ፡ ሊታተም ፡ የተሰናዳው ፡ የመታሰቢያ ፡ ስጦታ ፡ ብቻ ፡ ይታተምበት ፡ ብለው ፡ ስለመለሱለት ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ስም ፡ የሚታተመው ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀጥል ፡ ሆኗል ፡፡

፲፫፡ አሁን ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ መታሰቢያ ፡ ሆስፒታል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ለሴቶች ፡ ማዋለጃ ፡ እንዲሆን ፡ ያሠሩት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ናቸው ፡፡

፲፬፡ አባታቸው ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ እንዳረፉ ፡ ሞታቸው ፡ ተደብቆ ፡ አጽማቸው ፡ ባንድ ፡ ትንሽ ፡ የጸሎት ፡ ቤታቸው ፡ ውስጥ ፡ አርፎ ፡ ቆይቶ ፡ ነበር ፡፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ተብሎ ፡ የተሰየመው ፡



የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡፡
ቀስቱ ፡ የሚያሳየው ፡ አጽማቸው ፡ አርፎበት ፡ የነበረበትን ፡ ቤት ፡ ነው ፡፡



የበኢታ ፡ ገዳም ፡ በ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተመሥርቶ ፡ በ፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተፈጸመ ፡፡ ለድርጅቱም ፡ ሙሉ ፡ መተዳደሪያ ፡ ሰጥተውና ፡ ሥርዓት ፡ ሠርተውለት ፡ አጽማቸው ፡ እንዲያርፍበትና ፡ እንዲቀደስበት ፡ አደርገዋል ፡፡



ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በመታሰቢያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዓል ፡ ሲያከብሩ ፡፡


፲፭፡ በዓለም ፡ ለታወቁ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታት ፡ ስለውለታቸው ፡ ሐውልት ፡ የሚቆምላቸው ፡ መሆኑን ፡ ተመልክተው ፡ አባታቸው ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የደከሙላትና ፡ መሥዋዕት ፡ የሆኑላት ፡ የሥልጣኔ ፡ በር ፡ የከፈቱላት ፡ መሆናቸውን ፡ ተገንዝበውና ፡ ሐውልት ፡ እንዲቆምላቸው ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ አስበው ፤ ይህ ፡ አሁን ፡ በቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አቅራቢያ ፡ የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ አደባባይ ፡ ተብሎ ፡ በተሰየመው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የቆመውን ፡ ሐውልት ፡ ሙሴ ፡ ቤርትል ፡ በተባለ ፡ የጀርመን ፡ መሐንዲስ ፡ አስጠንተው ፡ ሐውልቱ ፡ ከጀ



የዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሐውልት ።

ርመን ፡ አገር ፡ ተሠርቶ ፡ እንዲመጣ ፡ አዘዙ ። ሐውልቱም ፡ መጥቶ ፡ ቦታው ፡ ተመድቦና ፡ ባካባቢው ፡ የነበረው ፡ ተነሥቶ ፡ በመደልደል ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ሐውልቱ ፡ ሳይቆም ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ድን ገት ፡ ስለአረፉ ፤ ሐሳባቸውን ፡ ከመጀመሪያው ፡ የሚያውቁት ፡ አልጋ ፡ ወራሻቸው ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ በዓል ፡ ተደርጎ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሁሉ ፡ በሰልፍ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሐውልቱ ፡ እንዲቆም ፡ ተደረገ ።





ንምረ ፡ ተፈሪ ።

፫ኛ፤ በ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አይሮፕላን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ መግሥት ፡ ነው ።

## (ሐ) የአሠሩዋቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ኛ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ እስከዛሬም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤት ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ ከ፯ ፡ በላይ ፡ ክፍል ፡ ያለውን ፡ ትልቅ ፡ ፎቅ ፡ ቤት ፡ አሠርተው ፡ ከኪራዩ ፡ ገቢ ፡ እሩቡ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ መናንያን ፡ መርጃ ፡ እንዲሆን ፤ የቀረው ፡ ለአስፈላጊው ፡ ለመንግሥት ፡ ጉዳይ ፡ እንዲውል ፡ አድርገዋል ፤

፪ኛ፤ የእንጦጦ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ ቀድሞ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የተሠራው ፡ በጭቃ ፡ ግንብ ፡ ስለነበረ ፡ አርጅቶ ፡ የሚፈርስ ፡ ስለሆነ ፡ ንግሥተ ፡ ነገ ሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ አሁን ፡ የሚገኘውን ፡ ሕንፃ ፡ አሠሩ ፤

፫ኛ፤ የአቃቂ ፡ ቀራንዮ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ትክሉ ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ነው ። ዳግማዊ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ያሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አርጅቶ ፡ የሚፈርስ ፡ ስለሆነ ፡ ፈርሶ ፡ አሁን ፡ የሚገኘውን ፡ ሕንፃ ፡ አሠሩ ፤

፬ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ጽርሐ ፡ አርያም ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ዳግማዊ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ በጭቃ ፡ ግንብና ፡ በሣር ፡ ክዳን ፡ ያሠሩት ፡ ስላረጀ ፡ ፈርሶ ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ ሕንፃ ፡ አሠሩ ፤

፭ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ደብረ ፡ አሚን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አሠሩ ፤

፮ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ደብረ ፡ ጽጌ ፡ ዑራኤል ፡ ትክሉ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ስለአረጀ ፡ ፈርሶ ፡ አሁን ፡ ያለውን ፡ ሕንፃ ፡ አሠሩ

፯ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ደብረ ፡ ሰላም ፡ እስጢፋኖስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ የተተከለ ፡ ነው ፤ የመጀመሪያውንም ፡ አለቃ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዛቸውን ፡ መልአከ ፡ ሰላም ፡ ወልደ ፡ መስቀልን ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ አሰኝተውና ፡ ሙሉ ፡ መተዳደሪያ ፡ ሰጥተው ፡ ሕንፃውንም ፡ አሠርተው ፡ በታላቅ ፡ ሰልፍ ፡ ታቦት ፡ እንዲገባ ፡ አደረጉ ።

ምንክያቱም ፡ የሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ እየተባለ ፡ የሚጠራው ፡ ድል ፡ የተገኘበት ፡ ቀን ፡ ጥቅምት ፡ ፲፯/፲፱፻፲፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የጥቅምት ፡ እስጢፋኖስ ፡ ዕለት ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፤

፰ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፱ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ደብረ ፡ ነገሥት ፡ ቁስቋምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲ኛ፤ የመናገሻ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፩ኛ፤ የፋሌ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፪ኛ፤ ሚታ ፡ የወረብ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፫ኛ፤ የአዋሽ ፡ ማርያምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፬ኛ፤ የኢጀርሳ ፡ ለፎ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤልን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፭ኛ፤ የየረር ፡ ሥላሴን ፡ (አድአ) ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፮ኛ፤ የአዲስ ፡ አበባ ፡ የቅዱስ ፡ ዮሴፍን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፯ኛ፤ የአድአ ፡ በርጋ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤

፲፰ኛ፤ ጠራ ፡ የደብረ ፡ በግዕ ፡ አቡነ ፡ ሕጻን ፡ ሞአን ፡ ገዳም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠሩ ፤ ይህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ልጅ ፡ የሆኑት ፡ የአጼ ፡ ምኒልክ ፡ አባት ፡ የንጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ መቃብር ፡ ያለበት ፡ ስለሆነ ፡ ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ከሚባሉበት ፡ ጊዜ ፡





መልአከ ፡ ሰላም ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡ ዘውዲቱ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ።
ደብረ ፡ ሰላም ፡ እስጢፋኖስን ፡ በመጀመሪያ ፡ የተሾሙት ።

ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እስፈላጊ ፡ የሆነው ፡ ድግስ ፡ እየተሰናዳ ፡ ሳይታጎል ፡ በየዓመቱ ፡ በፍትሐት ፡ የን ጉሥ ፡ ኃይለ ፡ መለኮት ፡ ስም ፡ ሲጠራበት ፡ ቆይቶ ፡ ነበር ፤

፲፱ኛ ፤ በግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ስለትምህርት ፡ የተነገረ ፤

ልጅ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ልጁን ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ የሆነ ፡ ትምህርት ፡ እንዲያስተምር ፡ የሚያስገድድ ፡ ዐዋጅ ።

ልጅ ፡ ያለው ፡ ልጁ ፡ ክፉንና ፡ በጐን ፡ የሚለይበትን ፡ ንጉሡንና ፡ ፈጣሪውን ፡ የሚፈራበት ፡ ዕውቀትን ፡ ለማግኘት ፤ የንባብና ፡ የጽሕፈት ፡ ትምህርት ፡ ያላስተማረ ፡ መቀጫውን ፡ ፶-፶ ፡ ብር ፡ እየከፈለ ፤ የመቀ ጫው ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እየገባ ፡ ለነዳያን ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ይሆናል ።

የንስሐ ፡ አባትም ፡ የሆንክ ፡ ቄስ ፡ ሁሉ ፡ የንስሐ ፡ ልጆችህ ፡ ልጆ ቻቸውን ፡ አስተምሩ ፡ ብለህ ፡ ከመከርክ ፡ በኋላ ፡ ምክርህን ፡ የማይቀ በሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ግን ፡ ዐዋጅ ፡ አፍራሾች ፡ መሆናቸውን ፡ ላገሩ ፡ ሹም ፡ አስታውቅ ።

የገጠር ፡ መሪ ፡ ጌታም ፡ የሆንክ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ከሌላው ፡ ግብርህ ፡ ጋራ ፡ ቀላቅለህ ፡ የሰበካውን ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ የንባብና ፡ የጽ ሕፈት ፡ ትምህርት ፡ አስተምር ።

የደብርም ፡ አለቃ ፡ የሆንክ ፡ ሰው ፡ ፈጣሪውን ፡ ዐውቆ ፡ የሚጠቅ ምበትን ፤ በደብርህ ፡ መንፈሳዊ ፡ ዕውቀት ፡ ለምእመናን ፡ በሚገባው ፡ ልክ ፡ የሰብከት ፡ ትምህርት ፡ በየደብርህ ፡ አስተምር ።

ሳታስተምር ፡ የቀረህ ፡ እንደሆን ፡ ግን ፡ በሹመትህ ፡ ትቀጣለህ ። ደግሞ ፡ ልጅ ፡ ያለህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ልጅህ ፡ የንባብና ፡ የጽሕፈት ፡ ትም ህርት ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡ ለሕይወቱና ፡ ለኑሮው ፡ የሚያሻውን ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ እንዳይቸገር ፤ ባገራችን ፡ ካለው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ልብህ ፡ የሚወደውን ፤ አንዳንድ ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ እንዲማር ፡ አድርግ ፡ ለትዳሩ ፡ የሚሆን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ሳታስተምረው ፡ የቀረህ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በአካል ፡ ጉዳይ ፡ ካለ ፡ ግማሽ ፡ ወደ ፡ ድሆች ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ የሚገባ ፡ መቀጫ ፡ ፶-፶ ፡ ብር ፡ ትከፍላለህ ፤ ይኸንንም ፡ የተቆረጠውን ፡ ትምህ



ርት ፡ ይማር ፡ የተባለው ፡ ልጅ ፡ ዕድሜው ፡ ከ፯ ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ፳፩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ነውና ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ላለው ፤ የትምህርት ፡ ዕድሜ ፡ በተላለፈው ፡ ልጁ ፡ አባቱ ፡ አላስተማርህም ፡ ተብሎ ፡ አይቀ ጣም ።

ጥቅምት ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡

ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የላይኛውና ፡ የታችኛው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ ነው ፤ እንደዚሁም ፡ ፡ የፊታውራሪ ፡ ሃብቴ ፡ ጊዮር ጊስና ፡ የአልጋ ፡ ወራሽ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ በመባባል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መለያየት ፡ በየጊዜው ፡ ይደረግ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ ንግሥቲቱ ፡ ሰላምና ፡ ፀጥታን ፡ ፈላጊ ፡ በመሆናቸው ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ በማብረድ ፡ በማስማማትና ፡ በታላቅ ፡ ትዕግሥት ፡ በመቻል ፡ ሊቀጣጠል ፡ የሚነሳውን ፡ የነገር ፡ እሳትና ፡ ሽብር ፡ ያበርዱት ፡ እንደነበረ ፡ ለማንም ፡ የተሠወረ ፡ አልነበረም ። ሆኖም ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ መሰናክል ፡ እየፈጠረ ፡ የሚናገር ፡ የዕለት ፡ እንጀራ ፡ ፈላጊ ፡ ሁሉ ፡ አስመስሎ ፡ መናገርን ፡ እንደትልቅ ፡ ትምህርት ፡ አድርጎ ፡ ይዞ ፡ ከወ ዲያ ፡ ወዲህ ፡ ነገር ፡ በማመላለስና ፡ በማዋሰብ ፡ በየጊዜው ፡ ብጥብጥ ፡ እየፈጠረ ፡ በመሐከሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ይገጥማቸው ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ ንግሥ ቲቱ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትዕግሥት ፡ ስለያዙት ፡ አንድም ፡ ነገር ፡ መሠረቱን ፡ ለቆ ፡ ሳይፋለስ ፡ እየበረደና ፡ እየተስማማ ፡ ወደ ፡ ታሰበበት ፡ ግብ ፡ ይደ ርስ ፡ ነበር ።

በየጊዜው ፡ ከተደረጉት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነበሩ ፡ ከምላቸው ፡ ነገሮች ፡ ለማስረጃ ፡ ያህል ፡ ሚኒስትሮችን ፡ ለማስወጣት ፡ የተደረገውን ፡ የመጀ መሪያ ፡ የሕዝብ ፡ አድማና ፡ እንደዚሁም ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ለማስቸ ገር ፡ ሞክረው ፡ የነበረውን ፡ በሚከተሉት ፡ ምዕራፎች ፡ ለማስረዳት ፡ እሞክራለሁ ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### (ሀ) በቶራ ፡ መስክና ፡ በሰገሌ ፡ በደሴና ፡ በመቅደላ ፡ በሌላም ፡ ስፍራ ፡ ውጊያ ፡ ስለመደረጉ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መስከረም ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ከመንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ ሽሮ ፡ ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱን ፡ በአባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ባስቀመጠበት ፡ ጊዜ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አደባባይ ፡ አዋጁ ፡ ሲነገር ፡ ቀላል ፡ ተኩስ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ በባዘኑ ፡ ጥይት ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ካራትና ፡ ካምስት ፡ የማይበልጥ ፡ ነበር ። በዘመኑም ፡ ከነበሩት ፡ መኳንንቶች ፡ ደጃዝማች ፡ አብርሃም ፡ አርኣያ ፡ እልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ግቢ ፡ ገብተው ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ መሻርና ፡ የንግሥቲቱን ፡ በዙፋን ፡ መቀመጥ ፡ በመቃወም ፡ ለማስቸገር ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የማያዋጣቸው ፡ መሆኑን ፡ አውቀው ፡ ወዲያው ፡ እጃቸውን ፡ ሰጡ ።


ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ከዙፋን ፡ መውረድ ፡ አባታቸው ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ እንደሰሙ ፡ የወሎን ፡ ሠራዊት ፡ አስከትተው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ጉዞ ፡ መጀመራቸው ፡ እንደ ፡ ተሰማ ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ እንዲጠባበቅ ፡ በራስ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡ የበላይ ፡ አዝማችነት ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አበበ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፤ ደጃዝማች ፡ ተሰማ ፡ ገዝሙ ፤ ፊታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ ጎበና ፤ ፊታውራሪ ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡ (በኋላ ፡ ቢትወደድ) ፡ አቶ ፡ ሸዋዬ ፡ አሳላፊ ፡ አቤ ፡ ሠራዊታቸውን ፡ አስከትለው ፡ ዘመቱ ። በጥቅምት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፩ ቶራ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ጦርነት ፡ የተጠቀሱት ፡ ሁሉ ፡ በታላቅ ፡ ጀግንነት ፡ በውጊያ ፡ ሲሞቱ ፡ ፊታውራሪ ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡ ብቻ ፡ ተርፈው ፡ ተመለሱ ።

እንደዚሁም ፡ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ጦር ፡ ከሐረርጌ ፡ በአዋሽ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ጉዞ ፡ መጀመሩ ፡ ስለተሰማ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ለማ ፤ ደጃዝማች ፡ መኩሪያ ፡ ገርማሜ ፤ ደጃዝማች ፤ አድማሱ ፡ ብሩ ፤ ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩ ፤ ግራዝማች ፡ አበበ ፡ዳምጠው ፤ ልጅ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፤ ፊታውራሪ ፡ ተክለሐዋርያት ፡ አገሩን ፡ ስለሚያውቁት ፡ ለዚሁ ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ ተዋግተዋል ።

---

፩ ራስ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡ አባ ፡ በላይ ፡ የተዋጉበት ፡ «ቶራ ፡ መስክ» ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ ከደብረ ፡ ብርሃንና ፡ አንኮበር ፡ መሐከል ፡ የሚገኝ ፡ አገር ፡ ነው ።






ንጉሥ ፡ ሚካኤል ።

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰገሌ ፡ ላይ ፡ ከንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ ዋናው ፡ ጦርነት ፡ ተደረገና ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ተማረኩ ።

ከመንግሥት ፡ በኩል ፡ ለዘመቱት ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ጠቅላይ ፡ አዛዥ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ሲሆኑ ፤ ከእርሳቸውም ፡ በታች ፡ የነበሩት ፡ ዋናዎቹ ፡ አዝማቾች ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሃብተ ፡ ጊዮርጊስና ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉ ፡ ነበሩ ። በዚህም ፡ ጦርነት ፡ ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እንዳለቀ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከመንግሥት ፡ ጦር ፡ በኩል ፡ ከሞቱት ፡ ትልልቆች ፡ ሰዎች ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፤ ፊታውራሪ ፡ ወልደሚካኤል ፡ አዴችና ፡ ግራዝማች ፡ ድልነሴ ፤ ደጃዝማች ፡ ተፈራ ፡ ገሠገሡ ፡ ልጅ ፡ አባሚልኪ ፡ ገሠገሡ ፡ ነበሩ ።

ከሰገሌ ፡ ውጊያ ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ በየሥፍራው ፡ ውጊያ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ፤

፩ኛ፤ ከሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ገና ፡ ሐረር ፡ ሳሉ ፡ በደጃዝማች ፡ ጉግሣ ፡ አልዩ ፡ የሚመራ ፡ ጦር ፡ ከሐረር ፡ ወደ ፡ አዋሽ ፡ እንዲሄድ ፡ ታዞ ፡ ዘምቶ ፡ ነበር ። ይህም ፡ ወሬ ፡ ስለተሰማ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ጦር ፡ ታዞ ፡ ወርዶ ፡ ገና ፡ አዋሽ ፡ ሳይደርስ ፡ ሚኤሶ ፡ ላይ ፡ ገጥሞ ፡



ልዑል ፡ አሊጋ ፡ ወራሽ ፡ ከመኳንንቶች ፡ ጋር ።

ከቀኝ ፡ ወደግራ ፡ በወንበር ፡ የተቀመጡ ፡ ልዑል ፡ አሊጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፤ እና ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ናቸው ።


ከግራ ፡ ወደቀኝ ፡ የቆሙ ፡ በጅሮንድ ፡ ግዛለ ፡ ድንግል ፤ ደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ሚካኤል ፤ አባ ፡ ግዛው ፤ ደጃዝማች ፡ ወልዴ ፡ ጻድቅ ፤ ልጅ ፡ ሺበሺ ፡ ጅማ ፡ (አባሐና ፡ ጅማ) ፤ ልጅ ፡ መንገሻ ፡ ወሰኔ ፡ (ደጃዝማች) ፤ ነጋድራስ ፡ ገና ፤ ባሻ ፡ በላይ ፡ (ጋሻጃግሬው) ፤ ከንቲባ ፡ ወሰኔ ።

ድል ፡ አደረገውና ፡ በደጃዝማች ፡ ጉግሣ ፡ አዝማችነት ፡ የመጣው ፡ ጦር ፡ ተበተነ ። ከዚህ ፡ ድል ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሐረርጌን ፡ ለቀው ፡ በረሃውን ፡ አቋርጠው ፡ በይፋት ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ ተጓዙ ። ሐሳባቸውም ፡ ወሎ ፡ ላይ ፡ ከአባታቸው ፡ ለመቀላቀል ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ የልጃቸውን ፡ ሽረት ፡ ወዲያው ፡ እንደሰሙ ፡ የወሎን ፡ ጦር ፡ አስከትተው ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ በግሥጋሴ ፡ ዘምተው ፡ ሰገሌ ፡ ፩ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ነበር ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ ገና ፡ በመንገድ ፡ ሳሉ ፡ ስለሰሙ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ሄዱ ።

፩ ሰገሌ፤ የሚባለው ፡ አገር ፡ ከደብረ ፡ ብርሃን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በሚያመጣው ፡ መንገድ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ብርሃን ፡ ፹፯ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ አገር ፡ ነው ።



፪ኛ፤ ከሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ በንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ የታዘዘውና ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ሆኖ ፡ የመጣውን ፡ ጦር ፡ ለማገድ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ በራስ ፡ ሉልሰገድ ፡ የሚመራ ፡ ቀዳሚ ፡ ጦር ፡ ተልኮ ፡ ነበር ። ጥቅምት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቶራ ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ተዋግተው ፡ የንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ አዝማቾች ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።



ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ።

፫ኛ፤ ባህያ ፡ ፊጅ ፡ በኩል ፡ በራስ ፡ ጉብረ ፡ሕይወት ፡ ሚካኤል ፡ አዝማችነት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲመጣ ፡ የታዘዘውን ፡ የንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ጦር ፤ ከሰገሌ ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡ የጅሩንና ፡ የጃማን ፤ የመርሐ ፡ ቤቴንና ፡ የሚዳን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ወረኢሉ ፡ ላይ ፡ ተጋጥመው ፡ ድል ፡ አደረጉት ፤ ራስ ፡ ጉብረ ፡ ሕይወትም ፡ ተማረኩ ።



ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ።



ራስ ፡ አባተ ፡ ቧያለው ።
ገጽ ፡ ፶ ፡ ተመልከት ፡

፬ኛ፤ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ እንደገና ፡ ጦር ፡ ሠርተው ፡ መቅደላ ፡ ከአምባቸው ፡ ገብተው ፡ ሳለ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ፡ ጊዮርጊስ፡ ዋና፡ አዝማች ፡ ሆነው፤ ራስ ፡ደምሰው፡ ነሲቡን፤





ራስ ፡ ደምሰው ፡ ነሲቡ ።



ራስ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ገብርኤል ።



ደጃዝማች ፡ ወሰኔ ፡ ትርፌ ።



ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡

ደጃዝማች ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤልን ፤ ደጃዝማች ፡ ወሰኔ ፡ ትርፌን ፤ ደጃዝማች ፡ ወልደጻድቅን ፤ ከነጦራቸው ፡ አስከትለው ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ተጓዙ ። ደሴ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ከሰገሌ ፡ ድል ፡



በኋላ ፡ የወሎ ፡ አገረ ፡ ገገር ፡ ሆነው ፡ የተሾሙት ፡ ራስ ፡ አባተ ፡ ቧያለው ፡ አብረው ፡ እንዲዘምቱ ፡ ተደርጎ ፡ መቅደላን ፤ አምባውን ፡ ከበው ፡ ተዋ ግተው ፡ በ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነሐሴ ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ መቅደ ላን ፡ አስለቀቋቸው ። ልጅ ፡ ኢያሱም ፡ ወደ ፡ አውሳ ፡ በረሃ ፡ ገብተው ፡ ተደበቁ ። ራስ ፡ አባተ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላም ፡ የወሎ ፡ ግዛት ፡ ለራስ ፡ ከበደ ፡



ራስ ፡ ከበደ ፡ መንገሻ ።

መንገሻ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ። ራስ ፡ ከበደም ፡ የወሎን ፡ ጦር ፡ አስከትተው ፡ ወደ ፡ አውሳ ፡ ዘመቱ ። የሐረርጌም ፡ ጦር ፡ በደጃዝማች ፡ አባሻውል ፡ እግር ፡ ታዞ ፡ አብሮ ፡ ዘምቶ ፡ ነበር ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የአውሳን ፡ በረሃ ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ግዛት ፡ ተሻግረው ፡ በመዘ

ዋወር ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ በ፲፱፻፲፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በራስ ፡ ጉግሳ ፡ አርአያ ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ተያዙ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ የልጅ ፡ ኢያሱን ፡ እህት ፡ አግብተው ፡ ስለነበረ ፡ ራስ ፡ ጉግሳን ፡ ወግተው ፡ ልጅ ፡



ራስ ፡ ጉግሳ ፡ አርአያ ።

ኢያሱን ፡ ሊነጥቁ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለተወራ ፡ ለጊዜው ፡ ወደ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ አርአያ ፡ ዘንድ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ ተልከው ፡ ሄዱ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስንና ፡ ከጎጃም ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ አስከትለው ፡ ወደ ፡ ትግሬ ፡ ዘመቻ ፡ ተጉዘው ፡ ደሴ ፡ ላይ ፡



ሲደርሱ ፡ ራስ ፡ ጉግሳ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ የጁ ፡ ላይ ፡ ከሸዋ ፡ ለተላከው ፡ ጦር ፡ ስላስረከቡ ፡ ዘመቻው ፡ ደሴ ፡ ድረስ ፡ ሆኖ ፡ ከደሴ ፡ ጦሩ ፡ ወደየሀገሩ ፡ እንዲመለስ ፡ ተደረገ ። ልጅ ፡ ኢያሱንም ፡ የተረከቡት ፡ ደጃዝማች ፡ ወሰኔ ፡ ትርፌ ፡ ፩ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ወ/ሚካኤል ፡ ፪ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደጃዝማች ፡ አባ ፡ ሻውል ፡ ደጃዝማች ፡ ዋቄ ፡ ነበሩ ። እንዲታሠሩ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረውም ፡ ኩላሽ ፡ በተባለው ፡ አምባ ፡ ስለነበረ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ በዚህ ፡ ሥፍራ ፡ አልታሠርም ፡ በማለት ፡ ቅርታቸውን ፡ ስለገለጡ ፡ መኳንንቶቹ ፡ ለንግሥትና ፡ ልአልጋ ፡ ወራሽ ፡ አመልክተው ፡ ኩረማሽ ፡ እንዲታሠሩ ፡ ተደረገ ። አልጋ ፡ ወራሽም ፡ ከደሴ ፡ ሲመለሱ ፡ ኩረማሽ ፡ ደርሰው ፡ ቦታውን ፡ አይተው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።



ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ።

---

፩ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ተረክቡ ፡ ከተባሉት ፡ ውስጥ ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ ወንድም ፡ ናቸው ።

፪ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ የእናታቸው ፡ ልጅ ፡ ወንድም ፡ ናቸው ።

ደጃዝማች ፡ ወሰኔ ፡ ትርፌ ፡ ገጽ ፡ ፶፱ ፡ ይመልከቱ ።



ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሥላሴ ።



ደጃዝማች ፡ አባቫውል ።



በላይኛው ፡ መስመር ፡ ላይ ፡ የዘመቻውን ፡ ቦታ ፡ ስጠቅስ ፡ ዘማቾቹን ፡ አልገለጥሁም ፡ ነበርና ፡ አሁን ፡ በሚቀጥለው ፡ መስመር ፡ እገልጸለሁ ።

፩ ፡ በቶራ ፡ መስክ ፡ አዝማች ፡ የነበሩት ፡

ራስ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡ ዋና ፡ አዝማች ፡

ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አበበ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡

ደጃዝማች ፡ ተሰማ ፡ ገዝሙ ፡

ፊታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ ኀበና ፡

ፊታውራሪ ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡ (በኋላ ፡ ቢትወደድ) ፡

አሳላፊ ፡ አቤ ፡

አሳላፊ ፡ ድልነሴ ፡



ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አበበ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ።



ደጃዝማች ፡ ተሰማ ፡ ገዝሙ ።

፪ በሚኤሶ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ዘምተው ፡ የነበሩ ፡—

ደጃዝማች ፡ ኃይሌ ፡ ማርያም ፡ ለማ ፡

ደጃዝማች ፡ መኰሪያ ፡ ገርማሜ ፡

ደጃዝማች ፡ አድማሱ ፡ ብሩ ፡


ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩ ፡

ግራዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡ (በኋላ ፡ ደጃዝማች) ፡

ልጅ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ (በኋላ ፡ ራስ) ፡



ፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ ኅበና ።



ፊታውራሪ ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ።

ፊታውራሪ ፡ ተክለሐዋርያትም ፡ (እርሳቸውም ፡ አገሩን ፡ ስለሚያውቁት ፡ ለዚህ ፡ ጦር ፡ መሪ ፡ የሆኑት ፡ ናቸው ። (በኋላ ፡ በጅሮንድ) ፡

## (ለ) ሚኒስትሮችን ፡ ከሥራ ፡ ስለማስለቀቅ ፡

ይህ ፡ ውጊያ ፡ በሆነ ፡ በ፪ኛው ፡ ወር ፡ የመሐል ፡ ሠፋሪ ፡ ፩ አድማ ፡ ተፈጠረ ። ምክንያቱም ፡ ሚኒስትሮችን ፡ ከሥራ ፡ ለማስለቀቅ ፡ ነበር ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ የዚህ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ እኔ ፡ ገና ፡ የ፲፯ ፡ እና ፡ የ፲፰ ፡ ዕድሜ ፡ ልጅ ፡ ስለነበርኩ ፡ ጉዳዩ ፡ የሚአገባኝ ፡ ሳይሆን ፡ ወሬ ፡ ለማየት ፡ ስል ፡ በስብሰባው ፡ አደባባይ ፡ ተገኝቼ ፡ ነበርና ፡ ጠቅላላውን ፡ የአድማ ፡ መንስኤ ፡ ምንም ፡ ባላውቀው ፡ በመጠኑ ፡ ያዳመጥኩትን ፡ ያህል ፡ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ለመጻፍ ፡ አሰብሁ ። ለአድማውም ፡ ምክንያት ፡ የሆነው ፡ ሚኒስት

መሐል ፡ ሠፋሪ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ጦር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሚቀመጡበት ፡ ከተማ ፡ ክየደምቡ ፡ እየተወጣጣ ፡ በወር ፡ ተራ ፡ እየገባ ፡ በቅርብ ፡ የሚገኘው ፡ ጦር ፡ ነው ፡ ይኸው ፡ ጦር ፡ ደምቡ ፤

- ፩ ፡ ወናድር ፡ ያዥ ፡
- ፪ ፡ ጠመንጃ ፡ ያዥ ፡
- ፫ ፡ ፈረስ ፡ ዘበኛ ፡
- ፬ ፡ ማለፊያ ፡ ጠመንጃ ፡ ያዥ ፡
- ፭ ፡ የባለሟል ፡ ደምብ ፡ የጨዋልጅ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡
- ፮ ፡ የውሐ ፡ ስንቁ ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራ ፡ በሊጋባው ፡ የሚታዘዝ ፡
- ፯ ፡ የግቢ ፡ ሚኒስቴርን ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴርን ፡ ባልደረባ ፡ እታ ፡ ቤትን ፡ ይቀስቅሳል ።



ሮች ፡ የየራሳቸውን ፡ የግል ፡ ጥቅም ፡ እንጂ ፡ ለአገርና ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ አልሠሩምና ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ይሻሩ ፡ በማለት ፡ ነበር ።

በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የነበሩት ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣናቸው ፡ ከፍ ፡ ያለና ፡ በሹም ፡ ሽርም ፡ ጉዳይ ፡ ይመክሩ ፡ ነበርና ፡ የብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ጌቶችም ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ከሥልጣን ፡ የመሻሩ ፡ ጉዳይ ፡ አስጊ ፡ መስሎ ፡ ታይቶ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ያድማው ፡ አነሳስ ፡ ከመጋቢት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ በየጊዜው ፡ እያደገ ፡ ስለሄደ ፡ የሕዝቡ ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ማሸነፉ ፡ አዘነበለና ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥራ ፡ ለቀው ፡ እንዲወጡ ፡ የማስገደዱ ፡ ሁናቴ ፡ እየተቃረበ ፡ ይሄድ ፡ ጀመር ። ከስብሰባው ፡ ውስጥ ፡ በአንደኛው ፡ ዕለት ፡ ሕዝቡ ፡ ተሰብስቦ ፡ በሚዶልትበት ፡ ጊዜ ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያስፈርድ ፡ አጋፋሪ ፡ ተሾመ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በተራ ፡ እያስነሳ ፡ ሲያስፈርድ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ የተናገረው ፡ የፍርድ ፡ ትችት ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ትዝ ፡ ስለሚለኝ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ መስመር ፡ ጽፌዋለሁ ።

ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ጌታችን ፡ እግዚእን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ፈጥሮ ፡ ፲፪ ፡ ሐዋርያትን ፡ አገር ፡ ከፍሎ ፡ እንዲያስተምሩ ፡ ያስማራቸውን ፡ ለመምሰል ፡ ላገሩና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ልማት ፡ በእውነት ፡ እንዲመክሩና ፡ እንዲሠሩ ፡ ፲፪ቱን ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ደጉ ፡ ጌታችን ፡ አጤ ፡ ምኒልክ ፡ መርጠው ፡ ቢሾሟቸው ፡ ለአገር ፡ ልማት ፡ ለሕዝብ ፡ አንድነት ፡ በመምከር ፡ ፈንታ ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ ለየራሳቸው ፡ ጥቅም ፡ በመመልከት ፡ አገሩን ፡ አበላሹት ፡ እንጂ ፡ ለመንግሥት ፡ የጠቀሙትና ፡ የሠሩለት ፡ ጉዳይ ፡ የለም ።

፲፪ቱን ፡ ሐዋርያት ፡ በማየት ፡ የተሾሙት ፡ ሚኒስትሮች ፡ ፲፪ት ፡ አጋንንት ፡ ስለሆኑ ፡ እንዲሻሩ ፡ ያስፈልጋል ፤ ለምሳሌ ፡ የሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተብሎ ፡ የተሾመው ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ በቤት ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ እየቀጠለ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ለመውጣት ፡ ይገሰግሳል ። እንደዚሁም ፡ የግቢ ፡ ሚኒስትር ፡ የተባለው ፡ የራሱን ፡ ሀብት ፡ ብቻ ፡ በማደራጀቱ ፡ ከምኒልክ ፡ ቤት ፡ ለግብር ፡ የሚሆን ፡ መሰናዶ ፡ ታጥቶ ፡ ባለፈው ፡ ሰሞን ፡ ከእርሱ ፡ ቤት ፡ ዱቄት ፡ ተግዞ ፡ ተሰናዳ ። ይህ ፡ ምን ፡ ያሳያል ፡ ሁሉም ፡ የየራሱን ፡ ጥቅም ፡ ለማደራጀት ፡ መዘጋጀቱን ፡ ነው ፤ እያለ ፡ ሲያስረዳ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ሚዳቋ ፡ ከምን ፡ ቦታ ፡ እንደመጣች ፡ ሳይታወቅ ፤ የሚዶልተው ፡ ሕዝብ ፡ በተሰበሰበበት ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ብቅ ፡ አለች ። የየመኳንንቱም ፡ አሽከሮች ፡ ስለ ፡ ተጯጯሁና ፡ ስለ ፡ ተራወጡ ፡ ሚዳቋዋ ፡ መሄጃ ፡ አጣችና ፡ በሕዝቡ ፡ መሐከል ፡ ገብታ ፡ አቋርጣ ፡ ስትሄድ ፡ አንዱ ፡ ፈጣን ፡ ወታደር ፡ ተከታትሎ ፡ ሚዳውን ፡ ጨርሳ ፡ ካሁን ፡ በላ ፡ ልትሄድ ፡ ስትል ፡ የኋላ ፡ እግሯን ፡ ይዞ ፡ አመጣትና ፡ በተሰበሰበው ፡

ሕዝብ ፡ መሐከል ፡ አረዳት ። እዚያ ፡ ያለውም ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ አጩኼ በጩበና ፡ አምልጣን ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የላካት ፡ ያ ፡ ተማሪ ፡ ስለሆነ ፡ ነገራችን ፡ ይበላሽ ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ይዘን ፡ ስለአረድናት ፡ ነገራችን ፡ ቀናን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አለና ፡ እንደገና ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ አጨብጭበው ፡ ያን ፡ ሚዳቋ ፡ የታየችበትን ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አቅራቢያ ፡ የሚገኘውን ፡ ሜዳ ፡ ለቀቀና ፡ ወደ ፡ ጃንሜዳ ፡ ወጥቶ ፡ ስብሰባው ፡ ቀጠለ ። ያድማውም ፡ ሁናቴ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ሄደ ። በቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ተመከረና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱና ፡ እጨጌው ፡ ከሊጋባው ፡ ጋራ ፡ እየሆኑ ፡ በሕዝቡና ፡ በመንግሥቱ ፡ መሐከል ፡ መላላክ ፡ ጀመሩ ። የመጨረሻውም ፡ ውሳኔ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ተሽረው ፡ እንዲወጡ ፡ ሲሆን ፡ ጃንሜዳ ፡ ላይ ፡ ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ እጨጌው ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሊጋባ ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ እድማው ፡ ላይ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የሚገኘውን ፡ ጽሑፍ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተልኮ ፡ ተነበበለትና ፡ ተነገረው ።

## ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ የተላከው ፡ ቃል ።

## የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡

በአንድነት ፡ ሆናችሁ ፡ በአባታችን ፡ እጅ ፡ የላካችሁት ፡ ቃል ፡ ደርሶናል ። የንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስን ፡ መሞት ፡ የሰማነው ፡ ከትላንት ፡ ወዲያ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ለእናንተ ፡ የሚያሳዝናችሁ ፡ አይደለምን ? ሁለተኛስ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱን ፡ ያህል ፡ እናታችሁን ፡ ተዝካራቸው ፡ በሚወጣበት ፡ ቀን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ተጓድሎ ፡ ቢውልና ፡ ድግሱ ፡ ቢበላሽ ፡ ሐዘኑና ፡ ጉዳቱ ፡ መልሶ ፡ ለእናንተ ፡ አይደለምን ? የላካችሁልኝን ፡ ቃል ፡ ለንግሥት ፡ አስታውቃለሁ ። ከጥንትም ፡ ቢሆን ፡ የሚኒስትሮችን ፡ ሹመት ፡ ዳግ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አፄ ፡ ምኒልክ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ጥቅምና ፡ እድገት ፡ የሚሆነውን ፡ ለማስጠበቅና ፡ ለማሠራት ፡ ሲሉ ፡ አቅደውት ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሕዝብን ፡ ለመጉዳት ፡ በማሰብ ፡ እንዳልነበር ፡ ታውቂታላችሁና ፡ አሁን ፡ አሳቡን ፡ ከራሳችሁ ፡ አውርዳችሁ ፡ እኛ ፡ እንድናስብበት ፡ ካደረጋችሁ ፡ ለመላው ፡ ሕዝብ ፡ ደስ ፡ የሚለውንና ፡ ለመንግሥቱ ፡ ብልጽግናና ፡ ጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ ለስኞ ፡ ጠዋት ፡ እስክናስታውቃችሁ ፡ ድረስ ፡ በንግግርም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ረገድ ፡ ቢሆን ፡ ሽብር ፡ እንዳይነሳ ፡ አደራ ፡ ተጥሎባችኋል ።

ከሁላችሁም ፡ ወገን ፡ ሁከትና ፡ ሽብር ፡ እንዲነሳ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጠላትነቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ስለሆነ ፡ እኛም ፡ በበኩላችን ፡ ከነሱ ፡ ወገን ፡ ሁከት ፡ እንዳይነሳ ፡ እናደርጋለን ፤ የሚል ፡ ቃል ፡ ባድማው ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ተነበበለት ። የተሰበሰበውም ፡ ሕዝብ ፡ በበኩሉ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ በጽሑፍ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ላከ ።



## የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ ሆይ ፡

እኛ ፡ ባሮችዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በንግሥታችን ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱና ፡ በርስዎ ፡ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሻችን ፡ በኩል ፡ ተበድለናልና ፡ ተጎድተናል ፡ የምንለው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሕዝቤን ፡ ይጠብቁልኛል ፡ የጀመርሁትንም ፡ የሥራ ፡ ውጥን ፡ ይፈጽሙልኛል ፡ ብለውና ፡ አስበው ፡ የሾሟቸው ፡ ሚኒስትሮች ፡ እንደገና ፡ ተሿሚዎቹ ፡ ብሰው ፡ ሕዝብን ፡ መበቀን ፡ አገራችንን ፡ ማጥፋት ፡ አገሪቱን ፡ ከነገንዘቧ ፡ ለየራሳቸው ፡ መከፋፈልና ፡ እውቀትን ፡ ማጥፋት ፡ ትምህርትንም ፡ መድፈን ፡ የጨዋን ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ከጥንት ፡ ከአባቱ ፡ ማዕረግ ፡ ማውረድ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ለመንግሥት ፡ የረዱትና ፡ የጠቀሙት ፡ ነገር ፡ የለም ።

ስለዚህ ፡ ከመበደልና ፡ ከመከፋት ፡ ከውርደትና ፡ ከመበሳጨት ፡ ደኅው ፡ ከመዘረፋና ፡ መንግሥቱም ፡ ጥቅሙን ፡ አጥቶ ፡ ጉዳት ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ለንግሥታችንና ፡ ለአልጋ ፡ ወራሹ ፡ እናመለክታለን ፤ እርስዎም ፡ ይህን ፡ ለንግሥታችንና ፡ ለርስዎ ፡ የጻፍነውን ፡ ቃል ፡ አይተው ፡ የቸርነትዎን ፡ መልስ ፡ እንድናገኝ ፡ የታመነ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ፲፱ ፡ ሚኒስትሮች ፡ እስካሁን ፡ ያጠፉትን ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ስለሀገርዎ ፡ አስበው ፡ እንዲያሻሽሉትና ፡ የተደላደለ ፡ እንዲያደርጉት ፡ ትክክለኛ ፡ እውቀትና ፡ ግምት ፡ እንዳለዎ ፡ እናውቃለን ።

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ እነዚሁ ፡ ሚኒስትሮች ፡ መሰናከል ፡ ቢሆኑብዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንግሥት ፡ በአባታቸው ፡ ዙፋን ፡ ከተቀመጡበትና ፡ እርስዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ጠቃሚ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩልን ፡ ነበር ። አሁንም ፡ እርስዎና ፡ ንግሥታችን ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩን ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስን ፡ ጨምረው ፡ ያስተዳድሩን ፡ እንጂ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለነዚህ ፡ ሚኒስትሮች ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳይሰጡብን ፡ እንለምንዎታለን ።

በንግሥታችንና ፡ በእርስዎ ፡ በአልጋ ፡ ወራሻችን ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሀገራችን ፡ ክፉ ፡ የሚመክሩ ፡ ሰዎችና ፡ የሚያስቡዎ ፡ ቢኖሩ ፡ ከፊትዎ ፡ የምንሞትና ፡ ደማችንን ፡ በመጀመሪያ ፡ የምናፈስ ፡ እኛ ፡ ባሮችዎ ፡ ነን ፤ ይህም ፡ ጥርጥር ፡ እንደሌለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ይመስክርብናል ። እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተፈሪን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ቢዛ ፡ የሰጠን ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

## ለሕዝቡ ፡ የመንግሥቱ ፡ ሁለተኛ ፡ መልስ ፡
## የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡

እናንተ ፡ በአንድነት ፡ ሆናችሁ ፡ ለላካችሁልኝ ፡ መልእክት ፤ መልስን ፡ ለሰኞ ፡ አስታውቃችኋለሁ ፡ ብያችሁ ፡ ነበር ። አሁንም ፡ አባቶቼና ፡ ወንድሞቼ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሁላችን ፡ በአንድነት ፡ ሆነን ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ላይ ፡ የተነሳነው ፡ የእስላም ፡ ሴት ፡ በማግባታቸውና ፡ በመስለማቸው ፡ ይህን ፡ ሕዝቡና ፡ እኛም ፡ እርግጠኛነቱን ፡ ስላየነው ፡ በእውነት ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማቆምና ፡ ሕዝቡን ፡ ከጥፋት ፡ ለማዳን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለራሳችን ፡ ጥቅም ፡ ብለን ፡ አይደለም ። ለዚህም ፡ ምስክርና ፡ አስረጅ ፡ ይሆነን ፡ ዘንድ ፡ ያን ፡ ጊዜውኑ ፡ አባታችንና ፡ እጨጌው ፡ ፊታውራሪ ፡ ሃብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ የምኒልክ ፡ ልጅ ፡ ትንግሥ ፡ አንተ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሆነህ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ በአንተ ፡ ይሠራ ፡ ቢሉኝ ፡ ሲሆን ፡ የአባቴን ፡ እርስት ፡ እያረስኩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከሚመጣባት ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ሳልለይ ፡ ልቀመጥ ፡ ያለዚያ ፡ አይሆንም ፡ ካላችሁኝ ፡ ሐረርጌን ፡ ይገፄ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ እረዳለሁ ፡ ብዬ ፡ ገባሁ ። መላው ፡ ሕዝብ ፡ ተባብሮና ፡ አንድነት ፡ ሆናችሁ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አደረጋችሁኝ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ አውቃለሁ ፡ አደላድለዋለሁ ፡ ብዬ ፡ አልገባሁም ።

ይህም ፡ በተደረገ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ሚካኤል ፡ ሊወጉን ፡ ቢመጡ ፡ አሽከሮቼ ፡ ይምጡና ፡ ይከተሉኝ ፡ ያባቴም ፡ ጦር ፡ ያብርልኝ ፡ ሳልል ፡ ይህን ፡ አስባችሁ ፡ ካደረጋችሁልኝ ፡ ጋራ ፡ አብሬ ፡ ዘምቼ ፡ ገባሁ ። አሁን ከእናቴ ፡ ከእመቤቴ ፡ ጋራ ፡ አብሬ ፡ ሆኜ ፡ የምረዳችሁና ፡ የማግዛችሁ ፡ ከሆንና ፡ አገሬስ ፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ የምትድን ፡ ከሆን ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ ለኔ ፡ አይደለምን ? ነገር ፡ ግን ፡ አንድነት ፡ የሕዝቡ ፡ መሰብሰብ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሚያጎድል ፡ ይመስላችኋል ፤ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ምክንያት ፡ መስኮብን ፡ ያህል ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ ያለውና ፡ በሰው ፡ ብዛትም ፡ ሆነ ፡ በሀገር ፡ ስፋትም ፡ ቢሆን ፡ ከአውሮፓ ፡ መንግሥታት ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጠው ፡ በአሥር ፡ ዓመት ፡ የማይደፈር ፡ ከተማውን ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ጠላቶች ፡ ገቡበት ። ስዋቸው ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተላለቀ ፡ አሁንም ፡ እናንተ ፡ ሚኒስቴሮችን ፡ ይሻሩልን ፡ ማለታችሁ ፡ የተሾሙት ፡ ሰዎች ፡ ይሻሩልን ፡ ብላችሁ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ የተነሳችሁት ፡ የበደላችሁ ፡ ሥራው ፡ አይደለም ።

አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ሥራቸው ፡ እየበዛ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ እየበረከተ ፡ መንግሥቱ ፡ እየሰፋ ፡ ሲሄድ ፡ የአውሮፓ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ መካርም ፡ የለው ፡ ሥራም ፡ አይሠራ ፡ እያሉ ፡ አገራቸውን ፡ ለመከፋፈል ፡ የሚፈልጉት ፡ ቢሆን ፡ አገሬም ፡ በዓለም ፡ካሉት ፡ ነገሥታት ፡ ትክክል ፡ ሆና ፡ ትጠራ ፡ ብለው ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሾመው ፡ ለየነገሥታቱ ፡ ሁሉ ፡ ወኪሎች ፡ መሾማቸውን ፡ አስታወቁ ። ሥራቸው ፡ ይጉደል ፡ እንጂ ፡ ሚኒስትሮች ፡ በመሾማቸው ፡ በዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ተመሰገኑ ፤ በዓለም ፡ ያሉ ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ ከሚኒስትሮች ፡ ሌላ ፡ መካር ፡ የሚያስፈልግ ፡ መሆኑን ፡ መርምረው ፡ ከየሀገሩ ፡ ሽማግሌ ፡ ፫፻ ፡ እና ፡ ፭፻ ፡ የሚሆን ፡ የአገር ፡ ጪዋ ፡ መርጠው ፡ ይሾማሉ ። ሠራተኛና ፡ አማካሪ ፡ ከሌለው ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ እንደምን ፡ ይቆጠራል ። ይህንንም ፡ የመሰለው ፡ ሁኔታ ፡ ከጥንት ፡ ከአባቶቻችን ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ የመንግሥትና ፡ የሕዝብ ፡ ኃይል ፡ ትክክል ፡ ነው ። አሁንም ፡ ለሹም ፡ ሽሩና ፡ ለሌላውም ፡ ሥራ ፡ ቢሆን ፡ እኛም ፡ ብንጨርሰው ፡ ከእኛም ፡ በኩል ፡ መካር ፡ አግኝተን ፡ ብንጨምር ፡ አስፈላጊነቱን ፡ እየተመለከትንና ፡ እያየን ፡ ለማድረግ ፡ እንችላለን ፤ አሁን ፡ ያሉትን ፡ ሚኒስትሮች ፡ ግን ፡ ሽረንላችኋል ።

ይህንንም ፡ ቀደም ፡ ብላችሁ ፡ በዝግታ ፡ ብታስታውቁን ፡ ኖሮ ፡ እንደሚሆን ፡ አድርገን ፡ ሕዝቡም ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አድማ ፡ ሥራ ፡ ረገድ ፡ ተሰበሰበ ፡ ሳይባልና ፡ በሌላ ፡ ተመልካች ፡ ዘንድ ፡ ሳይታወቅና ፡ ሳይገለጽ ፡ እኛው ፡ አስበን ፡ እንጨርስላችሁ ፡ እንደነበር ፡ የታመነ ፡ ነው ። መጋቢት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተጻፈ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ። የሚል ፡ ቃል ፡ ተነቦ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ለተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ተነገረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሚኒስትሮች ፡ እንዲሻሩና ፡ እንዲወጡ ፡ መወሰኑን ፡ በመጥቀስ ፡ አሥረድተው ፡ ለወደፊቱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ የአድማ ፡ ሥራ ፡ እንዳይደገም ፡ ጉዳት ፡ የሚያመጣ ፡ መሆኑን ፡ በምክር ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ገቡ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ [፩] ፊታውራሪ ፡ መርዳሳ ፡ ጆቴ ፡ የተባሉት ፡ ካድመኞቹ ፡ አንዱ ፡ ካራቸውን ፡ መዘዙና ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ እየገዘትህ ፡ ማሳሰር ፡ ለምዶሀል ፡ ፍታ ፡ ሲሉ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጩኸት ፡ ተናገሩ ፡ እጨጌው ፡ ግን ፡ የካራ ውንም ፡ መመዘዝ ፡ ሆነ ፡ ለማስፈራራት ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ የተነገረውን ፡ ከምንም ፡ ጉዳይ ፡ ሳይቆጥሩ ፡ በበኩላቸው ፡ በመቆጣት ፡ ያላንዳች ፡ ፍርሃትና ፡ ሥጋት ፡ አልፈታም ፡ በማለት ፡ ተናግረው ፡ እንደገና ፡ ግዝታቸውን ፡ አጸኑ ።

---

[፩] ግዝቱን ፡ የተቃወመው ፡ ፊታውራሪ ፡ መርዳሳ ፡ ጆቴ ፡ የወለጋ ፡ ሌቃ ፡ ባላባት ፡ የደጃዝማች ፡ ጆቴ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ጳጳሱ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስ ፡ ግን ፡ ፍታ ፡ ፍታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ በማለት ፡ በመስጋትና ፡ በመጨነቅ ፡ እየደጋገሙ ፡ ባልተማራ ፡ አማርኛ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እጨጌው ፡ አልፈታም ፡ በማለት ፡ ግዝታቸውን ፡ ስላጸኑ ፡ መከታና ፡ መጠጊያ ፡ የሌለበት ፡ ወለል ፡ ያለው ፡ ጃንሜዳ ፡



ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስና ፡ እጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ።

ካራ ፡ በመምዘዝና ፡ የጠመንጃ ፡ ቃታ ፡ በማውረድ ፡ ወደ ፡ መሸበሩ ፡ ሲያዘነብል ፡ ብልሁ ፡ የምኒልክ ፡ አሽከር ፡ ፩ ሊጋባ ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ ብለዋል ፡ ባለህበት ፡ እርጋ ፡ ብለው ፡ ከጳጳሱና ፡ ከእጨጌው ፡ መሐከል ፡ ሕዝቡ ፡ ወደአለበት ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡ ፊንጠር ፡ ብለው ፡ ወጥተው ፡ ስለተናገሩ ፡ ሊነሳ ፡ የነበረው ፡ ሽብር ፡ ወደ ፡ ሰላም ፡ ተለወጠና ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

---

፩ ሽብሩን ፡ ለማብረድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታ ፡ ብለዋል ፡ ብለው ፡ ጸጥ ፡ እንዲል ፡ ያደረጉት ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ መንግሥት ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ የአደጉ ፡ ሲሆኑ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ሚኒስትር ፡ በሾሙበት ፡ ጊዜ ፡ የሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተብለው ፡ የተሾሙት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱም ፡ መንግሥቱን ፡ ለቀው ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ሲነግሡ ፡ በወረኢሉ ፡ በኩል ፡ የመጣውን ፡ በራስ ፡ ኀብረ ፡ ሕይወት ፡ የሚመራውን ፡ የንጉሥ ፡ ሚካኤልን ፡ ጦር ፡ ወግተው ፡ ድል ፡ ያደረጉና ፡ መሪውን ፡ ራስ ፡ ኀብረሕይወትን ፡ የማረኩ ፡ ከጦሩ ፡ በኋላ ፡ ሊጋባነትን ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ።

ፎቶግራፋቸውን ፡ በገጽ ፡ ፺፯ ፡ ተመልከት ።



በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ሚኒስትሮች፡ ስምና ፡ ብዛት ፡—

| | | |
|---|---|---|
| ፩ | ፊታውራሪ ፡ ሃብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ | የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፪ | ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታ ፡ | የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፫ | ደጃዝማች ፡ ወልደጻድቅ ፡ | የአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፬ | ደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ | የንግድ ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፭ | አፈንጉሥ ፡ ጥላሁን ፡ | የፍርድ ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፮ | ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ አፈወርቅ ፡ | የጽሕፈት ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፯ | አዛዥ ፡ መታፈሪያ ፡ | የግቢ ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፰ | ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ ይመር ፡ | የሥራ ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፱ | ቀኛዝማች ፡ አምዴ ፡ | የርሻ ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፲ | መላከ ፡ ፀሐይ ፡ ኢስድሮስ ፡ | የትምህርት ፡ ሚኒስትር ፡ |
| ፲፩ | የፖስታ ፡ ሚኒስቴር ፡ ተብሎ ፡ ሳይሾም ፡ በሹም ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ | |
| ፲፪ | የጤና ፡ ጥበቃ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትር ፡ ውስጥ ፡ ነበር ። | |

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስማቸው ፡ በዝርዝር ፡ ከተጻፈው ፡ ውስጥ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሃብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ ብቻ ፡ ሲቀሩ ፡ ሁሉም ፡ ከሥልጣናቸው ፡ ተሽረው ፡ ወደርስት ፡ ሀገራቸው ፡ እንዲሄዱ ፡ ተወሰነና ፡ እየታዘዙ ፡ ሄዱ ። መንግሥቱም ፡ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሚኒስትር ፡ መባልንና ፡ በማንኛውም ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እየገቡ ፡ ይመክሩ ፡ የነበረውን ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ቀንሶ ፡ አስቀረና ፡ በየሥራው ፡ ላይ ፡ ተጠርቶ ፡ ሲጠየቅ ፡ ሐሳብ ፡ የሚሰጥ ፡ እና ፡ ተወስኖ ፡ የተሰጠውን ፡ ብቻ ፡ የሚሠራ፡ ሹም ፡ የእገሌ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በማለት ፡ አዲስ ፡ የአሿሿም ፡ ሥርዓት ፡ ተጀመረና ፡ ባዲሱ ፡ ተሻሚዎች ፡ ሥራው ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ ይካሄድና ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ።

በዚህ ፡ ዓይነት ፡ አሠራር ፡ አንድና ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ከተከናወነ ፡ በኋላ ፡ ሥልጣኑ ፡ ብቻ ፡ ሲወሰን ፡ እንደወትሮው ፡ ሚኒስትር ፡ የሚባለው ፡ ሹመት ፡ ታደሰና ፡ ይሾም ፡ ጀመር ። ለምን ፡ ሚኒስትር ፡ ተብሎ ፡ ይሾማል ፡ ብሎ ፡ ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የተቃወመ ፡ የለም ፤ ይህንንም ፡ ሲመለከቱት ፡ አሠራሩንና ፡ በጊዜው ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕዝቡም ፡ ሆነ ፡ መንግሥቱ ፡ የጠላው ፡ ሚኒስትር ፡ የሚያሰኘውን ፡ የሹመት ፡ ስም ፡ አልነበረም ፡ ለማለት ፡ ተችሏል ።

# ምዕራፍ ፡ ፬ ።

## በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ላይ ፡ የተደረገ ፡ የአድማ ፡ ክስ ። አድመኞቹ ፡ በፍርድ ፡ ስለመቀጣታቸው ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ በጅሮንድ ፡ ውብሸት ፡ ኃይሌ ፡ ስማቸው ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ሆነው ፡ ባድማ ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ አቅርበው ፡ ነበር ።

፩ ፊታውራሪ ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡ (በኋላ ፡ ቢትወደድ) ፡
፪ ቀኛዝማች ፡ ደስታ ፡ ወስኔ ፡
፫ ነጋድራስ ፡ ፋላስ ፡
፬ አቶ ፡ መልሴ ፡ ማህሌ ፡
፭ አቶ ፡ ተፈራ ፡ ንጉሜ ፡
፮ አቃ ፡ ገብሩ ፡

ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስማቸው ፡ የተመለከተውና ፡ሌሎች ፡ ስማቸው ፡ ያልተጠራ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ሆነው ፡ ለየመኳንንቱ ፡ በያለበት ፡ እየዞሩ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አገራችንን ፡ ሽጦታልና ፡ እንክሰስ ፡ እያሉ ፡ አድማ ፡ ሲያሳድሙ ፡ ነገሩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ እተገለጠበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አድማ ፡ ሊነሳ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተፈርቶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ ስማቸው ፡ የተጠራው ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ያድማው ፡ ፊጣሪ ፡ ሆነው ፡ ስለተገኙ ፡ በ፲፱፻፲፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በጥቅምት ፡ ወር ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ተደረገና ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ አሉ ፡ በመባል ፡ የታሙት ፡ እንዳይነኩ ፡ ተመክሮ ፡ ለነገሩ ፡ ፊጣሪ ፡ ናቸው ፡ የተባሉት ፡ ብቻ ፡ እንዲያዙ ፡ ታዘዘና ፡ በየቤታቸው ፡ ያለምንም ፡ ችግር ፡ ተያዙ ፡

አቃ ፡ ገብሩ ፡ የተባሉት ፡ የከተማ ፡ ዘበኞች ፡ ሹም ፡ የነበሩት ፡ ግን ፡ አምልጠው ፡ በእንግሊዝ ፡ ሌጋሲዮን ፡ ገብተው ፡ ስለደወሉ ፡ ሳይያዙ ፡ ቀርተዋል ።

## አድመኞቹ ፡ በፍርድ ፡ ስለመቀጣታቸው ።

ባድማው ፡ ውስጥ ፡ አሉ ፡ ከተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረማርያም ፡ እና ፡ ፊታውራሪ ፡ ደቻሳ ፡ በወቀሳ ፡ ተመክረው ፡ ሳይያዙ ፡ ቀርተዋል ፤ በመጀመሪያ ፡ ስማቸው ፡ የተመለከተው ፡ ግን ፡ ከአቃ ፡





ገብሩ ፡ በስተቀር ፡ በአጋፋሪዎች ፡ ተፋራጅነት ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ተወሰነና ፡ ተፈረደ ። የፍርዱም ፡ ዓይነት ፡ እጃቸውን ፡ እስላም ፡ ቤት ፡ ከብታቸውን ፡ እግድ ፡ ቤት ፡ በማለት ፡ ነበር ።

በፍርዱም ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ አድማ ፡ ውስጥ ፡ አሉ ፡ ከሚባሉት ፡ ያልተያዙ ፡ አንደኛው ፡ ታምተው ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ነበሩና ፡ ተነስተው ፡ በሚፈርዱበት ፡ ጊዜ ፡ ሲተቹ ፡ ከሚፈረድባቸው ፡ ወንጀለኞች ፡ አንዱ ፡ በጅሮንድ ፡ ውብሸት ፡ ኃይሌ ፤ የነፍሱ ፡ ካለ ፡ የገባሱን ፡ አይናገሩ ፤ እኔ ፡ እኮ ፡ እዚህ ፡ የቆምኩት ፡ እንደሴት ፡ አሾክሹኬ ፡ አልቀርም ፡ ብዬ ፡ ነው ፤ ይልቅስ ፡ አርፈው ፡ ይቀመጡ ፡ ብለው ፡ በመናገራቸው ፡ ፈራጁን ፡ በነገሩ ፡ ውስጥ ፡ አሉበት ፡ በመባል ፡ ታምተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ በአደባባይ ፡ ከነበረው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ሳያስተዋውቋቸው ፡ አልቀሩም ። እንደዚሁም ፡ አንዱ ፡ ሽማግሌ ፡ መኰንን ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ በታላቅ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ አዛዥ ፡ ግዛው ፡ የሚባሉት ፡ ሲፈርዱ ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ልጠቅሰው ፡ ስለወደድሁ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ መስመር ፡ ጽፌዋለሁ ።

አውራ ፡ ዶሮ ፡ ሞያውን ፡ ሲጠጣ ፡ ቢውል ፡ ያሮጌ ፡ በሬ ፡ ሽንት ፡ ያኽል ፡ አይጠጣም ፤ አሁንም ፡ አገር ፡ ተሸጠ ፡ ብላችሁ ፡ የተነሳችሁት ፡ ሁላችሁም ፡ ልጆች ፡ በመሆናችሁ ፡ ከሽማግሌ ፡ ጋራ ፡ ባትመከሩበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሽማግሌ ፡ ጋራ ፡ መክራችሁ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ የማያዋጣ ፡ ነገር ፡ መሆኑን ፡ ይመክራችሁና ፡ ከፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ሳትደርሱ ፡ ይቀር ፡ ነበር ። በጣም ፡ የሚያሳዝነው ፡ የውቤ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡ ልጅ ፡ የኃይሌ ፡ ገብሩ ፡ ልጅ ፡ ከነፋላስ ፡ ጋራ ፡ በመምከራችሁና ፡ እፍርድ ፡ ፊት ፡ በመቆማችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሥራችሁ ፡ ከጥፋት ፡ የሚቆጠር ፡ አይደለምና ፡ አጥፊ ፡ አይደላችሁም ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ የለም ፡ አጥፊዎች ፡ ናችሁ ፡ በሚገባ ፡ ትቀጣላችሁ ፡ ሲሉ ፡ ፈረዱ ።

እንዲሁም ፡ አፈ ፡ ንጉሥ ፡ እስጢፋኖስ ፡ የሚባሉት ፡ ሽማግሌ ፡ ካድማው ፡ እንዲቀላቀሉ ፡ በፊት ፡ ስማቸው ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ አንደኛው ፡ እቤታቸው ፡ ሄዶ ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ በራህሌ ፡ የሚባለውን ፡ በጨው ፡ ቀረጥ ፡ በብዙ ፡ ገቢ ፡ ለመንግሥት ፡ የሚረዳውን ፡ አገራችንን ፡ ሸጠውታልና ፡ እንድንከስ ፡ ብለው ፡ ነገሩዋቸውና ፡ ባድማው ፡ እንዲተባበሩዋቸው ፡ ቢያማክሩዋቸው ፡ አገሩን ፡ የሚሸጡ ፡ ምን ፡ ሊገዙ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አይለቱባቸውና ፡ ባድማው ፡ አለመግባታቸውን ፡ ገልጠው ፡ መለሷቸው ፡

ይባላል ፤ ምን ፡ ሊገዙ ፡ የተባለውም ፡ ትርጉም ፡ ላገሩ ፡ የሚያስብ ፡ በኋላ ፡ የሚነግሠው ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁም ፤ አገሩን ፡ ሸጦ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ይነግሣል ፡ ለማለት ፡ የተናገሩት ፡ ነው ፤ ሆኖም ፡ ያዳቆነ ፡ ሰይጣን ፡ ሳያቀስ ፡ አይለቅም ፡ እንደሚባለው ፡ ተረት ፡ ሁሉ ፡ ከፍርድ ፡ እንዲያመልጡ ፡ አላደራጋቸውምና ፡ ተፈርዶባቸው ፡ እጃቸው ፡ ታሰረ ፡ ከብታቸውም ፡ ተወረሰ ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።


## ወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ ወርቅና ፡ መሐመድ ፡ አባሻንቆ ፡ ስለመያዛቸው ።

ወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ ወርቅ ፡ ዳርጌ ፡ በትውልድ ፡ እኅትነታቸው ፡ ለንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱና ፡ ለአልጋ ፡ ወራሻቸው ፡ ለልዑል ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ ለልጅ ፡ ኢያሱም ፡ እኩል ፡ ሲሆን ፡ ፍቅራቸው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ያዘነበለ ፡ ነበር ።

አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ቅጥር ፡ ግቢ ፡ ወደሚገኘው ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሄዱ ፡ ለማስገደል ፡ አስበው ፡ መሐመድ ፡ አባ ፡ ሻንቆ ፡ ከሚባለው ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ ፡ አሽከር ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረው ፡ ደግሞም ፡ በዚሁ ፡ የሚተባበሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሳብረው ፡ ሲዶልቱ ፡ ተገኝተው ፡ ነሐሴ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተያዙና ፡ መስከረም ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ተደረገ ። ሲፈረድባቸውም ፡ በአደባባዩ ፡ የነበረው ፡ ፈራጅ ፡ ሁሉ ፡ በተባበረ ፡ ድምፅ ፡ በሞት ፡ እንዲቀጡ ፡ ሲፈርድ ፡ አንዳንዱም ፡ እንደንዴቱና ፡ እንደ ፡ ብስጭቱ ፡ መጠን ፡ ለፍርዱ ፡ ማለት ፤ ላገዳደሉ ፡ መልክ ፡ እየሰጠ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ። ለሚፈርደውም ፡ ፍርድ ፡ መልክ ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ፡ ያልኩት ፡ ግማሹ ፡ በመስቀል ፡ እንዲቀጡ ፡ ሲል ፡ ግማሹ ፡ ባውራ ፡ ጎዳና ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ አንገታቸው ፡ ተቀብረው ፡ ካንገታቸው ፡ በላይ ፡ ሳይቀበሩ ፡ እስከ ፡ ሕይወታቸው ፡ እንዳሉ ፡ ወገን ፡ (ከብት) ፡ ይነዳባቸው ፡ እያለ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ፤ ከፈራጆች ፡ ግራዝማች ፡ ይገዙ ፡ ድባቤ ፡ የሚባለው ፡ በመናደድና ፡ በመበሳጨት ፡ ሲፈርድ ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ እኛን ፡ ያስፈርዱናል ፡ እንጂ ፡ አይቀጧቸውም ፤ የተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቢቀጡ ፡ ኖሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥፋት ፡ ባልተደረገም ፡ ነበር ። የምሕረት ፡ ብዛት ፡ ጥፋተኛን ፡ ያበረክተዋል ፡ እንጂ ፡ አይቀንሰውም ።

ስለዚህ ፡ ለነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ርኅራኄና ፡ ምሕረት ፡ ሊደረግላቸው ፡ አይገባምና ፡ ሁሉም ፡ በሞት ፡ ይቀጡ ፤ የማሩዋቸው ፡ እንደሆነ ፡ ነፍስዎን ፡ አይማራት ፡ ብሎ ፡ ደሙ ፡ ፈልቶ ፡ እየተበሳጨ ፡ ፈረደ ። እንደዚሁ ፡ ከፈራጆቹ ፡ አንደኛው ፡ ግራዝማች ፡ ግዛው ፡ ሥራዊቱ ፡ ሲፈርዱ ፡ ከአድመኞቹ ፡ መሐከል ፡ አንደኛውን ፡ በጅሮንድ ፡ ውብሸት ፡ ኃይሌን ፡ የሥራ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩትን ፡ ስም ፡ ጠርተው ፡ አንተ ፡ ውብሸት ፡ ባድማ ፡

ሥራ ፡ ላይ ፡ ስትገኝ ፡ ሁለተኛህ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ አሁን ፡ ያመለጥህ ፡ መስሎህ ፡ ሰምቼ ፡ እስካጣራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቆየሁት ፡ ባድማው ፡ ውስጥ፡ የለሁም ፡ ትላለህ ፤ ለማጣራትስ ፡ ቢሆን ፡ እንዲጠነቀቁበት ፡ ነግሮ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሊገደሉ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ ለማጣራት ፡ ስል ፡ ነው ፡ የቆየሁት፡ የምትለው ፡ የማይመስል ፡ ነው ። ትንሹን ፡ ነገር ፡ ምስማር ፡ አለቀ ፡ እያልክ ፡ እጆሯቸው ፡ ልጥፍ ፡ ከምትል ፡ ይጠንቀቁ ፡ ብለህ ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ ትድን ፡ ነበር ። ያቀረብከው ፡ ምክንያት ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ አያድንህምና ፡ ሁላችሁም ፡ አንድነት ፡ በሞት ፡ ትቀጣላችሁ ፡ ሲሉ ፡ ተችተው ፡ ፈረዱ ። እንዚህም ፡ ወንጀለኞች ፡ እንደ ፡ ፍርዱ ፡ በሞት ፡ ሳይቀጡ ፡ ሁሉም ፡ በመወረስና ፡ በእሥራት ፡ ብቻ ፡ ተቀጡ ።



ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በአጤ ፡ መስቀል ፡ በዓል ፡ ላይ ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ በተፈረደ ፡ በማግሥቱ ፡ የአጤ ፡ መስቀል ፡ በዓል ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የምሬቱ ፡ ተራ ፡ የገነተ ፡ ጽጌ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደብር ፡ ነበርና ፡ ዲያቆኑ ፡ በዘመኑ ፡ የተነሳውን ፡ሕውከት ፡ በመጥቀስ ፤

«ውእቱ ፡ አሚረ ፡ ይጠፍዕ ፡ ዙሉ ፡ ምክሮሙ ፤

ብጹዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘአምላከ ፡ ያዕቆብ ፡ ረዳኢሁ ፤

ወትውክልቱኒ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ።» ፡ የሚለውን ፡ ምስባክ ፡ ሰበከ ፡ (መዝሙር ፡ ፻፵፭) ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

## ስለደጃዝማች ፡ በየነ ፡ (ሊጋባው) ፡

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ለቀው ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ እንዲነግሡ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ተፈሪም ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ እንዲሆኑ ፡ በተመከረበትና ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ሊጋባ ፡ የነበሩት ፡ ምክሩም ፡ ሲመከርና ፡ ውሳኔውም ፡ በአዋጅ ፡ ተነግሮ ፡ ሲፀና ፡ የእስላም ፡ ሎሌ ፡ የሆንክ ፡ ለይ ፡ ብለው ፡ ጎራዴያቸውን ፡ መዘው ፡ አዋጁን ፡ ያፀኑት ፡ ሊጋባ ፡ የኋላም ፡ የወላሞ ፡ ገገር ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ በወላሞ ፡ ሕዝብ ፡ በአስተዳደር ፡ በደሉን ፡ በማለት ፡ ክፍ ፡ ባለ ፡ ጥፋት ፡ ተወንጅለው ፡ ተከሰው ፡ ነበር ። አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ችሎት ፡ ቀርበው ፡ በተከሰሱበት ፡ ወንጀል ፡ ተረትተው ፡ እጃቸው ፡ ተይዞ ፡ እንኮበር ፡ ታስረው ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቆዩ ፡ በኋላም ፡ ምሕረት ፡ ተደርጎላቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲገቡ ፡ ተፈቅዶ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ አዲስ ፡ ጥፋት ፡ ሲሠሩና ፡ አድማ ፡ ሲያድሙ ፤ ሹብር ፡ ለማስነሳት ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ሲላላኩና ፡ ሲዶልቱ ፡ ስለተሰማባቸው ፡ እንዲያዙ ፡ ተደርጎ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ችሎት ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በተገኙበት ፡ እንዲቀርቡ ፡ ሆኖ ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ያድማው ፡ ዓይነት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ አኳኋን ፡ መሆኑ ፡ በአደባባዩ ፡ ላይ ፡ በግልጽ ፡ ተነገረ ። ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ። ራስ ፡ ተፈሪ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ እንደራሴ ፡ አይደሉም ፤ አልጋ ፡ ወራሹም ፡ ፊንታውን ፡ ይጠብቃል ፡ እንጂ ፡ በመንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ አይችልምና ፡ ባስተዳደሩ ፡ ሥራ ፡ የገቡት ፡ ያለሕግ ፡ ስለሆነ ፡ በአልጋ ፡ ወራሽነታቸው ፡ መብት ፡ ብቻ ፡ እንዲቆዩ ፡ ሆኖ ፡ ከሌላው ፡ ሥራ ፡ እንዲታገዱ ፡ የሚል ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ በመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ከሥልጣን ፡ ሲወገዱና ፡ ንግሥት ፡ ሲነግሡ ፡ እመውረቱ ፡ ላይ ፡ አልጋ ፡ ወራሽና ፡ እንደራሴ ፡ ሆነው ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥራ ፡ እንዲመሩ ፡ መወሰኑን ፡ በጽሑፍና ፡ በጊዜውም ፡ ላይ ፡ ከነበሩት ፡ መኳንንት ፡ ከነፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነበር ። የደጃዝማች ፡ በየነም ፡ አነሳስ ፡ ፀጥታውን ፡ ለማደፍረስ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ በአደባባዩ ፡ ላይ ፡ የተገኘው ፡ መኳንንትና ፡ መሳፍንት ፡ ተገነዘበው ። ይኸውም ፡ ነገር ፡ ሚያዝያ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፲፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ረቡዕ ፡ በፍርድ ፡ እንዲወሰን ፡ ተደረገና ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ክፍ ፡

ያለ ፡ ቅጣት ፡ እንዲፈጸምባቸው ፡ ተደረገና ፡ በግርፋት ፡ እንዲቀጡ ፡ ተወሰነ ። ይኸውም ፡ ፍርድ ፡ ሲወሰን ፡ ለማሸበር ፡ የተዘጋጀት ፡ ደጃዝማች ፡ ከአደባባዩ ፡ ላይ ፡ ቢነቻው ፡ ዘራፍ ፡ በማለት ፡ ፎከሩ ። ይህም ፡ ፉከራ ፡ በግርፋት ፡ እንዲቀጡ ፡ የተፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ ምሕረትን ፡ እንዳይመለከት ፡ ስላደረገው ፡ የግርፋት ፡ ፍርድ ፡ ተፈጸመባቸው ። ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በደጃዝማች ፡ አባ ፡ ሻውል ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ ወደ ፡ ሐረርጌ ፡ ሂደው ፡ ታሠሩ ።

# ምዕራፍ ፡ ፯ ።

## ስለ ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ።

ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ፡ የተባሉት ፡ የሲዳሞ ፡ ገዢ ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ እየከዱ ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ በሎሌነት ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ ብስጭት ፡ አድሮባቸው ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በ፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ከሲዳሞ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ መጥተው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲደርሱ ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ በአንድነት ፡ በተቀመጡበት ፡ ወታደሮቻቸውን ፡ አሰልፈው ፡ እቤተ ፡ መንግሥቱ፡ ግቢ ፡ ሰልፍ ፡ አሳዩ ። ወታደሩ ፡ ሰልፉን ፡ ጨርሶ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ወደ ፡ ተቀመጡበት ፡ ሰገነት ፡ ቀርበው ፡ እጅ ፡ ነስተው ፡ ንግሥትን ፡ ጫማ ፡ ስመው ፡ ሲመለሱ ፡ የአልጋ ፡ ወራሽ ፡ መቀመጫ ፡ ባቅራቢያው ፡ ስለሆነ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ብድግ ፡ ብለው ፡ ለመሳም ፡ ሲሉ ፡ ጉንፋን ፡ ይዞኛል ፡ ብለው ፡ አመሐኝተው ፡ ሰላምታ ፡ ነፈጓቸው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በአልጋ ፡ ወራሽና ፡ በደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ መሐከል ፡ ጠብ ፡ መኖሩ ፡ በአደባባይ ፡ ተገለጠ ፤ እንደዚሁም ፡ የግብር፡ሰዓት ፡ ደርሶ ፡ ገበታቸው ፡ ከአልጋ ፡ ወራሽ ፡ ጋራ ፡ ስለነበረ ፡ አሁንም ፡ አሞኛልን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ አልመጣም ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡ ሳይገቡ ፡ ከውጭ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ፤ እቤታቸው ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ከሲዳሞ ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ የመጡት ፡ ለማስረከብ ፡ ኖሮ ፡ መቼም ፡ ቀን ፡ አልቆባቸዋልና ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እቤታቸው ፡ ሽፈቱና ፡ ቢጠሩም ፡ አልመጣም ፡ አሉ ። ሽማግሌ ፡ መልክተኛም ፡ ቢላክባቸው ፡ በእምቢታቸው ፡ ጸኑ ፡ ለጊዜው ፡ ከብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ በመሆናቸው ፡ በመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ማስጋትና ፡ ማሳሰባቸው ፡ አልቀረም ።

ነገር ፡ ግን ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ብዙ ፡ ሽማግሌ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ በመሆኑ ፡ ነገሩ ፡ በእርጋታ ፡ እንዲታሰብበት ፡ እንጂ ፡ እሳቸውን ፡ ተከትሎ ፡ የኃይል ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ተመከረና ፡ በርጋታ ፡ ታስቦበት ፡ አብሯቸው ፡ ያለው ፡ የሚበዛው ፡ ፩ የቁጥር ፡ ጦር ፡ የሆነው ፡ የመንግሥቱ፡

፩ የቁጥር ፡ ጦር ፤ የሚባለው ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ሻለቃ ፡ በሚሾምበት ፡ አገር ፡ ከሻለቃው ፡ የግል ፡ አሽከሮች ፡ የተለዩ ፡ በመንግሥት ፡ አሽከርነት ፡ የተቆጠሩ ፡ ናቸው ፡ ማደሪያቸው ፡ በተለይ ፡ በእነሱ ፡ ስም ፡ የተመደበ ፡ ሆኖ ፡ ሻለቃው ፡ ለነዚሁ ፡ መተዳደሪያ ፡ አድርጎ ፡ የሚጠብቀው ፡ እንጂ ፡ ለግል ፡ አሽከሮቹም ፡ ሆነ ፡ ለራሱ ፡ ማድቤት ፡ ቢቸገር ፡ የማይነካው ፡ ባለማደሪ ፡ የሆነ ፡ የመንግሥት ፡ አሽከሮች ፡ ናቸው ፡ ሻለቃ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሲሾም የግል ፡ አሽከሮቹን ፡ ይዞ ፡ ይመጣል ፡ እንጅ ፡ ደምበኛ ፡ የመንግሥት ፡ የሆነው ፡ ይህ ፡ የቁጥር ፡ ጦር ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራው ፡ ባገር ፡ ጠላት ፡ ሲመጣ ፡ በተለይ ፡ የሚአዘምት ፡ ጦር ፡ መጥቶ ፡ ሻለቃው ፡ እንዲዘምት ፡ ሲታዘዝ ፡ በዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ከሻለቃው ፡ እየታዘዙ ፡ አብረው ፡ ይዘምታሉ ፡ እንጅ ፡ በግል ፡ ጉዳይ ፡ የሚአዛቸው ፡ አይደሉም ።

ወታደር ፡ ስለሆነ ፡ አዋጅን ፡ ተከትሎ ፡ የሚሄድ ፡ ነውና ፡ በአዋጅ ፡ የሲዳሞ ፡ ግዛት ፡ ለሌላ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተወሰነና ፡ ለደጃዝማች ፡ ብሩ ፡ ወልደገብርኤል ፡ ተሰጠ ። እንደታሰበውም ፡ የቁጥር ፡ ጦሩ ፡ በሙሉ ፡ የመንግሥቱን ፡ አዋጅ ፡ ተከትሎ ፡ ጥሏቸው ፡ ወደ ፡ አዲሱ ፡ ተሿሚ ፡ ዘንድ ፡ ሲሄድ፡ የቤት ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ብቻ ፡ ቀሩ ። ቢሆንም ፡ በዚያው ፡ ባላቸው ፡ ማስቸገራቸው ፡ አልቀረም ።

ነገር ፡ ግን ፡ አሁንም ፡ ቢሆን ፡ በዘዴ ፡ ማሳሳትና ፡ መቅነስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኩተማ ፡ ውስጥ ፡ የኃይል ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ተመክሮ ፡ በሽማግሌ ፡ መላላክ ፡ ተጀምሮ ፡ ከብዙ ፡ መላላክ ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ እንዳልቀርብ ፡ ብቻ ፡ ቃል ፡ ይሰጠኝና ፡ እጄን ፡ እሰጣለሁ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። ይኸ ፡ ጥያቄያቸው ፡ የሚፈጸም ፡ መሆኑ ፡ ለሽማግሌዎች ፡ ተነገረና ፡ በተላኩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ አማካይነት ፡ የካቲት ፡ ፲ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ በአንድነት ፡ በተቀመጡበት ፡ ድንጋይ ፡ ተሸክመው ፡ ይቅርታ ፡ በመለመን ፡ ወድቀው ፡ እጅ ፡ ነሱና ፡ ተመለሱ ። ወዲያው ፡ የበደሉት ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፡ ስለሆነ ፡ በተለይ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ቤት ፡ ሄደው ፡ ይቅርታ ፡ ይጠይቁ ፡ ተባሉና ፡ ወዲዚያው ፡ ሄደው ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቀው ፡ ለማረፊያ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀላቸው ፡ ሥፍራ ፡ ሄደው ፡ አደሩ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በማግሥቱ ፡ ወደ ፡ ጎንት ፡ ሄደው ፡ እንዲቀመጡ ፡ ተወስኖ ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ ጎንት ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በአደባባይ ፡ ታይተው ፡ ቢሄዱ ፡ ምሕረቱ ፡ የፀና ፡ መሆኑ ፡ በተመልካች ፡ ዘንድ ፡ ስሜት ፡ የሚያሳድር ፡ ስለሚሆን ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከአደባባይ ፡ ታይተው ፡ በማግሥቱ ፡ ቢሄዱ ፡ ይሻላል ፡ በልና ፡ ንገር ፡ በማለት ፡ ከንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መላክተኛ ፡ ተልኮ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ መልክተኛው ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ ወደ ፡ ተወሰነላቸው ፡ ቦታ ፡ የሄዱ ፡ በመሆናቸው ፡ መልስ ፡ ተሰጠውና ፡ ተመለሰ ።

ደጃዝማች ፡ ባልቻም ፡ ጎንት ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ፡ ከተመልካች ፡ ጠባቂ ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ አገምጃ ፡ ርስታቸው ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ተወስኖ ፡ ለተመልካችነት ፡ ከተመረጡት ፡ ከቀኛዝማች ፡ ነጋሽ ፡ ጠንፋና ፡ ከግራዝማች ፡ ረታ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አገምጃ ፡ ለመሄድ ፡ ጉዞዋቸውን ፡ እንደቀጠሉ ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ ሲደርሱ ፡ ማርያምን ፡ ተሳልሜ ፡ ልሂድ ፡ አሉና ፡ ከዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ ደውያለሁ ፡ አልሄድም ፡ ቄስ ፡ ጥራ ፡ ብለው ፡ እምቢ ፡ አሉ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተመልካች ፡ ጠባቂ ፡ የተባሉት ፡ በመውደቅ ፡ በመነሳት ፡ ቢለምኑዋቸው ፡ እምቢ ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግራዝማች ፡ ረታ ፡



የተባለው ፡ በመበሳጨት ፡ የርስዎን ፡ እንጀራ ፡ አባሕር ፡ አግብተው ፡ ደግሞ ፡ በእኔ ፡ በደኃው ፡ እንጀራ ፡ ላይ ፡ ውኃ ፡ ጨመሩብት ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይይልዎ ፡ በማለት ፡ ምርር ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ይባላል ። ያም ፡ ሰው ፡ እንደፈራው ፡ አይረባም ፡ መባልን ፡ አትርሮ ፡ ከሹመቱም ፡ ተሽሮ ፡ ወደ ፡ ደጀ ፡ ጠኝነት ፡ ተዛውሮ ፡ ሲጉላላ ፡ ኖረ ። እርሳቸው ፡ አዲስ ፡ ዓለም ፡ ማርያም ፡ በዘበኛ ፡ እየተጠበቁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ስለርስታቸው ፡ ሙግት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በየፍርዱ ፡ አደባባይ ፡ ብቻ ፡ ድረስ ፡ እንዲገቡ ፡ ምሕረት ፡ ተደረገላቸውና ፡ የርስታቸውን ፡ ክርክር ፡ እየቀጠሉ ፡ ቆዩ ።

ያ ፡ ሁሉ ፡ ክብራቸው ፡ ጎደለና ፡ ዳኛና ፡ ከልካይ ፡ ሌላውም ፡ ባላጋራ ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ ተባበረና ፡ እያንገላታ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቆይተው ፡ ውርደት ፡ ሲጀምራቸው ፡ ጊዜ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ደውያለሁና ፡ አለቃውን ፡ ጥሩልኝ ፡ አሉ ።

ወደ ፡ መቃብር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ መምሕሩን ፡ ሲጠብቁ ፡ ቆይተው ፡ መምሕሩ ፡ ሲመጡ ፡ መደወሌን ፡ ይንገሩልኝ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ጃንሆይ ፡ ላኳቸው ። መምሕሩም ፡ ወዲያው ፡ ሄደው ፡ ለጃንሆይ ፡ ነገሩ ። ግርማዊነታቸውም ፡ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰውንና ፡ የዚህን ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ፡ እኔን ፡ ከበደ ፡ ተሰማን ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ እንድንጠራቸው ፡ ላኩን ፡ መልክተኞቹም ፡ እመቃብር ፡ ቤት ፡ እንዳያድሩ ፡ ይምጡና ፡ እልፍኝ ፡ አድረው ፡ ጉዳይምን ፡ ጧት ፡ ሊያመለክቱ ፡ ይችላሉ ፡ ብለዋል ፡ ብለው ፡ የጃንሆይን፡ ቃል ፡ ቢነግሯቸው ፡ መቼውንም ፡ ቢሆን ፡ ትዕቢት ፡ ከልባቸው ፡ ያልጠፋላቸው ፡ ሽማግሌው ፡ ደጃዝማች ፡ ለጃንሆይም ፡ ሆነ ፡ ለእኔ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ በአደባባይ ፡ ገብቼ ፡ ምህረት ፡ ሳገኝ ፡ እንጂ ፡ እኔን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ጧት ፡ ከእልፍኝ ፡ አይወጣም ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰለሰጡ ፡ ልብስና ፡ ምንጣፍ ፡ እራታቸው ፡ እዚያው ፡ እመቃብር ፡ ቤት ፡ እንዲሄድላቸው ፡ ተደርጎ ፡ እዚያው ፡ አድረው ፡ ጧት ፡ መምህሩ ፡ መስቀል ፡ ጭምር ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ መጡ ። ጃንሆይም ፡ መኳንንቱን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ አስቀምጠው ፡ ሲገናኟቸው ፡ ስለ ፡ ሥላሴ ፡ ብዬ ፡ ምሬሃለሁ ፡ ብለው ፡ ይማሩኝ ፡ ብለው ፡ ከጃንሆይ ፡ ፊት ፡ ወደቁ ።

ጃንሆይም ፡ ምን ፡ አደረግሁዎ ፡ ምን ፡ በድየዎታለሁ ፡ ይንገሩኝ ፡ አሏቸው ። እሳቸው ፡ እኔ ፡ ምሕረት ፡ ነው ፡ የጠየቅሁዎና ፡ ስለሥላሴ ፡ ብዬ ፡ ምሬሃለሁ ፡ ይበሉኝ ፡ ብቻ ፡ በማለት ፡ ተናገሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊነታቸውም ፡ ስለ ፡ ሥላሴ ፡ ብዬ ፡ ምሬዎታለሁ ፡ ብለው ፡ የምህረት ፡ ቃላቸውን ፡ አሰሟቸው ። የምህረቱን ፡ ቃል ፡ ከሰሙ ፡ በኋላ ፡ ሽማግሌው ፡ ደጃዝማች ፡ ምን ፡ አደረግሁህ ፡ ምን ፡ በደልሁህ ፡ ያሉኝ ፡ ምኔ ፡

ቀርቶዎታል ፤ ገንዘቤ ፡ ነው ፤ መሬቴ ፤ ደግሞስ ፡ ለዚህ ፡ አልጋ ፤ ለዚህ ፡ መንግሥት ፡ አልሞትሁም ፡ አላገለገልሁምን ፤ ደግሞስ ፡ እነዚህ ፡ እነዚህን ፡ ያመጣኋቸው ፡ እኔ ፡ አይደለሁምን ? ብለው ፡ ሲናገሩ ፡ ጃንሆይ ፡ ቀበል ፡ ብለው ፡ ሞያማ ፡ እማን ፡ ዘንድ ፡ ኖሯል ፡ ባሕሬ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰላም ፡ ሆነና ፡ ሲመለሱ ፡ እነዚህ ፡ እነዚህን ፡ ያመጣኋቸው ፡ እኔ ፡ አይደለሁምን ፡ ከተባሉት ፡ ለጊዜው ፡ የነበሩት ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ስለነበሩ ፡ እውጭ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ እኛን ፡ ግዳይ ፡ ጥለው ፡ ከጃንሆይ ፡ ባሬ ፡ ታረቁ ፡ በማለት ፡ ተናገሩ ።



ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ።

፩ ደጃዝማች ፡ ባልቻም ፡ ወንድሚ ፡ ቂም ፡ አትያዝብኝ ፡ ሳላስበው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እንቅ ፡ አድርገው ፡ ሳሟቸውና ፡ እርቀ ፡ ሰላም ፡ ሆኖ ፡ እንኳን ፡ እርስዎ ፡ ታረቁ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አይደል ፡ በማለት ፡ ተለያዩ ።

፩ ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሆነው ፡ ያደጉ ፡ በጅሮንድ ፡ ተብለው ፡ የገንዘብና ፡ የዕቃ ፡ግምጃ ፡ ቤትን ፡ ሹመት ፡ ሚኒስትር ፡ የሚባል ፡ የሹመት ፡ ማዕርግ ፡ ሳይጀመር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፡ አስተዳደር ፡ በዚሁ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ለነበረው ፡ ወታደር ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ስለነበሩ ፡ በአድዋ ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ በተለይም ፡ በመቀሌ ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ ጣሊያን ፡ ያጠቁ ፡ ከነበሩት ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የጀግንነት ፡ ሙያ ፡ ከሠሩት ፡ አንደኛው ፡ ናቸው ። በግዞት ፡ ላይም ፡ ግሎ ፡ ጠላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረበት ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ጀግንነት ፡ ጠላትን ፡ በማጥቃት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመግባት ፡ እስከ ፡ ወጨጫ ፡ ድረስ ፡ ዘልቀው ፡ በታላቅ ፡ ጀግንነት ፡ ጠላትን ፡ ያጠቁ ፡ ባለሙያ ፡ አርበኛ ፡ ናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲ ።

## ደጃዝማች ፡ አባውቃውና ፡ ጊዜው ።

ፊታውራሪ ፡ ገብረማርያም ፡ የአጼ ፡ ምኒልክ ፡ የዘበኛ ፡ አለቃ ፡ የነበሩት ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ ታስረው ፡ ነበር ። ንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ሲነግሡ ፡ ከታሰሩበት ፡ ተፈትተው ፡ መጥተው ፡ በቀድሞ ፡ ሥራቸው ፡ ተሾመው ፡ ሲኖሩ ፡ በሕመም ፡ ምክንያት ፡ ሲሞቱ ፡ በምትካቸው ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ብሩ ፡ ተሾመው ፡ ነበር ፤ እኚህ ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሰው ፡ ደጃዝማች ፡ ተሾመው ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ እንደቆዩ ፡ በሊጋባ ፡ ወዳጆ ፡ አስነሽነት ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ ከመሐል ፡ ሰፋሪዎች ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፡ እናንግሥ ፡ የማለት ፡ አድማ ፡ መጀመሩን ፡ ፩ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ሰምተው ፡ ኖሮ ፡ እንዴት ፡ ተደርጎ ፡ የእኛ ፡ ሕይወት ፡ ሳያልፍ ፡ ይህ ፡ ይደረጋል ፡ ብለው ፡ በበኩላቸው ፡ ከሚመስሏቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተነጋገሩ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ መጥተው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ አድማ ፡ መነሳቱን ፡ ሰምቻለሁና ፡ በንግሥትስ ፡ በኩል ፡ የተሰማና ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ወይ ? ንግሥት ፡ ሳይፈቅዱና ፡ ሳያውቁት ፡ በኃይል ፡ ባድማ ፡ ሊሠራ ፡ የታሰበ ፡ ነገር ፡ እንደሆነ ፡ የእኛ ፡ ሕይወት ፡ ሳያልፍ ፡ ሊፈጸም ፡ አይችልምና ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ይገለጽልኝ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁ ፤ ንግሥትም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ከአንተ ፡ ከመስማቴ ፡ በስተቀር ፡ ካሁን ፡ በፊት ፡ የሰማሁትና ፡ ያወቅሁት ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ወንድሚን ፡ ራስ ፡ ተፈሪን ፡ ብጠይቀው ፡ ሁሉንም ፡ አጣርቶ ፡ ይነግረኛልና ፡ እስከዚያ ፡ አርፈህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብለዋቸው ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፡ ጠርተው ፡ በመጠየቅ ፡ አነጋገሯቸው ። ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ ስም ፡ ለማጥፋት ፡ ሲል ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ የሚያስወራው ፡ ወሬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አይደረግም ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ስለሰጡ ፡ ንግሥትም ፡ በበኩላቸው ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ በበኩላቸው ፡ ነገሩን ፡ አጣርተው ፡ ጠይቀው ፡ ሊገናኙበት ፡ ተደረገና ፡ በቀጠሮ ፡ ተለያዩ ።

፩ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፤ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ ያደጉ ፡ የሻቃ ፡ አባውቃው ፡ በመባል ፡ የደረጃ ፡ እድገት ፡ ጀምረው ፡ የወታደር ፡ አለቃ ፡ የሆኑ ፡ በንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሊቀ ፡ መኳስንት ፡ የቡና ፡ ደጃዝማች ፡ ተብለው ፡ የወላሞ ፡ አውራጃ ፡ ገዥ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የልፍኝ ፡ ዘበኛ ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ የተሾሙት ፡ ናቸው ።

ከዚህ ፡ ቀጠሮ ፡ በኋላ ፡ በሌላ ፡ ቀን ፡ ነገሩ ፡ በሙብረድ ፡ ፋንታ ፡ ወሬው ፡ እየገነነ ፡ ሄዶ ፡ ኖሮ ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ቀጠሮ ፡ ጠይቀው ፡ ከንግሥት ፡ ለመነጋገር ፡ በሚመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ከጧቱ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ከቀጠሮው ፡ ሰዓት ፡ በፊት ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ መጡና ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ተናገሩ ። ዛሬ ፡ እኔ ፡ ልታሰርና ፡ የታሰበው ፡ ሊፈጸም ፡ በእኔም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ አጋፋሪ ፡ ወልደማርያም ፡ ሊሾም ፡ ተመክሮ ፡ መወሰኑን ፡ ሰምቻለሁ ። እኔ ፡ ከመያዜ ፡ በፊት ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከቤታቸው ፡ ሲመጡ ፡ ከዋናው ፡ በር ፡ ላይ ፡ እከላከላለሁና ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። አልጋ ፡ ወራሽ ፡ የሚመጣው ፡ ይህንኑ ፡ ያድማውን ፡ አነሳስ ፡ አጣርቶ ፡ ለመነጋገር ፡ በቀጠሮ ፡ ነውና ፡ መከልከል ፡ አይሆንም ፡ አንተም ፡ አሁን ፡ የነገርሽኝን ፡ ወንድሜ ፡ ሲመጣ ፡ ብጠይቀው ፡ ይነግረኛልና ፡ ነገሩን ፡ አጣርቼ ፡ እስታስታውቅህ ፡ ድረስ ፡ አርፈህ ፡ ተቀመጥ ፡ ብለው ፡ ገሰጿቸውና ፡ ተመልሰው ፡ ሄዱ ።

እንቁላል ፡ ቤት ፡ ከሚባለው ፡ ፎቅ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ወጥተው ፡ የአልጋ ፡ ወራሽን ፡ አመጣጥ ፡ በመነጽር ፡ ሲመለከቱ ፡ ቆይተው ፡ የአልጋ ፡ ወራሽ ፡ መምጣት ፡ ወደ ፡ ግቢው ፡ ሲቃረብ ፡ ከፎቅ ፡ ወርደው ፡ ወደ ፡ ማረፊያ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱና ፡ የሚመስሏቸውን ፡ ወታደሮች ፡ ሰብስበው ፡ በበኩላቸው ፡ ይመክሩ ፡ ጀመር ። አልጋ ፡ ወራሽም ፡ ጳጉሜ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሐሙስ ፡ በቀጠሮዋቸው ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ መጡና ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ገብተው ፡ ንግግር ፡ ጀምረው ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እረፍት ፡ ሳይደረግ ፡ ከጧቱ ፡ በ፫ ሰዓት ፡ የተጀመረ ፡ ንግግር ፡ እስከ ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ቆዩ ። ሲለያዩም ፡ ነገሩን ፡ ሰማሁ ፡ ያሉት ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃውና ፡ አድማውን ፡ አስነሱ ፡ የተባሉት ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄ ፡ እንዲታሰሩ ፡ ሆነው ፡ ነገሩ ፡ እንዲጣራ ፡ ተወስኖ ፡ እንደ ፡ ውሳኔው ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄ ፡ በአፈ ፡ ንጉሥ ፡ አረጋይ ፡ እጅ ፡ እንዲታሰሩ ፡ ሆነው ፡ ተይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃውን ፡ ለመያዝ ፡ የሄዱትን ፡ አጋፋሪ ፡ ወልደማርያምን ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ አልያዝም ፡ ብለው ፡ አጉላልተው ፡ መልሰዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ባሉበት ፡ በኩል ፡ የሽለላና ፡ የፉከራ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ ።

## ፪ ፡ በጊዜው ፡ ስለነበረው ፡ የሽብር ፡ ስጋት ፤

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ያ ፡ ዕብድ ፡ ደጃች ፡ አባውቃው ፡ ባለበት ፡ በኩል ፡ ሽለላና ፡ ፉከራ ፡ ይሰማልና ፡ አጋፋሪ ፡ ወልደማርያም ፡ ሊይዘው ፡ ሲሄድ ፡ እክፉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ እንዳይደርስ ፡ እኔ ፡ ወደዚህ ፡ ላስጠራውና ፡ ከሰው ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ ሲመጣ ፡ ቢያዝ ፡



ይሻላል ፡ ብለህ ፡ ንገር ፡ ተብሎ ፡ መላክተኛ ፡ ተላከ ፡ የዚህ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ እኔ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ተልኬ ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሀንድ ፡ ገና ፡ ሳልደርስና ፡ መልእክቱን ፡ ሳልነግር ፡ የተፈራው ፡ ነገር ፡ ደረሰና ፡ አጋፋሪ ፡ ወልደማርያምን ፡ አልያዝም ፡ በማለት ፡ አጉላልተው ፡ ከመለሷቸው ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ እያሸለሉና ፡ እያስፎከሩ ፡ ከማረፊያ ፡ ቤታቸው ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡ ብቅ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ከጧት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ጉዳዩ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ በማለት ፡ የጉባኤውን ፡ ውጤት ፡ ለመስማት ፡ በአደባባዩ ፡ የተሰበሰውብ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተሸበረና ፡ ድብልቅልቁ ፡ ወጣ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የተነሳውን ፡ የሽብር ፡ ሁኔታ ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ ለመተረክ ፡ አስቸጋሪ ፡ ስለሆነ ፡ አልፌው ፡ ወደ ፡ ዋናው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ እገባለሁ ።

ይህ ፡ አስጊ ፡ የነበረው ፡ ሽብርና ፡ ድብልቅልቅ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ደግሞም ፡ በደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ተፈላጊው ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ እራሳቸው ፡ መሆኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ያለምንም ፡ ሥጋት ፡ የተሸበረውን ፡ ሕዝብ ፡ በማጽናናት ፡ በመሐሉ ፡ ገብተው ፡ በሽመል ፡ እየመቱ ፡ ጸጥ ፡ እንዲል ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ። ካንዱ ፡ በር ፡ ወደ ፡ አንደኛው ፡ በር ፡ እየተዘዋወሩ ፡ በየበሩ ፡ ላይ ፡ ፀጥታውን ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ በሚያቆሙበት ፡ ጊዜ ፡ አንደኛው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ለጊዜው ፡ ካገኟቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተነጋግረው ፡ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ በሩን ፡ ወጣ ፡ ሲሉ ፡ አምስት ፡ ደቂቃ ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ እዚያች ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ደረሱ ። የእግዚአብሔር ፡ መጠበቅ ፡ የተጨመረበት ፡ ስለሆነ ፡ ያችን ፡ ሰዓት ፡ አሳለፉት ፡ እንጂ ፡ የግንባር ፡ ግንኙነት ፡ አጋጥሞ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በጣም ፡ የከፋ ፡ ይሆን ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ እየተሰቀቀ ፡ ያልተነጋገረበት ፡ አይገኝም ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሽብር ፡ በኋላ ፡ ጸጥታው ፡ ትንሽ ፡ መልክ ፡ ሲይዝ ፡ አልጋ ፡ ወራሹ ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ መጥተው ፡ ሲገናኙ ፡ ሽብሩ ፡ የሚያሳስብና ፡ የሚያሰጋ ፡ አለመሆኑን ፡ በመግለጥ ፡ ሲያስረዱና ፡ ከንግሥትም ፡ ዘንድ ፡ የሚነገረውን ፡ መልስ ፡ በቅርብ ፡ ሆነን ፡ ስንመለከት ፡ የእናትና ፡ ልጅ ፡ መተሳሰብ ፡ ያለበት ፡ ስለሆነ ፡ ጠቡ ፡ ከማነው ፡ በማለት ፡ በመገረም ፡ እናስብ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ጥቂት ፡ በማጽናናት ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ወጡና ፡ እንጨት ፡ ቤት ፡ ወደተባለችው ፡ ማረፊያ ፡ ቤታቸው ፡ ሄዱ ።

ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ በየበኩላችን ፡ በበር ፡ በበሩ ፡ ላይ ፡ ታማኝነት ፡ አላቸው ፡ የሚባሉትን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ሲደረግ ፡ ሁላችንም ፡ ድርሻ ፡ ድርሻችንን ፡ ስንጠብቅ ፡ ንግሥት ፡ ባሉበት ፡ ቤት ፡ በር ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፡ ከሌሊቱ ፡ ፮ ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ልጅ ፡ ሣህሌ ፡ ድልነሳሁ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ይጠሩሀል ፡ ብሎ ፡ መጥቶ ፡ ስለነገረኝ ፡ ሄድኩ ፡ አልጋ ፡

ወራሽ ፡ ዘንድ ፡ ስደርስ ፡ ከብዙ ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ደረስሁ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ለንግሥት ፡ እንድነግር ፡ የሚቀጥለው ፡ ቃል ፡ ተነግሮኝ ፡ ተላክሁ ።



ልጅ ፡ ማህሌ ፡ ድልነሳሁ ፡ (ፊታውራሪ) ።

ያ ፡ ዕብድ ፡ አባውቃው ፡ ከመታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ እተኩሳለሁ ፡ ይላልና ፡ ምናልባት ፡ ቢሰማ ፡ ንግሥት ፡ እንዲልኩበት ፡ የሚል ፡ ነው ። ይህን ፡ ቃል ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ወዲያው ፡ ሄጄ ፡ ነገርሁ ፤ ግርማዊት ፡ ንግሥትም ፡ ለጊዜው ፡ አሁን ፡ ባጠገቤ ፡ የሚገኙት ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንን ፡ ዋልቴና ፡ ቀኛዝማች ፡ ኃይሌ ፡ ሥላሴ ፡ ብቻ ፡ ናቸውና ፡ ማንኛቸው ፡ ቢላኩ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ጥያቄ ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተላከ ። ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንን ፡ ቢሄዱ ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ ከአልጋ ፡ ወራሽ ፡ መልስ ፡ ተሰጠ ፤ ንግሥትም ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንንን ፡ አስጠርተው ፡ እንዲሄዱ ፡ ነገሯቸው ።

ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንንም ፡ የጊዜውን ፡ አለመተማመን ፡ አስበው ፡ ብቻዬን ፡ አልሄድምና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ዘንድ ፡ ከሚገኙት ፡ መኳንንቶች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አብሮኝ ፡ እንዲሄድ ፡ ይጨመርና ፡ እሺ ፡ እሄዳለሁ ፡ ስላሉ ፡





ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንን ፡ ዋልተንጉሥ ።


ይኸው ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ፡ ተላከ ። አልጋ፡ ወራሽም ፡ [፩] ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሃብተሚካኤል ፡ ተጨምሮ ፡ ቢሄድ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ሐሳብ ፡ ቢልኩ ፡ ከንግሥት ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠው ፡ መልስ ፡ ታፈሰን ፡ እዚህ ፡ ጠብ ፡ ያደረሰኝ ፡ እሱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ እየተማረረ ፡ ሲናገር ፡ ተሰምቷልና ፡ የታፈሰ ፡ መሄድ ፡ ጠቃሚ ፡ አይሆንምና ፡ ሌላ፡ ይመረጥ ፡ የሚል ፡ ነበር ፡ እዚያ ፡ ከነበሩት ፡ መኳንንቶች ፡ መሐከል ፡ ማን ፡ እንደሚሄድ ፡ እንዲመረጥ ፡ ሐሳብ ፡ ቢቀርብ ፡ ሁሉም ፡ ጠበኛ ፡ ነን ፡ በማለት ፡ ለመሄድ ፡ አለመፍቀዳቸውን ፡ ገለጡ ።

በዚህ ፡ መሐል ፡ ደጃዝማች ፡ አምደ ፡ ሚካኤል ፡ ጣልቃ ፡ ገቡና ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ቃሉ ፡ የሚታመንና ፡ መልእክቱንም ፡ አስተካክሎ ፡ ለመናገር ፡ ልጅ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ቢላክ ፡ አይሻልም ፡ ወይ ፡ ሲሉ ፡ ሐሳብ ፡ ስላቀረቡ ፡ ሁሉም ፡ ተስማሙበትና ፡ ትሄድ ፡ ወይ ፡ ሲሉ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ጠየቁኝ ። እኔም ፡ ለመሄድ ፡ ፈቃደኛ ፡ መሆኔን ፡ ገልጬ ፡

---

፩ ፊታውራሪ ፡ ታፈሰ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ጥጇ ፡ ከደጃዝማች ፡ ገርማሜ ፡ ቤተሰብ ፡ የሚወለዱ ፡ የደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ የሆኑ ፡ በደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ቤት ፡ ያደጉ ፡ በኋላ ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሎሌ ፡ ሆነው ፡ ዑጋዴን ፡ ተሾመው ፡ የነበሩ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ አሽከርነት ፡ ተዛውረው ፡ ኢሉባቦር ፡ ነጋድራስ ፡ ሆነው ፡ የተሾሙ ፡ በኋላም ፡ የሥራ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ።

መልእክቱ ፡ የሚነገረው ፡ በንግሥት ፡ ቃል ፡ ሲሆን ፡ ንግሥት ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ያስፈልጋል ፡ ስል ፡ አሳሰብኩ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽም ፡ ንግሥት ፡ የፈቀዱ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንግሥት ፡ ካልፈቀዱ ፡ አይሆንም ፡ ይሸንኑ ፡ ሄደህ ፡ ለንግሥት ፡ ንገር ፡ ሲሉ ፡ አዘዙ ፡፡ እኔም ፡ ወዲ



ደጃዝማች ፡ ዓምደ ፡ ሚካኤል ፡ ሀብቱ ፡ ሥላሴ ፡፡


ያው ፡ ሄጄ ፡ ለንግሥት ፡ ነገርሁ ፡፡ ንግሥት ፡ ከበደ ፡ ምንም ፡ ለመልእክቱ ፡ ማስተካከል ፡ ቢመረጥ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ እንዳይመለከተው ፡ ፩ መምህር ፡ ደስታና ፡ ፪ አለቃ ፡ ደስታ ፡ አብረው ፡ ቢሄዱ ፡ የተሻለ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ መልስ ፡ ስለላኩ ፡ ነገሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ስለተስማሙበት ፡ ለምስታችንም ፡ የመልእክቱ ፡ ቃል ፡ ከንግሥት ፡ ተነገረንና ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ መታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ሄድን ፡፡

---

፩ መምህር ፡ ደስታ ፡ ቀድሞ ፡ የራስ ፡ ወሌ ፡ ብጡል ፡ የነፍስ ፡ አባት ፡ የነበሩ ፡ በኋላም ፡ በንግሥት ፡ ንግሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ የገብርኤል ፡ ደብር ፡ አለቃና ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ንግሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ትርጓሜ ፡ ያስረዱ ፡ የነበሩና ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጳጳስ ፡ እንዲሾሙ ፡ በተደረገበትም ፡ ጊዜ ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ ተሿሚዎች ፡ አንዱ ፡ ሲሆኑ ፡ ጠላትም ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይዞ ፡ በነበረበት ፡ ስዮቂት ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የነበሩ ፡ አቡነ ፡ አብርሃም ፡ ናቸው ፡፡

፪ አለቃ ፡ ደስታ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ደጋሚ ፡ ሆነው ፡ የቆዩና ፡ አጼ ፡ ምኒልክም ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ አጽማቸው ፡ በአረፈበት ፡ ስዕል ፡ ቤት ፡ በተባለው ፡ የአጼ ፡ ምኒልክ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ዳዊት ፡ እየደገሙ ፡ እስከ ፡ ንግሥት ፡ እቴጌ ፡ መውጣት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የቆዩ ፡ ሲሆን ፡ የእንጦጦ ፡ ማርያምን ፡ አለቅነት ፡ መልአከ ፡ ፀሐይ ፡ እየተባሉ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ያህል ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ፡፡





መምህር ፡ ደስታ ፡ (አቡነ ፡ አብርሃም) ፡፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ ከእልፍኝ ፡ ግቢ ፡ ሳንወጣ ፡ እበሩ ፡ ላይ ፡ መተማመን ፡ ባልነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ዘበኛ ፡ ቆሞበት ፡ አገኘንና ፡ ፫ ፊታውራሪ ፡ ደቻሳ ፡ የሚባሉት ፡ እንደደረስን ፡ ወዴት ፡ እንደምንሄድ ፡ ጠየቁ ፡፡ ጠብ ፡ ለማብረድ ፡ ከንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደጃዝማች ፡ አባ

---

፫ ፊታውራሪ ፡ ደቻሳ ፡ የትውልድ ፡ አገራቸው ፡ በጅባትና ፡ሜጫ ፡ አውራጃ ፡ የጨቦ ፡ ተወላጅ ፡ ጋላ ፡ ናቸው ፡፡ በአሽከር ፡ ነፍጠኛ ፡ ደንብ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተመንግሥት ፡ ያደጉ ፡ ሲሆን ፡ አገልግሎታቸው ፡ ለታማኝነት ፡ የሚያአበቃቸው ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ የእልፍኝ ፡ ዘበኛ ፡ ምክትል ፡ አዛዥ ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ፡፡ በዚሁ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ ታመው ፡ ሳለ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ያስተዳደር ፡ ዘመን ፡ አጼ ፡ ምኒልክን ፡ ወደ ፡ እንኮበር ፡ ሰደው ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ እቤቱ ፡ መንግሥቱ ፡ ሊገቡ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ስለተወራ ፡ ዋናው ፡ የዘበኛ ፡ አለቃ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያምና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ቀኛዝማች ፡ የነበሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ ደቻሳ ፡ የእኛ ፡ ሕይወት ፡ ሳያልፍ ፡ ጌታችንን ፡ ማነው ፡ የሚያስወጣ ፡ በማለት ፡ ከሌሎቹ ፡ የበታች ፡ ሹማምንቶች ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ሲከላከሉ ፡ ከልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ ከተላኩት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ እስከመታኮስ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፡ አቡነ ፡ ማቴዎስና ፡ እጨጌ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በመሐከሉ ፡ በአስታራቂነት ፡ ገብተው ፡ ጠቡ ፡ ከበረደ ፡ በኋላ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረማርያምና ፡ ቀኛዝማች ፡ ደቻሳ ፡ (ፊታውራሪ) ፡ እጃቸው ፡ ተይዞ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ በጌምድር ፡ ለራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (ንጉሥ) ፡ ተሰጥተው ፡ ሲታሠሩ ፡ ቀኛዝማች ፡ ደቻሳ ፡ (ፊታውራሪ) ፡ ጐጃም ፡ ለራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተሰጥተው ፡ ታስረው ፡ የነበሩ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥቱን ፡ ለቀው ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ሲነግሡ ፡ ከታሠሩበት ፡ ተፈተው ፡ መጥተው ፡ በቀድሞ ፡ ሥራቸው ፡ ተሾመው ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የጋሻ ፡ ጃግሬ ፡ ማለት ፡ የማለፊያ ፡ ጠመንጃ ፡ ያዥ ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ፡፡

ውቃው ፡ ተልከን ፡ የምንሄድ ፡ መሆናችንን ፡ ነገርኳቸው ። እሳቸውም ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ይህን ፡ በር ፡ እንድጠብቅ ፡ እኔን ፡ አዘውኛል ፡ ደግሞም ፡ እኔን ፡ የሚጠብቁ ፡ እነዚህን ፡ አዘዋል ፡ በማለት ፡ በጥቅሻ ፡ አሳዩኝ ። እነዚህ ፡ ተብለው ፡ በጥቅሻ ፡ ያሳዩኝ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሙሉነህና ፡ ፊታውራሪ ፡ ተሰማ ፡ ባንቲ ፡ ነበሩ ።



ልጅ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ (ደጃዝማች) ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሩን ፡ ከፈቱልንና ፡ ለማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ቁርጥ ፡ ለማወቅ ፡ ቁርጥ ፡ ጠብ ፡ በሆን ፡ ጊዜ ፡ ንገረን ፡ እንጂ ፡ በሌላው ፡ በኩል ፡ እንሰጋም ፡ በምኒልክ ፡ ልጅ ፡ ጥዛ ፡ የለም ፡ አደራህን ፡ አሉኝ ። አሮጌው ፡ ነፍጠኛ ፡ ደቻሳ ፡ የምኒልክ ፡ አሽከር ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ መሬቷ ፡ ጠባው ፡ መድረሻ ፡ ባጣበትና ፡ በተጨነቀበት ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ጋቢውን ፡ ተከናንቦ ፡ በርኖሱን ፡ እንደለበሰ ፡ ሐኔውና ፡ እጁ ፡ ብቻ ፡ ተገናኝተው ፡ እንደተማላ ፡ ሆኖ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፡ የሚጠብቀው ። መልክተኞቹም ፡ በንግሥትና ፡ በአልጋ ፡ ወራሽ ፡ መሐከል ፡ ምንም ፡ ጠብ ፡ አለመኖሩን ፡ አረጋግጠንላቸው ፡ በሩን ፡ ስንወጣ ፡ ሌሎቹ ፡ የዘበኞች ፡ አለቆች ፡ ከዘብ ፡ መደባቸው ፡ እየተነሱ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መጥተው ፡ በጌታችን ፡ በምኒልክ ፡ ልጅ ፡ የደረሰ ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ቁርጡን ፡ ንገሩን ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁ ፤ እኛም ፡ እንደ ፡



መጀመሪያው ፡ ቃል ፡ ጠብ ፡ አለመኖሩንና ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተስማምተው ፡ የላኩን ፡ መሆናችንን ፡ ገልጠን ፡ ነገርናቸውና ፡ ወደ ፡ ተላክንበት ፡ ሄድን ።

ከመታሰቢያ ፡ ቤት ፡ በር ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ በሩ ፡ እንዳይከፈት ፡ ከደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ለበረኛው ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጠ ፤ እኛም ፡ ከንግሥት ፡ በንድ ፡ የተላክን ፡ መሆናችንን ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ አስታወቅን ። ከርሳቸው ፡ በንድ ፡ ግን ፡ ያገኘነው ፡ መልስ ፡ ደርበህ ፡ በለው ፡ ማለትን ፡ ሲሆን ፡ ከውስጥ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ግራዝማች ፡ ዋሴ ፡ ዘመድ ፡ አገኘሁና ፡ ፩ ኩንተብ ፡ ወልደማርያም ፡ የተባለ ፡ የፊታውራሪ ፡ ገብረማርያም ፡ አሽከር ፡ የነበረው ፡ ተንግሥት ፡ ተልከናል ፡ ሲሉና ፡ ሰዎቹም ፡ የታወቁና ፡ የታመኑ ፡ ሲሆኑ ፡ አናስገባም ፡ ማለት ፡ አይገባም ፡ ብለው ፡ ተከላክለው ፡ በሩ ፡ ተከፍቶ ፡ እንድንገባ ፡ ሆነ ። በሩን ፡ በገባን ፡ ጊዜም ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ በመታሰቢያ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ከያዙ ፡ ሥራ ፡ ቢቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወጥተው ፡ እየተበላና ፡ እየተጠጣ ፡ እሳቸው ፡ ጠመንጃቸውን ፡ በክንዳቸው ፡ መንጃር ፡ ባንገታቸው ፡ ይዘው ፡ ሰይፋቸውን ፡ ታጥቀው ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ እየተንጐራደዱ ፡ መልክተኞቹን ፡ ተቀበሉን ፤ ጊዜያቱም ፡ ከሌሊቱ ፡ ወደ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ የተቃረበ ፡ ነበር ። መልክተኞችም ፡ ከንግሥት ፡ የተላክነውን ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እያስረዳን ፡ ብንነግራቸው ፡ ከንግሥት ፡ ቃል ፡ ካልሰማሁ ፡ ከናንተ ፡ የሰማሁትን ፡ መልክት ፡ ስለ ፡ ማላምነው ፡ ልሰማችሁ ፡ አልችልም ፡ በማለት ፡ መልስ ፡ ሰጡ ፤

ከመልክተኞቹ ፡ አንዱ ፡ የኛን ፡ ቃል ፡ ካልሰሙ ፡ በማንተማቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ጽሑፍ ፡ እናምጣልዎ ፡ ቢሏቸው ፡ ማኅተሙን ፡ የሚይዘው ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደመስቀል ፡ መሆኑን ፡ ስለማውቅ ፡ ጽሑፉ ፡ ቢመጣ ፡ አልሰማም ፤ ንግሥት ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የሚመጡበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ መጥተው ፡ ከቃላቸው ፡ ካልሰማሁ ፡ በመልክት ፡ የሚፈጸም ፡ አይደለም ። እስካሁንም ፡ የቆየሁት ፡ በመጨለሙ ፡ ሕግን ፡ ሴት ፡ ለመለየት ፡ ስላልተቻለ ፡ ነው ። እላይ ፡ ባመለከትኩት ፡ ዓይነት ፡ የንግሥትን ፡ ደኅንነት ፡ ከቃላቸው ፡ ካልሰማሁ ፡ ወገግ ፡ ብሎ ፡ ብርሃን ፡ ሲታይ ፡ መታኰሴ ፡ የማይቀር ፡ ነው ። በማለት ፡ በገነተረ ፡ ቃላቸው ፡ መለሱልን ።

መልክተኞቹም ፡ ይህንኑ ፡ ቃል ፡ ተመልሰው ፡ ለንግሥት ፡ አመለከቱ ። ንግሥትም ፡ የከብርን ፡ ነገር ፡ ሳይመለከቱ ፡ የጊዜውን ፡ ጸጥታ ፡ መጠበቅና ፡ ደም ፡ የሚያፋስስ ፡ ነገር ፡ እንዳይደርስ ፡ በማሰብ ፡ ወደ ፡

---

፩ ኩንተብ ፡ ወልደማርያም ፡ የእልፍኝ ፡ ዘበኛ ፡ የነበሩት ፡ የፊታውራሪ ፡ ገብረማርያም ፡ አጋፋሪ ፡ የነበረ ፡ ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ተዛውሮ ፡ በእልፍኝ ፡ ዘበኛ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ያገለግል ፡ የነበረ ፡ ነው ።

ተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ለመሄድ ፡ ታጥቀው ፡ ከተነሡ ፡ በኋላ ፡ መሄዳቸው ፡ እንዲታወቅ ፡ ወደ ፡ አሉጋ ፡ ወራሽ ፡ ተላከ ፡ የንግሥት ፡ ቃል ፡ እንደደረሳቸው ፡ አሉጋ ፡ ወራሽም ፡ ባጠገባቸው ፡ ይገኙ ፡ ለነበሩት ፡ መኳንንቶች ፡ ስላማከሯቸው ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ ከንግሥት ፡ ከቃላቸው ፡ ካልሰማሁ ፡ ካለ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተኩስ ፡ ተነስቶ ፡ ደም ፡ ከሚፋሰስ ፡ የንግሥት ፡ መሄድና ፡ ነገሩን ፡ ማብረድ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ተስማሙ ፤ ይኸን ፡ ጊዜ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከመኳንንቱ ፡ ሐሳብና ፡ አስተያየት ፡ በመለየት ፡ አንድ ፡ ሽፍታ ፡ በተነሳ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሱ ፡ ሄዶ ፡ መማለድ ፡ ይገባ ፡ አይመስለኝምና ፡ በእኔ ፡ አስተያየት ፡ ንግሥት ፡ እንዲሄዱ ፡ አልስማማም ። ስለዚህ ፡ የመኳንንቱንም ፡ አስተያየትና ፡ ሐሳብ ፡ እንደዚሁ ፡የእኔንም ፡ ሐሳብ ፡ ለይተህ ፡ ንገር ፡ ተብሎ ፡ ለመልክተኛው ፡ መልስ ፡ ተሰጠውና ፡ ይህንኑ ፡ በሁለት ፡ የተከፈለውን ፡ ቃል ፡ መልክተኛው ፡ ለንግሥት ፡ ቢነግራቸው ፡ በነገሩ ፡ ጥቂት ፡ ካሰቡበት ፡ በኋላ ፡ ባቅራቢያቸው ፡ የሚገኙትን ፡ ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንን ፡ ዋልቴንና ፡ ቀኛዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴን ፡ አስጠርተው ፡ ሐሳቡን ፡ አካፈሏቸው ።

፩ ቀኛዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተባሉት ፡ ነገሩን ፡ ወዲያው ፡ እንደሰሙ ፡ ቀበል ፡ አድርገው ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ከንግሥት ፡ ቃል ፡ ካልሰማሁ ፡ አላምንም ፡ ከሆነ ፡ ያለው ፡ ለዚህ ፡ ሲባል ፡ ንግሥትንም ፡ እዚያ ፡ ድረስ ፡ መሄድ ፡ አያስፈልግም ፤ አሁን ፡ ስልክ ፡ ቢጠለፍ ፡ ይደርሳልና ፡ ንግሥት ፡ በስልክ ፡ ቢያነጋግሩት ፡ ይሻላል ፡ ሲሉ ፡ ሐሳብ ፡ አቀረቡ ፤ ንግሥትም ፡ ስልክ ፡ ተቀጥሎ ፡ ለመነጋገር ፡ የሚደርስ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ የተሻለ ፡ ነውና ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ይነገርና ፡ በሐሳቡ ፡ የሚስማማበት ፡ ሲሆን ፡ ወዲያው ፡ ስልኩ ፡ እንዲቀጠል ፡ ይሁን ፡ ስላሉ ፡ ወደ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተላከ ።

ይህም ፡ ቃል ፡በአልጋ ፡ ወራሽም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ በነበሩት ፡ መኳንንቶች ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ሆኖ ፡ ስለተፈቀደ ፡ የፖስታ ፡ ሚኒስቴሩም ፡ እዚያው ፡ ስለነበሩ ፡ ወዲያው ፡ ተነገረና ፡ የስልክ ፡ መቀጠሉ ፡ ሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ስለተከናወነ ፡ ንግሥት ፡ በስልክ ፡ አስቀርበው ፡ ከመታሰቢያ ፡ ቤቱ ፡ ላይ ፡ የሸፈቱትን ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃውን ፡ አነጋገሯቸው ። በንግግሩም ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ለአባቴ ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ነዋሪ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ያሠራሁት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባልረባና ፡ ባልተጣራ ፡ ነገር ፡ ተነስተህ ፡

፩ ቀኛዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መገኖ ፡ የአጼ ፡ ምኒልክ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሆነው ፡ ያደጉ ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፩ኛ ፡ የሌባ ፡ ሻይ ፡ አጠጭዎች ፡ አለቃ ፡ ፪ኛ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሹምና ፡ የሰይፈ ፡ ጃግሬዎች ፡ አለቃ ፤ ፫ኛ ፡ በተለይ ፡ ለግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ የልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡ የበላይ ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ ሲሠሩ ፤ የቆዩ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ አዛዥ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተብለው ፡ እንደራሴነት ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ።





ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታ ፡ (ራስ) ።

ላንተ ፡ መታከሻ ፡ ሆኖ ፡ ይደፈርን ? የሚል ፡ ቃል ፡ በቁጣ ፡ ተነገረ ። ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ከዚህ ፡ ተግሣጽ ፡ ቃል ፡ በኋላ ፡ እረ ፡ ለመሆኑ ፡ ንግሥት ፡ ደኅና ፡ ነዎት ፡ ወይ ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁ ። ምናለብኝ ፡ ደኅና ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ መለሱላቸው ፤ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ከንግሥት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሲሰሙ ፡ በንግሥት ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የደረሰ ፡ ነገር ፡ ይኖራል ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ንግሥትማ ፡ በደኅና ፡ ካሉ ፡ እንግዲያው ፡ እኔ ፡ አልነግሥ ፡ የሚይዘኝ ፡ ሰው ፡ ይላክ ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰጡ ። ወዲያው ፡ እጨጌ ፡ ገብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (አቡነ ፡ ማቴዎስና) ፡ እኔ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ሄደን ፡ በደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ሰንሰለት ፡ አግብተን ፡ ይዘናቸው ፡ መጣን ።

## ፫ኛ ፤ የሸብሩ ፡ ጊዜያት ፡ አልፎ ፡ በፍርድ ፡ ስለመወሰኑ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሸብሩ ፡ ሁናቴ ፡ ታልፎ ፡ ነገሩ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አፈጻጸም ፡ ተለወጠና ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ፍርዱ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደሚፈጸም ፡ ይነጋገሩበት ፡ ጀመር ። የንግግሩም ፡ ዓይነት ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ለማሳለፍ ፡ የተነሳ ፡ አመጸኛ ፡ ስለሆነ ፡ በችሎት ፡ ቀርቦ ፡ ነገሩ ፡ ታይቶ ፡ ውሳኔ ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ የፍርዱ ፡ ውሳኔ ፡ በሞት ፡ እንዲቀጣ ፡ የሆን ፡

እንደሆነ ፡ ያለምህረት ፡ እንደፍርዱ ፡ ቅጣቱ ፡ በሞት ፡ እንዲፈጸም ፡ በማለት ፡ ሲሆን ፡ በንግሥት ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ አስቦ ፡ ይነሳ ፡ እንጂ ፡ በተነሳበት ፡ ነገር ፡ ነፍስ ፡ የጠፋ ፡ ስላልሆነ ፡ ባልተጣራ ፡ ነገር ፡ በመነሳቱ ፡ ሞት ፡ ቢፈረድበትም ፡ በእሥራት ፡ ቢቀጣ ፡ እንጂ ፡ በሞት ፡ መቀጣቱ ፡ ቅር ፡ ያሰኛል ፡ ሲሉ ፡ ሐሳብ ፡ ስለሰጡ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ በአልጋ ፡ ወራሽና ፡ በንግሥት ፡ መሐከል ፡ ጥቂት ፡ የሐሳብ ፡ መለያየት ፡ መጣና ፡ በሽማግሌ ፡ መነጋገር ፡ ጀመሩ ። በመሐል ፡ ገብተው ፡ በሽምግልና ፡ ይላላኩ ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታና ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ጻድቅ ፡ ነበሩ ፡ ነገሩም ፡ በፍርድ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሆነና ፡ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ችሎት ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈረደባቸውና ፡ የሞቱ ፡ ፍርድ ፡ በእሥራት ፡ ተለውጦ ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ታስረው ፡ ወደ ፡ እንኮበር ፡ እንዲላኩ ፡ ተወሰነ ።



ቀኛዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።



ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ (ቢቶደድ) ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ በተፈረደበት ፡ ቀን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የወንጀለኛ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዴንት ፡ የነበሩት ፡ ዳኛ ፡ ደጃዝማች ፡ መስፍን ፡ ገመች ፡ በአደባባዩ ፡ ማለት ፡ ፍርድ ፡ በተሰጠበት ፡ አቅራቢያ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ሲኖሩ ፡ በችሎቱ ፡ ላይ ፡ አልተገኙም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በችሎቱ ፡ ቦታ ፡ ቆይቼ ፡ የፍርዱን ፡ ውሳኔ ፡ ሰምቼ ፡ ስመለስ ፡ እላይ ፡ ስማቸው ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሰው ፡ አገኘኋቸውና ፡ ምነው ፡ እዚህ ፡ ተቀምጠዋል ፡

ቀኛዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ገጽ ፡ ፹፬ ፡ ተመልከት ።



የደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ፍርድ ፡ አሁን ፡ እኮ ፡ ነበር ፡ ተፈርዶ ፡ አልቆ ፡ ችሎት ፡ መልስ ፡ ሆነ ፡ አልኳቸው ። እርሳቸውም ፡ ምን ፡ ልፈርድ ፡ ልሂድ ፡ አሉኝ ፤ እኔም ፡ በችሎቱ ፡ የተገኘው ፡ መኳንንትና ፡ ወንበሮችም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥቱም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ፈረደባቸው ፡ ብዬ ፡ ስነግራቸው ፡ እኝህ ፡ ሰው ፡ ከችሎቱ ፡ የቀሩበትን ፡ ምክንያት ፡ የሚያስረዳ ፡ ንግግር ፡ ነገሩኝ ፤ ለፈራጅ ፡ አስቸጋሪነቱም ፡ ገለጹልኝ ፡ ቃሉም ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።



ደጃዝማች ፡ መስፍን ፡ ገመች ።

በፍትሐ ፡ ነገሥቱ ፡ ባንዱ ፡ አንቀጽ ፡ ጌታውን ፡ የከዳና ፡ የወጋ ፡ ይሙት ፡ ሲል ፡ ደግሞ ፡ ባንደኛው ፡ አንቀጽ ፡ በጌታው ፡ የደረሰውን ፡ አደጋ ፡ ለመከላከል ፡ ሲል ፡ ቢገል ፡ ሞት ፡ የለበትም ፡ ይላል ፤ ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ጥፋት ፡ ማንኛው ፡ ነው ፡ አሉኝ ።

ምን ፡ ልመልስላቸው ፡ ፍርድ ፡ የተፈጸመባቸው ፡ ወንጀለኛ ፡ የሆኑት ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ሁለቱንም ፡ የሠሩ ፡ ሆነው ፡ ተገኝተዋል ።

እንግዲህ ፡ የነገሩን ፡ ሁናቴ ፡ ከገለጽሁ ፡ በኋላ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ አስተዳደር ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ለፈራጅ ፡ አስቸጋሪ ፡ የሆኑ ፡ ነገሮች ፡ ይገጥሙት ፡ እንደነበረ ፡ ለማስረዳት ፡ ያህል ፡ ልገልጸው ፡ እወዳለሁ ።

እንግዲህ ፡ የደጃዝማች ፡ አባ ፡ ውቃው ፡ ወንጀል ፡ ባልጋ ፡ ወራሽ ፡ በኩል ፡ ሆነው ፡ ሲመለከቱት ፡ ጌታቸውን ፡ የከዱና ፡ በጌታቸው ፡ ላይ ፡ ያመጹ ፡ መሆናቸውን ፡ ያሳያል ። ደግሞ ፡ በንግሥት ፡ በኩል ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከቱት ፡ በጌታው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ እንዳይደርስ ፡ የመጠበቅ ፡ ተግባሩን ፡ የመፈጸም ፡ ሁናቴን ፡ የሚያሳይ ፡ ሆኗል ።

ጌታ ፡ በወንጌል ፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ለሁለት ፡ ጌታ ፡ ሊገዛ ፡ ወይም ፡ ሊታዘዝ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ቢጠቀስ ፡ ተገቢ ፡ ቦታውን ፡ ሳያገኝ ፡ አልቀረም ፡ እላለሁ ።

## ፬ኛ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ንጉሥ ፡ ስለመባላቸው ።

ይህ ፡ በዚህ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ተፈጠረና ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፡ ንጉሥ ፡ ብለው ፡ ይሹሙልን ፡ ነገረኛ ፡ ያውጡልን ፡ በማለት ፡ አዲስ ፡ አድማ ፡ ተነሳ ። ለዚህም ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ያልታወቁና ፡ እቁጥር ፡ የማይገቡ ፡ ሰዎች ፡ ተልከው ፡ እንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ሲቀርቡ ፡ መጀመሪያ ፡ ጠያቂ ፡ ሆነው ፡ የቀረቡት ፡ ሰዎች ፡ ያልታወቁ ፡ ተራ ፡ ሰዎች ፡ በመሆናቸው ፡ ደግመኛም ፡ በፈቃድ ፡ የሚደረገውን ፡ በአድማ ፡ በመጠየቁ ፡ ንግሥትን ፡ ጥቂት ፡ ሳያሳዝናቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበር ። መልክተኛ ፡ ሆነው ፡ የመጡትንም ፡ ሰዎች ፡ ኧረ ፡ ለመሆኑ ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ጠያቂ ፡ ሆናችሁ ፡ የቀረባችሁት ፡ ፩ እነማን ፡ ናችሁ፤ የሰው፡ አለመኖር ፡ የሚታወቀው ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ እናንተ ፡ ተልካችሁ ፡ መምጣታችሁ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በቁጣ ፡ ቃል ፡ መለሷቸው ።

እነሱን ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ከመለሷቸው ፡ በኋላ ፡ በጉዳዩ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽን ፡ ጠርተው ፡ ተነጋገሩበትና ፡ በነገሩ ፡ አስበውበት ፡ ንግሥት ፡ በፈቃዳቸው፡ በ፲፱፻፳፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፳፪ ፡ ቀን፡ የጐንደር ፡ ንጉሥና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ብለው ፡ ሾሟቸውና፡ ለወትሮው ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ይበላ ፡ የነበረው ፡ የግብር ፡ ሥርዓት ፡ ተለወጠ ። በየቀኑ ፡ የነበረውም ፡ ግንኙነትና ፡ መመካከር ፡ ቀረና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ግብር ፡ የሚያበሉበትና ፡ ሥራም ፡ የሚያከናውኑበት ፡ የተለየ ፡ ቤት ፡ ተዘጋጅና ፡ ዓይነቱ ፡ ለወጥ ፡ ብሎ ፡ መሠራት ፡ ጀመረ ።

፩ እነማናችሁ ፡ የተባሉት ፡ ሰዎች ፡ ቀኛዝማች ፡ ባንትይዋሉና ፡ ግራዝማች ፡ ይገዙ ፡ እንደልቡ ፡ ናቸው ። ቀኛዝማች ፡ ባንትይዋሉ ፡ የፊታውራሪ ፡ ሀብተማርያም ፡ አሽከር ፡ የነበሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ተዛውረው ፡ የገቡ ፡ ናቸው ። ግራዝማች ፡ ይገዙ ፡ በአራዳ ፡ ዘበኞች ፡ ውስጥ ፡ ዳኛ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ነው ።





ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡ ምንም ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ቢፈጸም ፡ አዲስ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ በመሆኑ ፡ ጥቂት ፡ ቅሬታን ፡ ሳያሳይ ፡ አልቀረም ፡ ነበር ፡ ቅሬታንም ፡ ያስከተሉት ፡ ነገሮች ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ተሰማኝና ፡ እንደአወቅሁት ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተጻፉት ፡ ናቸው ፡

፩ኛ/ በፈቃድ ፡ የሚሆነውን ፡ በአድማ ፡ መጠየቁ ፡
፪ኛ/ ንጉሥ ፡ የመባሉ ፡ ጉዳይ ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ከተነጋገሩበት ፡ በኋላ ፡ ሲፈቀድ ፡ በዓሉ ፡ የሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሆንላቸው ፡ በልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሲፈለግ ፡ በግርማ

ዊት ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚደረገው ፡ የዘውድ ፡ በዓል፡ ለንጉሡ ፡ ንግሥት ፡ ሲሆን ፡ ንጉሡ ፡ ንግሥቱ ፡ ንጉሥ ፡ ብሎ ፡ የሚሾመው ፡ ንጉሥ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ንጉሡ ፡ ንግሥቱ ፡ ዘውዱን ፡ ያደርግለታል ፡ እንጂ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይደለም ። በማለት ፡ ነበር ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ንግግር ፡ ከተደረገበት ፡ በኋላ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሆኑ ፡ ቀርቶ ፡ አማካይ ፡ በሆነ ፡ በመሐከለኛ ፡ አኳኋን ፡ እንዲፈጸም ፡ ሆኖ ፡ ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ በታች ፡ ጐተራ ፡ ሜዳ ፡ ይባል ፡ ከነበረው ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ የቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ታላላቅ ፡ ድንኳኖች ፡ ተተክለው ፡ የንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ንግሥት ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ የንጉሥነት ፡ ዘውድ ፡ በንግሥት ፡ እጅ ፡ ለልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ተደረገላቸውና ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንደገለጽሁት ፡ የጐንደር ፡ ንጉሥ ፡ ተብለው ፡ ከተሰየሙ ፡ በኋላ ፡ ሠረገላ ፡ ቀርቦላቸው ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ታጅበው ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄደው ፡ ለዚህ ፡ ላበቃቸው፡ አምላክ ፡ የምሥጋና ፡ ጸሎት ፡ አድርሰው ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ ግቢ ፡ በኋላ፡ ገነተ ፡ ልዑል ፡ ወደተባለው ፡ ቤታቸው ፡ ወጥተው ፡ ለበዓሉ ፡ ክብር ፡ የተከተለውን ፡ መጣፍንት ፡ መኳንንትና ፡ መላውን ፡ ሕዝብ ፡ ግብር ፡ አበሉ ።

ከዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ ንግሥትና ፡ አልጋ፡ ወራሽ ፡ እንደቀድሞው ፡ ሳይሆን ፡ በቀጠሮና ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ እየተናኙ ፡ ከአንገት ፡ በላይ ፡ በሆነ ፡ በፖለቲካ ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ እየተ ነጋገሩ ፡ ጊዜውን ፡ ያሳልፉት ፡ ነበር ።

ይህን ፡ ታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ የምጽፈው ፡ በቅርብ ፡ ሆኜ ፡ ሁኔታ ውን ፡ እንዳጠናሁት ፡ የንግሥትን ፡ አስተያየትና ፡ ሐሳብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በተመለከተው ፡ ዐረፍተ ፡ ነገር ፡ በአጭሩ ፡ እገልጻለሁ ።

«እኔን ፡ ሳያውቀኝና ፡ ሳልጠቅመው ፡ የአባቴን ፡ ውለታና ፡ ወሮታ ፡ ለመመለስ ፡ ሲል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሳፍንት ፡ መኳንንትና ፡ ሕዝቡም ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታግዞ ፡ ለአባቴ ፡ ዙፋን ፡ ቢያበቃኝ ፡ ከኔ ፡ አስተ ዳደር ፡ አለማወቅ ፡ የተነሳ ፡ ሕዝቡ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ተፋጅቶ ፡ ከሚያል ቅና ፡ ራሳቸውን ፡ አልቻሉም ፡ ተብሎ ፡ በዘመኑ ፡ መንግሥቴ ፡ የባዕድ ፡ መንግሥትና ፡ ገዢ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ከሚገባ ፡ እኔ ፡ የተጠየቅሁትን ፡ ሥልጣን ፡ እየለቀቅሁና ፡ እየሰጠሁ ፡ ነገሩን ፡ ማብረድ ፡ ይሻላል» ፡ በማ ለት ፡ ለጊዜው ፡ የሚገጥማቸውን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ትእግሥት ፡ ያሳልፉት ፡ እንደነበረ ፡ በግልጽ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተተቀውንም ፡ ቃል ፡ ስጽፍ ፡ ከራሴ ፡ ሐሳብ ፡ ያነ ቃሁት ፡ ሳይሆን ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ከመኳንንቱም ፡ ሆነ ፡ ከመሐል ፡ ሰፋሪ ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ ዘንድ ፡ እየመጡ ፡ ጥቃትዎንና ፡



በደለዎን ፡ አንወድምና ፡ ቅር ፡ የተሰኙበት ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ይንገሩን ፡ እያሉ ፡ ሲጠይቋቸው ፡ እነዚህን ፡ ለመሰሉት ፡ ሰዎች ፡ መልስ ፡ ሲሰጡ ፡ ከንግሥት ፡ የተነገረውን ፡ በመስማቴ ፡ ገለጽሁ ፡ እንጂ ፡ አስመስዬ ፡ በመናገር ፡ የተጻፈ ፡ አይደለም ፡ በጊዜው ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እውነትም ፡ ሆነ ፡ ለሐሰት ፡ እንግሥትም ፡ ዘንድ ፡ ሆነ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ዘንድ ፡ አሳቢ ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ እያስመሰለ ፡ የሚናገር ፡ ብዙ ፡ ነበር ።

ለምሳሌ ፡ ከመሐል ፡ ሰፋሪዎች ፡ ወይም ፡ ከደጅ ፡ አጋፋሪዎች ፡ ውስጥ ፡ ግራዝማች ፡ ኃይሌ ፡ እንደብልሃቱ ፡ ይባል ፡ የነበረውን ፡ ከዕለ ታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከላይ ፡ በምዕራፍ ፡ ፯ ፡ እንደገለጽሁት ፡ ስለ ፡ ደጃዝ ማች ፡ ባልቻ ፡ ጉዳይ ፡ ከንግሥት ፡ ተልኬ ፡ ማለዳ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ቤት ፡ ሄጄ ፡ ነበር ፡ ይህን ፡ ስሙ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ሰው ፡ የአልጋ ፡ ወራሽ ፡ ምክ ትል ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ ከነበረ ፡ ከግራዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አረጋይ ፡ ጋራ ፡ ከላይኛው ፡ ግቢ ፡ እልፍኝ ፡ ደጃፍ ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘሁት ። ወደ ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ዘንድ ፡ ገብቼ ፡ መልክቱን ፡ ተናግሬ ፡ ብመለስ ፡ ያን ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ ከነበረበት ፡ ቦታ ፡ አጣሁት ። ይህም ፡ ሰው ፡ ከላይ ፡ እታች ፡ እያለ ፡ የሚያመላልሰውን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ንግሥትም ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ አቀባይ ፡ ሞሮታል ፡ የእኔን ፡ ከንግሥት ፡ ዘንድ ፡ ተልኬ ፡ መሄዴን ፡ አላ ወቀም ። በእርሱ ፡ ግምት ፡ እንደርሱ ፡ ከላይ ፡ እታች ፡ ነገር ፡ የማመላልስ ፡ መስሎውና ፡ ወዲያው ፡ በፍጥነት ፡ ከላይኛው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ንግሥት ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ደርሶ ፡ ልጅ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ በማለዳ ፡ ሰው ፡ ሳያየው ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ቤት ፡ ተደብቆ ፡ ገብቶ ፡ አየሁት ፡ የንግሥትን ፡ ምስጢር ፡ ለመናገር ፡ ሳይሆን ፡ አይቀር ምና ፡ ጉዱ ፡ እንዲገለጥ ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ ቢፈለግ ፡ ባለመገኘቱ ፡ ይታወ ቃል ፡ በማለት ፡ ተናግሮ ፡ ኖሮ ፡ ለንግሥት ፡ እኔ ፡ ከመመለሴ ፡ በፊት ፡ ወሬው ፡ ደርሷቸው ፡ ነበር ። እኔም ፡ ተመልሼ ፡ መጥቼ ፡ የተላኩበትን ፡ ጉዳይ ፡ መልሱን ፡ ከነገርኋቸው ፡ በኋላ ፡ አንተን ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ቤት ፡ ስትገባ ፡ ያየህ ፡ ሰው ፡ ከእኔ ፡ ሳትላክ ፡ የእኔን ፡ ምስጢር ፡ ለማውጣት ፡ ተደብቀህ ፡ እንደሄድክ ፡ አድርጎ ፡ ላከብኝ ፡ ስትገባ ፡ ማን ፡ አይቶህ ፡ ነበር ፡ ሲሉ ፡ ጠየቁኝ ፤ እኔም ፡ ስገባ ፡ ያየሁት ፡ ማን ፡ እንደነበረና ፡ ስወ ጣም ፡ እንዳጣሁት ፡ ገልጬ ፡ ስለ ፡ ነገርኋቸው ፡ በመገረም ፡ ሳቁና ፡ አሳ ለፉት ። እንግዲህ ፡ ነገሩ ፡ በትኩሱ ፡ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ በመነገሩ ፡ ሌላ ፡ ማስረጃ ፡ ሳያሻ ፡ ንግሥት ፡ እራሳቸው ፡ የላኩኝ ፡ መሆናቸውን ፡ አስታውሰው ፡ ባያሳልፉት ፡ ነገሩም ፡ ቆይቶ ፡ በተረሳበት ፡ ጊዜ ፡ ተነ ግሮ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ነገረ ፡ ሠሪው ፡ በቅን ፡ ሠራተኛው ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥሎበት ፡ ሊያጠፋው ፡ ነበር ።

ይህንንም ፡ ቃል ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መጥቀሴ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የዕለት ፡ እንጀራ ፡ ፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ ሲቀባጥር ፡ ነገሩ ፡ እየከረረ ፡ ከትልቅ ፡ ጠብ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ሳይጣራ ፡ በመቅረቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቢጣራ ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ ሁናቴ ፡ ከፍሬው ፡ ገለባው ፡ ይበዛ ፡ እንደነበረ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ (የቋና) ፡ ውጊያ ።

### ፩ኛ ፤ ጉግሣ ፡ ወሌና ፡ የአንችም ፡ ውጊያ ።

ይህ ፡ ታልፎ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደቆየ ፡ የበጌምድሩ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢ ፡ ቀድሞ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ባል ፡ የነበሩት ፡ እላይ ፡ጠቀሼ፡ እንደነበረውና ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ያልተደረገውን ፡ ተደረገ ፡ በሚል ፡ በሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ ተመርተው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ትእዛዝና ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ሆነው ፡ ከንግሥትም ፡ ከአሊጋ ፡ ወራሽም ፡ መልክት ፡ ቢላክባቸው ፡ አልሰማም ፡ ብለው ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ለመዋጋት ፡ መደራጀታቸው ፡ ተሰማ ።

በመንግሥቱም ፡ በኩል ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ መላላክ ፡ በኋላ ፡ የማይመለሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ ተረዳ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታን ፡ አዝዞ ፤ እሺ ፡ ቢሉ ፡ በሰላም ፡ እንዲገቡ ፡ እምቢም ፡ ቢሉ ፡ በማስገደድ ፡ አስፈላጊውን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ በ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ላኳቸው ። የጦር ፡ ሚኒስትሩም ፡ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ለመፈጸም ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ቤጌምድር ፡ ተጉዘው ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ፩ ቋና ፡ አንችም፡ ከተባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ጦር ፡ ተገናኘ ። በሰላም ፡ ለመግባት ፡ የታሰበውም ፡ ቀርቶ ፡ ተዋጉና ፡ በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ መጋቢት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።

### ፪ኛ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ማረፍ ፤

ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱም ፡ የጦር ፡ ሚኒስትራቸው ፡ ድል ፡ ማድረጋቸውን ፡ ሲሰሙ ፡ የራስ ፡ ጉግሣን ፡ በጦሩ ፡ ላይ ፡ መሞት ፡ ገና ፡ ሳይሰሙ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ግሬብ ፡ አድርጎ አሟቸው ፡ በነበረው ፡ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ መጋቢት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ዓ ፡ ም ፡ አረፉ ። ሥርዐቱ ፡ ቀብራቸውም ፡ ለአባታቸው ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ባሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምድር ፡ ቤቱ ፡ አረፈ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ተብለው ፡ በዙፋኑ ፡ ተተኩ ።

፩ ቋና ፡ አንችም ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።